# ፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን

## የተሽከርካሪ አገልግሎት አሰጣጥና ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ

## አሰራር መመሪያ ቁጥር 671/2013

የካቲት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ


መግቢያ ........ 1

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ ........ 2

1. አጭር ርዕስ ........ 2
2. ትርጓሜ ........ 2
3. የተፈጻሚነት ወሰን ........ 7

ክፍል ሁለት

የተለያዩ ተቋማት መስፈርትና የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራና ምዝገባ ........ 8

4. የተሽከርካሪ አስመጪዎች ሊያሟሏቸዉ የሚገቡ መስፈርቶች ........ 8
5. የተሽከርካሪ ማስገቢያ ፈቃድ ........ 9
6. ተሽከርካሪ ሀገር ውስጥ ለሚገጣጥሙ እና ለሚያመርቱ ተሽከርካሪ አምራቾች የሚያስፈልገው መስፈርት ........ 10
7. ለአስመጪ የሚሰጥ ኢት ተላላፊ ሰሌዳ ........ 10
8. ተሽከርካሪን ወደ ምዝገባ ቦታ ለማድረስ የሚወሰድ ተላላፊ ሰሌዳ ........ 11
9. የተሽከርካሪ የምዝገባና የሰሌዳ ዓይነቶች ........ 12
10. ለተሽከርካሪ ምዝገባ የሚደረግ የቴክኒክ ምርመራ ........ 13
11. አዲስ ተሽከርካሪ ምዝገባ ........ 13
12. ለአዲስ ተሽከርካሪ ምዝገባ የሚያስፈልጉ ሰነዶች ........ 14
13. በሀገር ውስጥ ከሚመረቱ እና ከሚገጣጥሙ ተሽከርካሪዎችን ገዝቶ ለምዝገባ ሲቀርቡ የሚያስፈልጉ ሰነዶች ........ 15
14. የግል ንግድ የተሽከርካሪ ምዝገባ ........ 15
15. በእርዳታ እና በበጎ አድራጎት ለተሰማሩ ድርጅቶች የተሽከርካሪ ምዝገባ ........ 16
16. ለዕጣ ባለዕድሎች የተሽከርካሪ ምዝገባ ........ 16
17. የኮር ዲፕሎማት ሠሌዳ ምዝገባ ........ 16




ስማሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority

18. ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነጻ ሲገባ የሚካሄድ ምዝገባ ........................................ 16
19. የተሽከርካሪ ኦርጅናል ዲክላራሲዮን እና የሲስተም ማረጋገጫ/VVD/ ...................... 17
20. አስመጪ ድርጅት ተሽከርካሪ አስመጥቶ በራሱ በድርጅቱ ስም ለማስመዝገብ...... 17
21. ጅምላ ገዥ ተሽከርካሪ በችርቻሮ ለተጠቃሚዎች በሚሸጥበት ጊዜ ........................ 17
22. የምርት ዘመን የሌላቸው ተሽከርካሪ ምዝገባ............................................. 17
23. የኢ.ት ሠሌዳ አገልግሎት አሰጣጥ.......................................................18
24. ለአምቡላንስ እና ለቱሪስት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች...... 18
25. ማሽነሪ የሚገጠምላቸዉ ተሽከርካሪዎች ምዝገባ .......................................19
26. ተሽከርካሪዎች ለምዝገባ ሲቀርብ የሶስተኛወገን መድን ዋስትና ስለማስፈለጉ...... 19
27. ለኮድ- 02 (ለግል መገልገያ) ተሽከርካሪ ምዝገባ ......................................... 19
28. ድርብ ተግባር /ደብል ካፕ ተሽከርካሪዎች አመዘጋገብ................................. 20
29. ኪን ካፕ ተሽከርካሪ አመዘጋገብ..........................................................20
30. ልዩ ጎታችና ተሳቢ ተሽከርካሪ ምዝገባ.................................................20
31. የሻንሲና የሞተር ቁጥር/Chassis and Engine No/ ማረጋገጥ ...................... 21
32. የተሽከርካሪ ሞድፊክ /Value Add/ ስራ ..................................................23
33. በተለያዩ ምክንያት መረጃ ሳያሚላ ተመዝግቦ የተገኘ ተሽከርካሪ ........................ 23
34. የባለቤትነት ስም ምዝገባ ክፍያ/የቴምብር ቀረጥ2%/ የማይመለከታቸው................24
35. ከቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲመዘገቡ ስለተፈቀደላቸው ተሽከርካሪዎች ....................... 24
36. በጋራ ባለንብረት ላይ የቴምብር ቀረጥ፡-................................................ 24
37. የተሽከርካሪ አካል ስፋት እና ርዝመት ስታንዳርድ.......................................25
38. የተሽከርካሪው ክብደት፡.......................................................................... 25
39. በአንድ ደረሰኝ የተሸጡ ብዛት ያላቸዉ ተሽከርካሪዎች ....................................27
40. ኢንቮይስ ሲጠፋ...............................................................................27
41. የመረጃ ግልባጭ አሰጣጥ ......................................................................27
42. የኦርጅናል ደረሰኝ /invoice አጠቃቀም......................................................27
43. ልዩ ልዩ የእርማት አገልግሎቶች ...........................................................28

ክፍል ሶስት

የተሽከርከሪ አገልግሎት አሰጣጥና የሚያስፈልጉ ሰነዶች ..........................................29

44. የተሽከርካሪ ወቅታዊ የዋጋ ግምት አሰጣጥ ........................................ 29

45. በሽያጭ የተሽከርካሪ ስም ዝውውር ........................................ 29

46. በጨረታ የሚሸጡ ተሽከርካሪ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ ሰነዶች ........................................ 30

47. የመንግስት ድርጅት በሚዋሃዱበት፣ በሚለያዩበትና እንዲፈርሱ በሚደረግበት ጊዜ .31

48. የሰነድ ጉድለት ያለበት እና የጠፋ ፋይል ያለው የተሽከርካሪ ስም ዝውውር ምዝገባ ........................................ 31

49. የሰነድ ጉድለት ያለበት የመንግስት ተሽከርካሪ በጨረታ ተሽጦ ለምዝገባ ሲቀርብ 32

50. አደጋ የደረሰበት የኢንሹራንስ ተሽከርካሪ ስም ዝውውር ምዝገባ........................................ 32

51. የጠፋ ሠሌዳ ወይም ሊብሬ ምትክ አሰጣጥ ........................................ 33

52. የሊብሬ ግልባጭ አሰጣጥ፡ ........................................ 34

53. ቦሎ ሲጠፋ ወይም ሲበላሽ ምትክ/ግልባጭ/ አሰጣጥ ........................................ 34

54. የተበላሸ ወይም የዕድሳት ቦታ ላለቀ ሊብሬ እና ለተበላሸ ሰሌዳ ምትክ ስለመስጠት 34

55. የብዙ ባለንብረትነት መብትና የሊብሬ ለውጥ፡ ........................................ 35

56. ለቀድሞ ሠሌዳ ለዉጥ መስጠት ........................................ 35

57. የውጭ ሀገር መንግስት ኢምባሲዎች፣ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችና የቆንስላ ጽ/ቤቶች ተሽከርካሪ ሰሌዳ አመላለስ ........................................ 35

58. የተሽከርካሪ ምዝገባ ስረዛ ........................................ 36

59. የተሽከርካሪ ምዝገባ ጊዜያዊ ስረዛ እና ሰሌዳና ሊብሬ በአደራ ሲቀመጥ ........................................ 36

60. ከክልል ወደ ክልል የሚዘዋወር የተሽከርካሪ ፋይል ........................................ 37

ክፍል አራት

የተሽከርካሪ የአካልና የአገልግሎት ለውጥ ስታንዳርድና ምዝገባ ........................................ 39

61. ከደረቅ ጭነት ወደ ሕዝብ ማመላለሻነት በሞዲፊክ የሚለወጥ የተሽከርካሪ የጭነት ልክ አወሳሰን ........................................ 39

62. ከደረቅ ጭነት ወደ ሕዝብ ማመላለሻነት የሚለወጥ ተሽከርካሪ በቅድመ ምርመራ ወቅት የሚታዩ መስፈርቶች ........................................ 39

63. የተሽከርካሪው የወንበር ስፔስፊኬሽንና መስፈርት ........................................ 40

Federal Democratic Republic of
Ministry of Transport Authority

64. በአካል ለውጥ ጊዜ የጭነት /የተሳፋሪብዛት /አወሳሰን ........................................ 40

65. በሞደፊክ የሚሠሩ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የጭነት አወሳሰን ................ 40

66. ወደ ህዝብ ማመላለሻነት ሊቀየሩ የሚችሉ የተሽከርካሪ ሞዴሎች ......................... 41

67. ወደ ህዝብ ማመላለሻነት ሊቀየሩ የማይችሉ የተሽከርካሪ ሞዴሎች ...................... 42

68. የአካልናየአገልግሎት ለውጥ ምዝገባ የሚያደርጉ ተሽከርካሪዎች የዕድሜ ገደብ ...... 43

69. በአካል ለውጥ አሰራር ሂደት ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች እና መረጃዎች ...... 43

70. የአካልለውጥ ያደረገ ተሽከርካሪ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ሰነዶች ...... 44

71. ከተቋም ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው ለውጥ የሚያደርጉ አገልግሎቶች .......................... 44

72. የተሽከርካሪ የሞተር ለውጥ ፈቃድ ስለመስጠት ..................................................... 47

73. የተሽከርካሪ የሞተር ለውጥ በሚደረግበት ወቅት በቴክኒክ መረጋገጥ ያለባቸው መስፈርቶች ........................................................................................................ 47

74. ለሞተር ለውጥ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና ፈቃድ አሰጣጥ ........... 48

75. የተሽከርካሪ የሻንሲ ለውጥ ፈቃድ ........................................................................ 50

76. የተሽከርካሪ ሻንሲ እና ሞተር ቁጥር ስለ ማስመታት ............................................. 50

77. የሻንሲና የሞተር ቁጥር ማስመቻ ፈቃድ ................................................................. 52

78. የተሽከርካሪ ሻንሲ ለውጥ እና የሻንሲ ጥገና ፈቃድ .............................................. 53

ክፍል አምስት

የተሽከርካሪ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ /ቦሎ/ .......................................................... 55

79. የዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ አስፈላጊነት፡ ............................................................ 55

80. ተሽከርካሪው ቦሎ ለመውሰድ የማያስችሉ ሁኔታዎች ............................................ 55

81. የቦሎአሰጣጥ በተሽከርካሪ የአገልግሎት አይነት .................................................. 55

82. ለዓመታዊ የተሽከርካሪ ምዝገባ /ቦሎ/ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ሠነዶች ............... 56

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........................................................................................... 57

83. የስም ዝውውር ወይም የባለቤትነት መብት የሚተላለፍባቸው ህጋዊ መንገዶች ....... 57

84. በሽያጭ ስም የሚዞርበት ሁኔታ ........ 57
85. በስጦታ ስም የሚዞርበት ሁኔታ ........ 58
86. ተሽከርካሪ በመለዋወጥ ስም የሚዞርበት ሁኔታ ........ 58
87. በውርስ ወይም በኑዛዜ ስም የሚዞርበት ሁኔታ ........ 58
88. ወራሽነት ያለኑዛዜ ........ 59
89. ወራሽነት በኑዛዜ ........ 59
90. በፍርድ ቤት ውሳኔ ያለ ሀራጅ የተሽከርካሪ ስም ዝውውር ........ 59
91. በፍርድ ቤት ውሳኔ በፍርድ አፈጻጸም አማካኝነት አንድ ተሽከርካሪ በሀራጅ ሲሸጥ 59
92. ባንክ በዋስትና የያዘውን ተሽከርካሪ በህግ ሲሸጥ ........ 60
93. እገዳ ማገድ ........ 60
94. የፍርድ ቤት ዕግድ ........ 61
95. ባንኮችና የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት/ድርጅቶች፦ ........ 62
96. የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዕግድ፦ ........ 62
97. እግድ ማንሳትን ........ 62
98. የባለንብረትነት መብትና የሊብሬ ለውጥ፡ ........ 63
99. የውርስ ድርሻ መልቀቅን በተመለከተ ........ 64
100. ሻጭ በተወካይ መኪናውን ሸጦ ስም ሳያዞር የመኪናው ባለቤት (ሻጩ ወይም ወካዩ) ቢሞት ........ 64
101. የተሽከርካሪ የሽያጭ ሂደት ከተጀመረ በኋላ ሻጭ ሲጠፋ ........ 64
102. ገዥው በውልና ማስረጃ አጸድቆ ሊብሬና ተሽከርካሪውን ገዥ ከተረከበ በኋላ ሻጭ ቅሬታ ካቀረበ ........ 65
103. ውል ማፍረስ ........ 65
104. ባል ወይም ሚስት በስጦታ፣ በውርስ ወይም በሌሎች ሁኔታዎች በግላቸው ያገኙትን ተሽከርካሪ የጋራ ንብረት ስለማድረግ........ 66
105. የባልና ሚስት የስም ዝውውር /ድርሻ መልቀቅ/ ጉዳይ........ 66
106. የባልና ሚስት የተሽከርካሪ ባለንብረትነት መብት........ 66
107. በፕራይቬታይዜሽን ድርጅት ለሚሸጡ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት አሰጣጥ ........ 67
108. የጉምሩክ ዕዳዎችን በሚመለከት ........ 67
109. የመተባበር ግዴታ ........ 68

110. የተሻሩ መመሪያዎች ........................................................68
111. መመሪያውን የማሻሻል ........................................................68
112. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ ........................................................68
አባሪ ........................................................69
አባሪ 1. አዲስ/ያላገለገሉ/ ተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ ሂደት ........................................................69
አባሪ 2. የኢምባሲዎች፣ የዓለም አቀፍና የዕርዳታ ድርጅቶች የሰሌዳ አይነቶችና የቀለም ቅብ........................................................71
አባሪ 3. የተሽከርካሪ ጠቅላላ ስታንዳርድ ........................................................72
አባሪ 4. የጭነት ተሽከርካሪ ስታንዳርድ........................................................73
አባሪ 5. የህዝብ ተሽከርካሪ አካል ለውጥ የጭነት መወሰኛና ሞዴል........................................................74
አባሪ 6. ወደ ህዝብ ተሽከርካሪ የሚለወጡ ሞዴሎች........................................................75
አባሪ 7. ወደ ሕዝብ ማመላለሻነት ሊቀየሩ የማይችሉ ሞዴሎች........................................................ 77/77

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

## መግቢያ

በሀገራችን ካሉት  የትራንስፖርት አገልግሎት ውስጥ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚከናወነው በመንገድ ትራንስፓርት ዘርፍ በመሆኑ በአግባቡና ወጥ በሆነ መንገድ የተሸከርካሪዎች ምዝገባና የቴክኒክ ምርመራ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት የሚያስይዝ መመሪያ በማውጣት ተሽከርካሪዎች ቀልጣፋና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ ያለ ሕይወት መጥፋትና የንብረት ውድመት ተቆጣጥሮ ለመጠቀም እንዲቻል በአግባቡ ተመዝግበውና የቴክኒክ አቋማቸው ተረጋግጦ ለተገቢው አገልግሎት ማዋል ያስችላል፡፡

በመሆኑም ከውጭ ሀገር ወደ ሀገሪቷ የሚገቡ ተሽከርካሪዎችም ሆኑ በሀገር ውስጥ የሚገጣጠሙና በከፊል የሚመረቱ ማንኛውም ተሽከርካሪዎች የሀገሪቱን መስፈርት በጠበቀ መልኩ ተመዝግበው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል፡፡

ለዚህም አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመርያዎችና የስራ ማንዋሎች ላሰራሩ መዘመን የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፈጻሚዎቹ የመፈጸም አቅም ጎን ለጎን ድርሻው ጉልህ ነው፣ ይሁን እንጂ እስካሁን በስራ ላይ ያሉ መመሪያዎችና ደንቦች፣ አዋጆች በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ ካለው አሰራር ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ ባለመከለሳቸው ባሰራሩ ላይ ከፍተኛ ወጥነት የጎደለው አሰራር እንዲታይ አድርጓል፡፡በመሆኑም ተገልጋዩ ህብረተሰብ የሚፈልገውን ቀልጣፋና ጥራት ያለው  አገልግሎት ለመስጠት መመሪያ (ክለሳ) በማድረግ እስካሁን በስራ ላይ ያሉትን እና ተበታትነው ላሰራር እያስቸገሩ ያሉትን መመሪያዎች እና ማንዋሎች ላሰራር በሚያመች መልኩ ወጥነት ወዳ አለው ሰነድ በማጠናቀር ማዘጋጀት እና ለፈጻሚ በሚያመች መልኩ አገልግሎቱን የሰለጠነ እና ከቅሬታ ነጻ የሆነ ለማድረግ ትራንስፖርት ለመቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2(ቀ) መሰረት ይህ መመሪያ የወጣ ሲሆን መመሪያ ቁጥር 2/2004 የአካል ለውጥ መመሪያ በሚመለከት በዚህ መመሪያ ውስጥ ተካተዋል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የተሽከርካሪዎች አመዘጋገብና የቴክኒክ ምርመራ የአሰራር መመሪያ ቁጥር **671/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡

1. **ባለስልጣን ማለት፡** በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በአዋጅ ቁጥር 468/1997 የተቋቋመ የትራንስፖርት ባለስልጣን መ/ቤት ነው
2. **የክልል ትራንስፖርት ቢሮ፡-**ማለት ትራንስፖርትን ለመምራት፣ ተሽከርካሪን ለመመዝገብ እና የአሽከርካሪን ብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት የተቋቋመ የክልል ወይም የከተማ መስተዳድር የመንግስት ተቋም ነው፡፡
3. **አስመጪ ማለት፡-** ማለት ከትራንስፓርት ባለሥልጣን መ/ቤት አዲስ ወይም ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ሕጋዊ የአስመጪነት ፈቃድ ያላቸው ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ማለት ነው፡፡
4. **የተሽከርካሪ አስመጪ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት፡-** ማለት የትራንስፓርት ባለሥልጣን መ/ቤት ለተሽከርካሪ አስመጪ ድርጅቶች ያወጣውን መስፈርት አሟልተው ለተገኙ የአስመጭነት ብቃት ማረጋገጫ ነው፡፡
5. **የተሽከርካሪ ማስገቢያ ፈቃድ፡-** ማለት በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚገቡን ማንኛዉም አይነት /ሞዴል/ ተሽከርካሪ የሀገሪቱን የተሽከርካሪ ስታንዳርድ ወይም መስፈርት እያሟሉ እንዲገቡና የማያሟሉት እንዳይገቡ ለማድረግ በትራንስፖርት ባለስልጣን የሚሰጥ ፈቃድ ነዉ፡፡
6. **የተሽከርካሪ ማስጫኛ ሰነድ /Bill of Loading/ ማለት፡-**ተሽከርካሪው ከተመረተበት አገር ወይም ከተገዛበት አገር ወደ ሀገር ውስጥ እስኪገባ ድረስ የተጓጓዘበት የመጫኛ ሰነድ /በመርከብ፣ በአውሮፕላን፣ በባቡር፣በተሽከርካሪ ተጭኖ ወይም እየተነዳ የመጣበት ሰነድ ነው፡፡
7. **አዲስ ተሽከርካሪ ምዝገባ ማለት፡-**ከዚህ በፊት በፌዴራል ወይም በክልል ትራንስፓርት ቢሮ ምዝገባ ያልተደረገላቸው አዲስም ሆነ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎችን አዲስ ምዝገባ የተደረገለት ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡

8. **ቋሚ መለያ ሰሌዳ፡-** ማለት አንድ ተሽከርካሪ የሚያስፈልጉት ህጋዊ ሰነዶች ተሟልተውና ተገቢው ምርመራና ምዝገባ ከተደረገለት በኋላ ከተሽከርካሪው ከፊትና ከኋላ የሚለጠፍ በስራ /አገልግሎት/ ዓይነት ተለይቶ የሚሰጥ ቋሚ የሰሌዳ ቁጥር ነው፡፡
9. **የርቀት የኮምፒውተር ግንኙነት** /WAN/፡-ማለት የሚሰጠውን ዓመታዊ የተሽከርካሪ ቴክኒክ ምርመራ አገልግሎት አፈፃፀም ከየርቀቱ ባሉ ኮምፒውተሮች ለመናበብና መረጃ ለመለዋወጥ እንዲያስችል በስልክ መስመር ወይም በሌላ መንገድ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡
10. **የቀጥታ መስመር** /0nline connection/**ግንኙነት**፡-ማለት የመረጃ ምንጩ መረጃዎችን ከመዘገበ በኋላ ወደ ማዕከላዊ ዳታ ባንክ በቀጥታ ለማስተላለፍ የሚጠቀምበት ወይንም የመረጃ ምንጩ የሚፈለገውን መረጃ ከማዕከላዊ ዳታ ባንክ ለማግኘት የሚያስችል በመረጃ ምንጩና በማዕከል ኮምፒውተሮች ሁልጊዜም የሚኖር ክፍት የስልክ ግንኙነት መስመር ማለት ነው፡፡
11. **ቴክኒሽያን**፡-ማለት ተሽከርካሪን ለመመርመር የሙያ ብቃት ያለው እና ለብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት የሚመጡና አገልግሎት የሚወስዱ ተሽከርካሪዎችን በየደረጃው በእይታና በዘመናዊ መሳሪያ የቴክኒክ ብቃታቸውን በማረጋገጥ፣ የምርመራ ሰርትፍኬት የሚሰጥ ባለሙያ የሆነ ሰው ነው፡፡
12. **የሙያ ብቃት፡-** ማለት የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ ሥራ በብቃት ለመወጣት የሚያስችል በመደበኛ የትምህርት ሂደት በሥልጠና ጭምር የተደገፈና በት/ባለስልጣን በተቀመጠው አነስተኛ ተፈላጊ /Minimum Requirement/ ሙያ /ክህሎት/ መሠረት የሚሰጥ ሙያዊ የስራ ብቃት ማረጋገጫ ሰርትፍኬት ማለት ነው፡፡
13. **ውል ሠጪ፡-** ማለት በትራንስፖርት መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 468/97 አንቀጽ 243 አ1 እና በክልል መስተዳድር አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ 45/85 ለትራንስፓርት አካላቱ የተሰጠውን ተግባርና ሀላፊነት ለሌላ ወገን ውክልና የሚሰጥ ማለት ነው፡፡
14. **ተሳቢ**፡-ማለት ለመንገደኞች ወይም ለጭነት ማመላለሻ የሚያገለግል በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚሳብ ሆኖ ተሽከርካሪውም የጭነቱ ክብደት በከፊል በሌላ ተሽከርካሪ ላይ እንዲያርፍ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ እንዲሳብ ተደርጎ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፡፡
15. **ግማሽተሳቢ**፡-ማለት ለራሱ የተለየ የሞተር ኃይል የሌለው ሆኖ ጎታች በሆነ በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ ላይ ሊቀጠልና ሊጎተት የሚችል ተሽከርካሪ ነው፡፡
16. **ቀላል ተሽከርካሪ፡-** ማለት የግል አውቶሞቢል፣ ሞተር ሳይክል፣ትራይ ሳይክል ጠቅላላ ክብደቱ እስከ 3500 ኪ.ግ የሚደርስ ተሽከርካሪ ነው፡፡
17. **መካከለኛ ተሽከርካሪ፡-** ማለት ጠቅላላ ክብደታቸው ከ3500 ኪ.ግ እስከ 7500 ኪ.ግ ያሉትን ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፡፡

18. **ከባድ ተሽከርካሪ፡-** ማለት ባለሞተር ተሳቢ፣ ከባድ ካሚዮን፣ ግማሽ ተሳቢ፣የእርሻ መሳሪያዎች ሆኖ ጠቅላላ ክብደታቸው ከ7500 ኪ.ግ በላይ የሚመዝኑ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፡፡
19. **ሞተር ብስክሌት፡-**ማለት በሞተር ኀይል የሚንቀሳቀስ ያለው ባለሁለት እግር /wheel/ ሆኖ ሰው ብቻ ለማጓጓዝ የሚያገለግል ነው፡፡
20. **ትራይ ሳይክል/ባጃጅ/፡-** ማለት በሞተር ኀይል የሚንቀሳቀስ ና ባለሶስት እግር /wheel/ ሆኖ ሰው ወይም ዕቃን ለማጓጓዝ የሚያገለግል ነው፡፡
21. **ልዩ ተንቀሳቃሽ፡-** ማለት ሰው ወይም ዕቃን በመንገድ ላይ እንዲያመላልስ ሆኖ የተሰራ ተሽከርካሪ ሳይሆን ለእርሻ፣ ለአትክልት፣ ለከብት፣ ለመንገድ፣ ለህንፃ፣ለቁፋሮ ወይም ለማንኛውም ተመሳሳይ ስራ የተሰራ ወይም ለዚህ ጉዳይ እንዲውል የተደረገ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፡፡
22. **ሥም ማዛወር፡-** ማለት በሽያጭ ፣ በስጦታ ፣ በውርስና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በመሣሠሉት ምክንያቶች በተሽከርካሪው ላይ የሚከናወን የባለቤትነት ይዞታ ለውጥን የሚያጠቃልል ነው፡
23. **የምዝገባ/ አገልግሎት ለውጥ፡-** ማለት ተሽከርካሪዉ ከሚሰጠው አገልግሎት ወደ ሌላ አገልግሎት ዘርፍ ሲቀየርና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሠሌዳ ኮድ በመለወጥ የሚከናወን ነው፡፡
24. **የምዝገባ ስረዛ፡-** ማለት አንድ ተሽከርካሪ ተመዝግቦ ሲሰራበት ከነበረው አገልግሎት በእርጅና፣ በአደጋ፣ በመለዋወጫ /Spare Parts/ ዕጥረት ተሽከርካሪው ከአገልግሎት ውጪ በመሆኑ ሠሌዳና ሊብሬ ሲመልስ የሚከናወን ስረዛ ማለት ነው፡፡
25. **ነጠላ የተሽከርካሪ ክብደት፡-** ማለት ተሽከርካሪው ሹፌሩን ፣ የግሪስ ማጠጫ ፣ ሽራ ፣ ተለዋጭ(ቅያሪ) ጎማ ፣ እና ¾ኛ የነዳጅ ታንክ ሙሉ በሆነበት እነዚህን ይዞ ተለክቶ ያለዉ ክብደት ነዉ፡፡
26. **ጠቅላላ የተሽከርካሪ ክብደት፡-** ማለት ተሽከርካሪው ጭኖ ሊኖረው የሚችለው የክብደት መጠን /ውጤት/ ነው፡፡
27. **የጭነት ልክ፡-** ማለት ከጠቅላላ ክብደት ላይ ነጠላ ክብደት ተቀንሶ የሚገኘው የጭነት ልክ ነው፡፡
28. **የታክሲ ተሽከርካሪ፡-** ማለት ሰዎችን ከቦታ ወደ ቦታ የሚያመላልስ የከተማ ውስጥ የንግድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ ላይ የተሰማራ ባለሞተር ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡
29. **የቤት ተሽከርካሪ፡-** ማለት ለቤት ወይም ለቤተሰብ አገልግሎት እንዲውል የተመዘገበ ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡
30. **የንግድ የመንገደኞች /የተጓዦች ማመላለሻ ተሽከርካሪ፡-** ማለት በግለሰብ ወይም በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል በሚመራ ድርጅት መንገደኞችን ወይም እቃዎችን ለኪራይ፣ለጥቅም ወይም ለትርፍ የማመላለስ ሥራ የሚያከናውን ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡

31. **የግል ንግድ የመንገድ ላይ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፡-** ማለት መንገደኞችን ወይም እቃዎችን የሚያመላልሰው ተሽከርካሪ ንብረትነቱ የድርጅቱ ሆኖ፣

ሀ. የሚመላለሱት እቃዎች የዚያው የድርጅት ንብረት የሆኑ ወይም ለጥገና ወይም ለማሳደስ በአደራ የተሰጡ የሆኑ እንደሆኑና እቃዎቹን ለማመላለስ ለድርጅቱ ዓይነተኛ የንግድ ሥራ አስፈላጊና ማሟያ የሆነ እንደሆነ ወይም

ለ. የሚመላለሱት መንገደኞች የዚያው ድርጅት ሠራተኞች ሆነው የሚመላለሱትም ወደ ሥራ ቦታቸውና ከሥራ ቦታቸው ወደ ቤታቸው የሆነ ወይም የድርጅቱን ሥራ ማከናወን የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

32. **የመንግሥት ተሽከርካሪ፡-** ማለት የፌዴራል ወይም የክልል መንግስት መስሪያ ቤት ንብረት የሆነ ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡

33. **የመከላከያ ኃይል ተሽከርካሪ፡-** ማለት የአገር መከላከያ ሚኒስቴር ንብረት ሆኖ ሰሌዳና ምዝገባ የሚያካሂደውም በሚ/ር መ/ቤቱ የሆነ እንዲሁም ለወታደራዊ ተግባር ብቻ እንዲውል የተመደበ ማንኛውም ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡

34. **የሃይማኖት ድርጅትና የማሕበር ተሽከርካሪ፡-** ማለት የሃይማኖት ድርጅት፣የቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ እና ነጋዴ ላልሆኑ ማህበራት እና ለመሳሰሉት ተቋማት አገልግሎት እንዲውሉ የተመዘገቡ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፡፡

35. **ኤምባሲ፣ የዓለም አቀፍና የዕርዳታ ሰጪ ድርጅት ተሽከርካሪ፡-** ማለት በኢትዮጵያ መንግሥት እውቅና ያገኘ ንብረትነቱ የእነዚህ መስሪያ ቤቶች የሆነ ወይም በተባበሩት መንግስታት መስሪያ ቤት ውስጥ የዲኘሎማቲክ መብት ላለው ባለሥልጣን ወይም ለመስሪያ ቤቱ አባል ለሆነ ሰው የሚሰጥ ተሽከርካሪ ማለት ነው፡

36. **ቴክኒክ ምርመራ መሳሪያዎች፡-**ማለት ብቃታቸው በዕይታ ብቻ ሊታወቁ የማይችሉ የተሽከርካሪ አካላትንና ልዩልዩ ክፍሎች ያሉበትን የቴክኒክ አቋምና ብቃት ለማወቅ የሚያገለግሉ ዘመናዊ የምርመራ መሳሪያዎች ሲሆኑ፣ የፍሬን፣ የጭስ፣የግንባር መብራት አቅጣጫና ሀይል፣ የአረግራጊ ክፍሎችና የሳይድ ስሊፕ መመርመሪያ መሳሪያዎች ማለት ነው፡፡

37. **ምዝገባ ዕድሳ/ከላውዶ/ ፡-** ማለት አንድ ተሽከርካሪ በተመዘገበበት አገልግሎት አይነት የቴክኒክ ብቃቱ ተመርምሮ ለአገልግሎቱ የቴክኒክ ብቃቱ ብቁ ሆኖ ሲገኝና የተረጋገጠ ተገቢውን የመንግስት ግብር ሲከፍል የወቅቱን ምዝገባ ማደስ ማለት ነው፡፡

38. **የምርመራ ሰርተፊኬት፡** ማለት ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ አድርጎ የቴክኒክ ብቃቱን ላሟላ ተሽከርካሪ የሚሰጥ የምርመራ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ነው፡፡

39. **የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ፡-** ማለት የተሽከርካሪ ምርመራ ተሽከርካሪው አደጋን በማያስከትል ሁኔታ በመንገድ ላይ መሽከርከር ስለመቻሉ በእይታና በመሳሪያ በቴክኒሽያን መርማሪዎች የሚካሄድ ምርመራ ማለት ነው፡፡
40. **ዓመታዊ የምርመራ ተለጣፊ ምልክት /ቦሎ/፡-** ማለት አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ የቴክኒክ ብቃትና ምቾት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚሰጥና ለአንድ አመት የሚፀና ተለጣፊ ምልክት ነው፡፡
41. **የተሽከርካሪ ምርመራ፡-** ማለት አንድ ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ የቴክኒክ ብቃትና ምቾት ያለው መሆኑንና መንቀሳቀስ የመቻል ብቃቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ የቴክኒክ ምርመራ ነው፡፡
42. **ትውልደ ኢትዮጵያዊ ማለት፡** የሌላ ሀገር ዜግነት ከመያዙ አስቀድሞ የኢትዮጵያ ዜግነት የነበረው ወይም ከወላጆቹ፣ ከአያቶቹ ወይም ከቅድመ አያቶቹ ቢንያስ አንዱ በማናቸውም ጊዜ የኢትዮጵያዊ ዜግነት ይዞ የነበረ የውጭ ዜጋ ነው፡
43. **ሰነድ ማለት፡** ማናቸውም መብት ወይም ግዴታ የተመሰረተበት፣ የተመዘገበበት፣ የተላለፈበት፣ የተወገደበት፣ ልኩ የተወሰነበት፣ ወይም የተስፋፋበት ወይም የተጠቀሰው ድርጊት ተፈጽሟል የተባለበት ዋናው የጽሁፍ መረጃ ነው፡፡
44. **ዲክሌሬሽን ማለት፡-**ከውጪ አገር ወደ አገር ውስጥ የገቡ ተሽከርካሪዎች የአስመጪው ስም፣ የተሽከርካሪው ሞዴል፣የሞተርና የሻንሲ ቁጥሮች በሰነዱ ላይ ተሞልተው አስፈላጊው ቀረጥ ተከፍሎ ወይም ከቀረጥ ነፃ ከሆነ ተረጋግጦ የሚሰጥ የጉምሩክ ባለስልጣን ሰነድ ነው፡፡
45. **ዜሮ ዲክላራሲዮን ማለት** ወደ ሀገር ውስጥ ከቀረጥ ነጻ የገባ ተሽከርካሪ የቀረጥ ክፍያውን ለ10 ዓመታት በተፈቀደለት ዘርፍ በአገልግሎት እንዲከፍልና አገልግሎቱን ከፈጸመ በኋላ የቀረጥ አግባቡን ለመክፈሉ ቀረጥ ነጻ የሚለው ተነስቶ የሚሰጥ የተሽከርካሪ ዲክላራሲዮን ማለት
46. **ቀረጥ ማለት፡** በትክክል ለእቃው በተደረገ ጠቅላላ ወጭ ላይ ተመስርቶ እና የዓለም አቀፍ የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየምና አመዳደብ ሥርዓትን ተከትሎ በወጣው የጉምሩክ የታሪፍ ደንብ መሰረት በገቢና ወጪ እቃዎች ላይ የሚጣልና የሚሰበሰብ ታሪፍ ነው፡፡
47. **ታክስ ማለት፡** ፀንተው በስራ ላይ ባሉ የግብር ህጎች መሰረት በገቢና በወጭ እቃዎች ላይ እየተጣለ የሚሰበሰብ ክፍያ ነው፡፡
48. **የቴምብር ቀረጥ ማለት፡** በአዋጅ ቁጥር 110/1990 መሰረት ማንኛውም ሰው ንብረት በስሙ ሲያስመዘግብ በስሙ በሚያስመዘግበው የንብረት መጠን ተሰልቶ የንብረቱን መጠን 2% ለመንግስት እንዲከፍል ማድረግ ማለት ነው

49. **የተሸከርካሪ የማስገቢያ ፈቃድ ማለት፡** ከውጪ አገር ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ተሽከርካሪዎች ከትራንስፖርት ባለሥልጣን የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

50. **ቀረጥ ነጻ ማለት** በጉምሩክ የታሪፍ ደንብ መሰረት በገቢና ወጪ እቃዎች ላይ ከሚጣልና ከሚሰበሰብ ቀረጥና ታክስ ነጻ መሆን ማለት ነው፡፡

51. **የተሸከርካሪ ስፔስፊኬሽን ማለት** የተሸከርካሪውን የስሪት ይዘት የሚገልጹ የተሸከርካሪ መሰረታዊ ክፍሎች ሲሆኑ የተሸከርካሪውን ዓይነት፣ የሞዴል ዓይነት፣ የሰራውን ፋብሪካ፣ የስሪት ዘመን፣ የጉልበት መጠን፣ የጭነት ልክ፣ የአክስል ብዛት፣ ወዘት የሚገልጽ መስፈርት ነው ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ ሃገር ውስጥ የሚገጣጠሙ ተሽከርካሪዎች ሃገሪቱ ያወጣችውን የተሸከርካሪ የስሪት ይዘት የመለኪያ ነጥቦች/ስፔስፊኬሽን/ ማለት ነው

52.**ሊብሬ ማለት** የተሸከርካሪ መሰረታዊ ክፍሎች እና የባለንብረቱ ስም የተጻፉበት ተሽከርካሪው በህጋዊ መልኩ ምዝገባ ለማድረጉ እና ለባለንብረቱ የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ በትራንስፖርት ቅ/ጽ/ቤት የሚሰጥ ደብተር ነው፡፡

53.**አዲስ ተሽከርካሪ ማለት፡-** ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በሌላ ሀገር ተመዝግቦ አገልግሎት ያልሰጠ ሆኖ ሁለት ዓመት ያልበለጠው ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡

54.**ያገለገለ ተሽከርካሪ ማለት፡-** ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባቱ በፊት በሌላ ሀገር ተመዝግቦ አገልግሎት ሰጥቶ ወደ ሃገር የገባ ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡

55.**ድርብ ተግባር ያለው ተሽከርካሪ ማለት፡-**ከሾፌሩ ውጭ ከሁለት በላይ ሰዎችን የሚጭን እና የጭነት አገልግሎት ጭምር ደርቦ አገልግሎት የሚሰጥ ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡

56.**የተሽከርካሪ መሰረታዊ ሰነዶች ማለት፡-**የተሽከርካሪውን ምንነት በመሰረታዊነት ሊገልጹ የሚችሉ የጉምሩክ ኦርጂናል ዲክላራሲዮን፣ ኢንቮይስ፣ ቀረጥ የተከፈለበት ደረሰኝ /ሪሙቫል/ የተሽከርካሪ የብቃት ስታንዳርድ መግለጫ ቅጽ(ሮዝ ወረቀት) ማለት ነው፡፡

### 3. የተፈጻሚነት ወሰን

በዚህ መመሪያ መሰረት አገልግሎት ለሚጠይቁና አገልግሎት በሚሰጡት አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የተለያዩ ተቋማት መስፈርትና የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራና ምዝገባ

4. የተሽከርካሪ አስመጪዎች ሊያሟሏቸዉ የሚገቡ መስፈርቶች

ሀ. አዲስ እና ያገለገሉ ተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስመጡ አሰመጪዎች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው

1. አዲስ ተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስመጡ አሰመጪዎች ብቻ ከአምራች ኩባንያው የኤጀንትነት ፈቃድ /Letter of Authorization/ መኖር፣
2. አዲስ ተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስመጡ ብቻ አሰመጪዎች ከአምራች ኩባንያው ቻምበራይዝድ /Chamberized/ የሆነ ማረጋገጫ ሰነድ መኖር
3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገኘው መረጃ ከኢትዮጲያ ውጭ ከሆነ በኢትዮጵያ መንግሥት ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አዉቶንቲኬሽን ያገኘ ሠነድ፣
4. አዲስ ተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስመጡ አሰመጪዎች ብቻ ተሽከርካሪው ከተመረተ ከ 2 ዓመት ያልበለጠ መሆን፣
5. አስመጭው አቀርባለሁ የሚለው ተሽከርካሪ ከሀገሪቱ የአየር ፀባይና የመልክዓ ምድር አቀማመጥ እንዲሁም ከብክነት የጸዳ /enviromental pollution free/ መሆን፣
6. ለሚያቀርበው ተሽከርካሪ በቂና አስተማማኝ የመለዋወጫ ዕቃ ለማቅረቡ ግዴታ መግባት፣
7. ባለስልጣኑ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት የወርክሾፕ /Work Shop/ ፋሲሊቲና የሰው ሀይል በበቂ ሁኔታ ላይ መሆን፣
8. ባለስልጣኑ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት በቂ የተሽከርካሪ ማቆሚያና የሥራ ቦታ ስለመኖሩ ማረጋገጫ ማቅረብ፣
9. Original Brouchers and Technical Specification በእንግሊዘኛ የተፃፈ እና
10. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ ከ1-9 የተጠቀሱትን ሲያሟሉ የተሽከርካሪ አስመጭነት ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ከትራንስፖርት ባለሥልጣን ይሰጣቸዋል፡፡

ለ. ተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚያስመጡ አሰመጪዎች የሚጠበቁ ተጨማሪ ግዴታዎች

1. የተሽከርካሪ አስመጭነት ብቃት ማረጋገጫ ሰርትፍኬትና የማስገቢያ ፈቃድ ከትራንስፖርት ባለሥልጣን እና የንግድ ፈቃድ ከፈቃድ ሰጪ አካል ማቅረብ፣
2. አዲስና ያገለገለ ተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ የሚስገቡ የትራንስፖርት ባለሥልጣን ባወጣው ስፔስፊኬሽን መሠረት ሁሉንም ስታንዳርድ መሟላት፣

3. አስመጪዎች ለሚያስመጡት ተሽከርካሪ በሽያጭ ጊዜም ሆነ ከሽያጭ በኋላ ተገቢዉ ሰነድ አሟልተዉ ለተገልጋዩ መስጠት፣
4. አዲስ ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸዉ ተሽከርካሪዎች ሲያስገቡ ለሚያስገቧቸዉ ተሽከርካሪዎች ለተገልጋይ ሆነ ለሚመለከተው የአጠቃቀም ጥንቃቄ/ሴፍቲን/ በስፋት ማሳወቅ ፤
5. አቅምን ባገናዘበ መልኩ የአዳዲስ ቴክኖሎጂን በኤግዚቢሽን /በሚዲያ/ ለሕብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
6. ያስመጧቸውን ተሽከርካሪዎች በሥራ ላይ ተሰማርተው ያጋጠመ ቴክኒካል ችግር መኖሩንና አለመኖሩን መረጃ መሰብሰብ ፤
7. በተሽከርካሪው ላይ የተገኘ ችግር ተለይቶ ከታወቀ በኋላ ምክንያቱና መፍትሔው በሥልጠና ተካቶ ለሚመለከተው አካል ሥልጠና መሰጠት ፤
8. ስለአስመጡት ተሽከርካሪዎች ቴክኖሎጂ ለባለ ጋራገሮችም ሆነ ለሚመለከተው የሥራ ላይ ሥልጠና መስጠት፣
9. የአውቶሞቲቭን ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረገ ከሌሎች አስመጭ ካምፓኒዎችና ከሚመለከተታቸው ባለሙያዎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ ፤
10. በሥልጠና ዙሪያ ያለውን ሁኔታ ለማወቅ ከካምፓኒው ስልጠና ማዕከል እና ከባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት ጋር የቅርብ ግንኙነት ማድረግ እና
11. የተሽከርካሪ አስመጪ ካምፓኒዎች በየ3ወሩ ስለተሰጠው የሥራ ላይ ስልጠና ለትራንስፖርት ባለስልጣን ሪፖርት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

**ሐ. በልዩ ሁኔታ ተሽከርካሪ የሚያስገቡ ተቋማት/ግለሰቦች**

ፈቃድ ከሰጠው መስሪያ ቤት የተፈቀደበትን አግባብ የሚገልጽ ደብዳቤ ማምጣት

## 5. የተሽከርካሪ ማስገቢያ ፈቃድ

ተሽከርካሪውን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ፈቃድ የሚሰጠው ተሽከርካሪውን ከወደብ ከመጫኑና ወደ ሀገራችን ከመግባቱ በፊት ወይም ተሽከርካሪው ከተገዛበት ሀገር ወደ እዚህ ከመጫኑ በፊት በመሆኑ

1. ማስገቢያ ፈቃድ የሚያገለግለው ለስድስት (6) ወራት ጊዜ ብቻ መስፈርቱን አሟልቶ ሀገር ውስጥ እንዲገባ
2. ተሽከርካሪው በጉምሩክ የአሰራር ሂደት ውስጥ ከገባ የማስገቢያ ፈቃድን ማደስ ሳያስፈልግ

3. አንድ አስመጪ ወይም ግለሰብ ወይም ድርጅት ተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲያስገባ የተሰጠው ማስገቢያ ፈቃድ 6 ወር ያለፈው ሆኖ ተሽከርካሪውን በትራንስፖርት ቢሮዎች ለምዝገባ ሲያቀርብ ማስገቢያ ፈቃድ ሳይታደስ ቀድሞ የተሰጠውን የማስገቢያ ፈቃዱን ኮፒ ወይም ዋናውን በአስመጭው እርጥብ ማህተም እንዲረጋገጥ በማድረግ በምዝገባ ወቅት ከሌሎች መረጃዎች ጋር በማያያዝ

4. ተሽከርካሪውን ከአስመጪ የገዛ ባለንብረት የተሽከርካሪ ማስገቢያ ፈቃድ በራሱ ሥም ሳይጠየቅ በአስመጪው ማስገቢያ ፈቃድ ኮፒ ብቻ እና የሚጠበቅበትን ክፍያ ሲከፍል አገልግሎቱ ይሰጠዋል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ 5 ከ (1-4) የተዘረዘሩት እንደተጠበቀ ሆኖ በማስገቢያ ፈቃዱ የጊዜ ገደብ መሠረት ተሽከርካሪው አገር ውስጥ ወይም የጉምሩክ የአሰራር ሂደት ውስጥ ሳይገባ የተሰጠው የ6 ወር የፈቃድ ጊዜ ካለፈ የማስገቢያ ፈቃዱን ማደስ ይጠበቅበታል፡፡

6. **ተሽከርካሪ ሀገር ውስጥ ለሚገጣጥሙ እና ለሚያመርቱ ተሽከርካሪ አምራቾች የሚያስፈልገው መስፈርት**

   1. ባለስልጣኑ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት የወርክሾፕ /Work Shop/ ፋሲሊቲና የሰው ሀይል በበቂ ሁኔታ ላይ መሆን፣
   2. ባለስልጣኑ በሚያወጣው መስፈርት መሰረት በቂ የተሽከርካሪ ማቆሚያና የሥራ ቦታ ስለመኖሩ ማረጋገጫ ማቅረብ፣
   3. ለሚገጣጥሙትና እና ለሚያመርቱት ተሽከርካሪዎች በቂና አስተማማኝ የመለዋወጫ ዕቃ ለማቅረቡ ግዴታ መግባት፣
   4. የተሽከርካሪ መገጣጠሚያና ማምረቻ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እና የቫንሲ ቁጥር ፈቃድ ከትራንስፖርት ባለሥልጣን መውሰድ ፡፡

7. **ለአስመጪ የሚሰጥ ኢ.ት ተላላፊ ሰሌዳ**

   ሀ. የሚያገለግለው አስመጪው ተሽከርካሪውን ከጉምሩክ ጣቢያ ወደ ጉምሩክ መመርመሪያ ቦታ እንዲደርስ ፣ ከጉምሩክ መመርመሪያ ቦታ ወደ አስመጪው አድራሻ እስኪደርስ የሚያገለግል የተሽከርካሪ ጊዜያዊ ሰሌዳ ሲሆን ይህ ሰሌዳ ከአስመጪው አድራሻ ወደ ተሽከርካሪ ምዝገባ ቦታ ለመዉሰድ አያገለግልም፡፡



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No 1

ለ. አስመጪው ኢት ተላላፊ ሰሌዳ ለመውሰድ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ሰነዶች

1. አስመጪዉን የሚገልጽ መታወቂያ
2. የታደሰ የተሸከርካሪ አስመጪነት ንግድ ፍቃድ
3. የተሸከርካሪ ማስገቢያ ፍቃድ
4. የተሸከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ
5. በጉምሩክ እርጥብ ማህተም የተረጋገጠ ዲክለራሲዮን

8. ተሸከርካሪን ወደ ምዝገባ ቦታ ለማድረስ የሚወሰድ ተላላፊ ሰሌዳ

ሀ. የክልል እና የከተማ አስተዳደር ተላላፊ ሰሌዳ

ተላላፊ ሰሌዳዉ ተሸከርካሪዉን ከአስመጪዉ አድራሻ ወደ ተሸከርካሪ ምዝገባ ለማድረስ እና ለማስፈተሽ እንዲሁም ተሸከርካሪዉን 25 ኪ.ሜትር ለማይበልጥ ደርሶ መልስ ርቀት ለማንቀሳቀስ የሚያገለግል ለሦስት ቀናት በጊዜያዊነት የሚሰጥ ሰሌዳ ነዉ፡፡

ለ. ተላላፊ ሰሌዳ ለመዉሰድ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ሰነዶች፡-

1. ባለንብረቱን የሚገልጽ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ/መንጃ ፈቃድ/ ወይም የትዉልደ ኢትዮጲያዊ መታወቂያ ከፓስፖርት ጋር እንዲሁም ፓስፖርት፣
2. ዉክልና የተሰጠዉ ግለሰብ ከዋናዉ ጋር የተገናዘበ ህጋዊ ዉክልና ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ፣መንጃ ፈቃድ፣ ፓስፖርት
3. ከመስሪያ ቤት ወይም ከድርጅት የተወከለ ከሆነ የድርጅቱ የዉክልና ደብዳቤና የደርጅቱን መታወቂያ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
4. ኦርጅናል የጉምሩክ ዲክለራሲዮን
5. ከጉምሩክ ዲክለራሲዮን ጋር የተገናዘበ የVDD print out(C-number)
6. የታደሰ የተሸከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ እና የአስመጭነት ፈቃድ
7. ወደ ሀገር ዉስጥ የሚገቡ የተሸከርካሪ መመርመሪያ ቅጽ /ሮዝ ወረቀት/
8. የተቆረጠ ደረሰኝ/Invoice/ በባለንብረቱ ስም ከአታችመንት ጋር ማቅረብ ሲኖርባቸዉ ደረሰኝ/Invoice/ ማቅረብ ለማይችሉ የእጅ በእጅ የደረሰኝ ህትመት እና የማሳተሚያ ፍቃድ ከገቢዎችና ጉምሩክ በደረሰኙ መነሻ ቁጥር የተፈቀደበት ደብዳቤ፡፡
9. ተገቢዉን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ተላላፊ ሰሌዳ መስጠት፣

ሐ. ተላላፊ ሰሌዳ ዕድሳት

አንድ ተላላፊ ሰሌዳ የተሰጠዉ ተሸከርካሪ ተላለፊ ሰሌዳዉ ለሦስት ቀን (3 ቀን) የሚያገለግል ሲሆን ከሦስት ቀናት በላይ ካስፈለገ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚታደስ ሆኖ

ከአንድ ጊዜ በላይ ዕድሳት ለሚፈልጉ ባለጉዳይ ተላላፊ ሰሌዳዉ ለአላስፈላጊ ተግባር ሊዉል ስለሚችል በተሽከርካሪ የምዝገባ ሲስተሙ መሰረት በቅጣት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

## 9. የተሽከርካሪ የምዝገባና የሰሌዳ ዓይነቶች

በተሽከርካሪ የአመዘጋገብ መመሪያ መሰረት ተሽከርካሪዎችን እንደ ሚሰማሩበት የአገልግሎት ዓይነት በኮድ ለይቶ ቀጥሎ በተመለከተው መሰረት የምዝገባ እና የሰሌዳ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

1. ኮድ 01 ለታክሲ አገልግሎት
2. ኮድ 02 ለቤት አገልግሎት
3. ኮድ 03 ለንግድና ለግል ንግድ አገልግሎት(TIN NO. ላለቸው ለመንግስት ልማት ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች)
4. ኮድ 04 ለመንግስታዊ ተቋማት
5. ኮድ 05 ለሃይማኖት ተቋማት፣ ለሀገር በቀል ልዩ ልዩ ድርጅቶችና ማህበራት
6. ጊዜያዊ ሠሌዳ
   - 6.1. ተላላፊ
   - 6.2. የዕለት ሠሌዳ
7. ፓሊስ፡-ንብረትነታቸው የፖሊስ ለሆኑ ተሽከርካሪዎች፣
8. የኢምባሲዎች፣ የዓለም አቀፍና የዕርዳታ ድርጅቶች፣ አባሪ 3ን ይመለከቱ
   - 8.1. የተባበሩት መንግሥታት፡-
     - CD፡-በተባበሩት መንግሥታት የዲፕሎማቲክ መብት ላላቸው
     - UN፡-በተባበሩት መንግሥታት መስሪያ ቤት ወይም ለመስሪያ ቤቱ አባላት ተሽከርካሪዎች፣
   - 8.2. አፍሪካ ሕብረት ድርጅት፡-
     - CD፡-በአፍሪካ ሕብረት ድርጅት የደፕሎማቲክ መብት ላላቸው
     - AU፡-በአፍሪካ ሕብረት ድርጅት መስሪያ ቤት ወይም ለመስሪያ ቤቱ አባላት ተሽከርካሪዎች፣
   - 8.3. CD፡-ለዲፕሎማቲክ መልዕክተኞች ተሽከርካሪዎች፣

8.4. CD (ዕድ):- በተራድኦ ድርጅት መስሪያ ቤት ውስጥ የዲፕሎማቲክ መብት ላላቸው ባለሥልጣን ተሽከርካሪዎች፣

9. ልዩ ተንቀሳቃሽ:- ለማንኛውም ልዩ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ

10. የመከላከያ:- ንብረትነታቸው የመከላከያ ኃይል ለሆኑ ተሽከርካሪዎች፣

11. የልዩ ተንቀሳቃሽ ተሽከርካሪ በኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና የመከላከያ ተሽከርካሪ በመከላከያ ሚኒስቴር ምዝገባቸው የሚካሄድ ይሆናል፡፡

## 10. ለተሽከርካሪ ምዝገባ የሚደረግ የቴክኒክ ምርመራ

1. ተሽከርካሪዉ በአካል በተቋሙ መመርመሪያ ቦታ ማቅረብ፡፡
2. በሀገር ዉስጥ ሞደፊክ አሰርተው ለሚቀርቡ ተሽከርካሪዎች የታደሰ የአካል ለዉጥ ፈቃድ፡፡
3. የሀዝብም ሆነ የጭነት ተሽከርካሪ ጠቅላላ ክብደቱንና የጭነት ልኩ ከተገለፀ በስሌቱ መሰረት የሚስተናገድ ሆኖ ካልተገለፀ የሚዛን ወረቀት ያመጣል፡፡
4. ለአዲስ ያላገለገሉ ተሽከርካሪዎች በእንግሊዘኛ የተፃፈ የፋብሪካውን ብሮሸር /technical Spcification/ ማቅረብ ግዴታቸዉ ሲሆን የጭነት /የወንበር/ ልክ በተቀመጠው ቀመር መሰረት ይሰራላቸዋል፡፡
5. የተቋሙ ቴክኒሽያኖች ተሽከርካሪዉን መሰረታዊ የመመርመሪያ ቅጽ ላይ የተመለከቱት የተሽከርካሪዉ መለያ መስፈርት /specification/ መሟላቱን ማረጋገጥ፡፡

አዲስ/ያላገለገሉ/ ተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ አባሪ 1 ይመልከቱ

## 11. አዲስ ተሽከርካሪ ምዝገባ

1. አንድ ተሽከርካሪ የሕይወት ታሪክ የሚገልፁ ሰነዶችን በመመዝገብ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መያዝና
2. ተሽከርካሪው ለሚሰማራበት የአገልግሎት ዓይነት ተገቢ የሆነ መለያ ቁጥር ወይም ሠሌዳ ፣ ስለባለቤትነቱ ማረጋገጫ ሕጋዊነት ያለው የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ መስጠት
3. ለዓመቱ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ዓመታዊ ተለጣፊ ምልክት/ቦሎ/ መስጠት
4. አንድ ተሽከርካሪ ስለ ሕይወት ታሪኩ አንድ ነባር ቋሚ መዝገብ ይኖረዋል፡፡
5. በዚህ መዝገብ ውስጥ የተሽከርካሪ መሰረታዊ ሰነዶችና መረጃዎች ይያያዛሉ፡፡

6. ማንኛውም ለአዲስ ምዝገባ የሚቀርብ ተሽከርካሪ አስፈላጊ የምዝገባ ሰነዶች ተሟልተው መቅረባቸው ተረጋግጦ የቴክኒክ ምርመራ ከተከናወነ በኋላ አስፈላጊው መረጃ በአዲስ ተሽከርካሪ ምርመራ ሠርተፍኬት ላይ ጭነት ተወስኖና ተሞልቶ እንዲሁም በዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ሠርተፍኬት ላይ ብቃቱ ተረጋግጦ ለምዝገባ ይላካል፡፡

12. **ለአዲስ ተሽከርካሪ ምዝገባ የሚያስፈልጉ ሰነዶች**

1. ተላላፊ መመለሱን ማረጋገጥ፡፡
2. ተላላፊ ለመዉሰድ የቀረቡ መሰረታዊ ሰነዶች መሟላታቸዉን ማረጋገጥ፡፡
3. ለመጀመሪያ ምዝገባ የሚመጣ ተሽከርካሪ ለጭነት አወሳሰን የነጠላ ክብደት መመዘን የሚገባው ከሆነ የተመዘነበት ማረጋገጫ ሰነድ /የሚዛን ወረቀት/፡፡
4. ተሽከርካሪው ዋጋ ካሽ ሬጅስተር ደረሰኝ/Invoice/ ከዲክላራሲዮን ዋጋ በማነፃፀር ከፍተኛ በሆነዉ የቴምብር ቀረጡን 2% ማስከፈል፡፡
5. የ3ተኛ ወገን የጸና የመድን ዋስትና
6. ከ6 ወር ወዲህ የተነሱት 2 ጉርድ ፎቶ፣ ቴምብር
7. ተወካይ ከሆነ ሊብሬዉ በቴምብር ይሰራል፡፡
8. የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ሰሌዳ፣ ሊብሬ፣ ቦሎ መስጠት፡፡

ማሳሰቢያ

1. ተሽከርካሪዉ ወደ ሀገር ዉስጥ የገባበት የተሽከርካሪ መመርመርያ መስፈርት ማቅረብ ላልቻሉ በጉምሩክ ጣቢያ በሚገኙ የፌዴራል ትራንስፖርት የተሽከርካሪ ስታንዳርድ በሚያረጋግጡ ቴክኒሻኖች እንዲቀርቡና የስታንዳርድ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው ይደረጋል
2. ለመጀመሪያ ጊዜ ለአዲስ የተሽከርካሪ ምዝገባ የሚመጣ ተገልጋይ የመንገድ ፈንድ ክፍያ አይጠየቅም
3. አስመጪዉ ተሽከርካሪ አስመጥቶ በአስመጭው ግለሰብ ስም ለማስመዝገብ ሲፈልግ ደረሰኝ በስሙ በማሰራትና 2% በመክፈል እንደማንኛዉም ተገልጋይ አገልግሎት ያገኛል፡፡

4. በኢንቨስትመንት ስራ ላይ ለመሰማራት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሲያቀርብ ንግድ ፍቃድ ሳይጠየቁ የተሽከርካሪ መሰረታዊ ሰነዶችን ማሟላቱን በማረጋገጥ አገልግሎት ይሰጠዋል፡፡
5. የተሽከርካሪ ምዝገባ የሚካሄደዉ በሀገሪቱ የመሪ ህግ መሠረት ግራ መሪ ተሽከርካሪ ብቻ ነዉ፡፡

**13. በሀገር ውስጥ ከሚመረቱ እና ከሚገጣጠሙ ተሽከርካሪዎችን ገዝቶ ለምዝገባ ሲቀርቡ የሚያስፈልጉ ሰነዶች**

1. ከባለስልጣኑ የተሰጠ የተሽከርካሪ አካል ማምረቻና መገጣጠሚያ ብቃት ማረጋገጫ የታደሰ ፈቃድ፣
2. የተሰራው ወይም የተገጣጠመው ተሽከርካሪ የስታንዳርድ የወንበር/የጭነት ልክ ዝርዝር መግለጫ ሲቀርብ እና ሌሎች አስፈላጊ መሰረታዊ ሰነዶች ሲሟሉ አገልግሎት ይሰጣል

**14. የግል ንግድ የተሽከርካሪ ምዝገባ**

1. የድርጅት ስያሜያቸው በግለሰቡ ስም ከሆነ ንግድ ፈቃዱ ላይ ከግለሰቡ ስም በመቀጠል የተፈቀደለትን የንግድ ዘርፍ ሊብሬው ግርጌ ላይ በመፃፍ የተፈቀደለትን የግል ንግድ በማለት አገልግሎቱን መስጠት፡፡
2. ከገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚፈለግበት የስራ ግብር የሌለ ለመሆኑ ማስረጃ/ክሊራንስ ማቅረብ
3. በግል ንግድ የተመዘገበ ተሽከርካሪ የአገልግሎት ለውጥ ለማድረግ የባለንብረትነት ስም ማስመዝገቢያ እና የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል አገልግሎቱ ይሰጠዋል
4. ለግል ንግድ የተሽከርካሪ ምዝገባ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ ይኖርበታል ይሁን እንጅ ንግድ ፈቃድ ለማውጣት የተሽከርካሪ ሊብሬ ለሚያስፈልጋቸው በግል ንግድ ለሚሰማሩ ድርጅቶች የንግድ ስያሜ ማጸደቂያ ሰርተፊኬት ሲያቀርቡ ይስተናገዳል
5. ለንግድ ተሽከርካሪዎች በምዝገባ ወቅት የንግድ ፈቃድ ማቅረብ አይጠበቅባቸውም

15. በእርዳታ እና በበጎ አድራጎት ለተሰማሩ ድርጅቶች የተሽከርካሪ ምዝገባ

1. ለበጎ አድራጎት ወይም ለእርዳታ ድርጅቶች ከመሰረታዊ ሰነዶች በተጨማሪ ፈቃድ ከሚሰጥ አካል ፈቃድ ሲያመጡ
2. ለቀይ መስቀል፣ ቀይ ጨረቃ፣ ለኃይማኖት ተቋማትና ትርፋማ ላልሆኑት ማህበራት፣ ለህዝባዊ ማህበራትና ለመሳሰሉት ተቋማት አገልግሎት እንዲዉሉ ኮድ 5 ሰሌዳ እና
3. ለዓለም አቀፍ/ ለሀገር በቀል እርዳታ ድርጅቶች በነጭ መደብ ከብርቱካናማ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር እንደ ሀገራቱ መለያ ቁጥር የሚሰየም ሰሌዳ ይሰጣቸዋል፡፡

16. ለዕጣ ባለዕድሎች የተሽከርካሪ ምዝገባ

የተሽከርካሪ የሎቶሪ ዕጣ ዕድለኛ ስም ለማዛወር መሠረታዊ የተሽከርካሪ ሰነድ ማሟላት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ዕጣ አውጥቶ ለእድለኞች እንዲያስተላልፍ በአዋጅ ስልጣን ከተሰጠዉ አካል ህጋዊ ፈቃድ እና
2. ለአሸናፊዎቹ ከአሸነፉበት የዕጣ ቁጥር ጋር የተሽከርካሪውን ሻንሲና ሞተር ቁጥር በመጥቀስ ለባለእድለኛዉ ምዝገባ እንዲደረግ ከሚመለከተው አካል የተፃፈ ደብዳቤ ሲቀርብ አገልግሎት ይሰጠዋል

17. የኮር ዲፕሎማት ሠሌዳ ምዝገባ፡

መሰረታዊ የተሽከርካሪ ሰነዶች መሟላታቸው እንደተጠበቁ ሆነው፡-

1. የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የፈቀደበት ማስረጃ
2. ከቴምብር ቀረጥ 2% ክፍያ ነጻ ከሆነ ከገንዘብና ኢኮኖሚና ትብብር ሚኒስቴር ማስረጃ በማቅረብ አገልግሎት ያገኛሉ

18. ተሽከርካሪ ከቀረጥ ነጻ ሲገባ የሚካሄድ ምዝገባ

መሰረታዊ የተሽከርካሪ ሰነዶች መሟላታቸው እንደተጠበቁ ሆነው፡-

1. የቀረጥ ነጻ የመፍቀድ ስልጣን ካለው መ/ቤት ቀረጥ ነጻ መብት የተፈቀደበት ደብዳቤ
2. አስመጪው ከባለ ቀረጥ ነጻ ባለመብቱ ጋር ባለው ስምምነት መሰረት ቀረጥ ነጻ ከተፈቀደለት በላይ የዋጋ ልዩነት ካለው የልዩነቱን ቀረጥ ይቆርጣል

19. **የተሽከርካሪ ኦርጅናል ዲክላራሲዮን እና የሲስተም ማረጋገጫ/VVD/**

1. ለእያንዳንዱ የተሽከርካሪ ምዝገባ ከሚመለከተው አካል ኦርጅናል ዲክላራሲዮን መቅረብ ይኖርበታል
2. የተሰጠው ኦርጅናል ዲክላራሲዮን መረጃ በሲስተም ወይም በጉምሩክ ድህረ-ገጽ በኩል ከተለቀቀው መረጃ ጋር በማናበብ የመረጃው (ቬሪፌኬሽን ፎርም) ፕሪንት አውት ከሰነዶቹ ጋር መያያዝ አለበት
3. ቬሪፌኬሽን ፎርሙ ታትሞና በፊርማና ማህተም ተረጋግጦ ከዲክለራሲዮን ጋር ፋይል የሚደረግ ሲሆን ለተላላፊ ወይም ለምዝገባ አገልግሎት ብቻ እንጂ ለአስመጭ ወይም ለሌላ ባለንብረት ሊሰጥ አይችልም፡፡

20. **አስመጪ ድርጅት ተሽከርካሪ አስመጥቶ በራሱ በድርጅቱ ስም ለማስመዝገብ**

መሰረታዊ ሰነዶች መሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. Invoice/ደረሰኝ መቁረጥ አይጠበቅበትም
2. አንድ አስመጪ ተሽከርካሪውን ሲገዛ ሰነዶቹ በድርጅቱ ስም የተመዘገቡ መሆኑን ማረጋገጥ
3. 2% የቴምብር ቀረጥ ማስከፈል
4. ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ኮድ 03 ሰሌዳ ብቻ ይሰጠዋል

21. **ጅምላ ገዥ ተሽከርካሪ በችርቻሮ ለተጠቃሚዎች በሚሸጥበት ጊዜ**

መሰረታዊ ሰነዶች መሟላታቸው እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1. ቸርቻሪዉ ከጅምላ ሻጭ የገዛበት ደረሰኝ/Invoice ከነፕሪንት አውቱ ኮፒ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ በእርጥብ ማህተም የተረጋገጠ ወይም የእጅ በእጅ ሽያጭ ከገቢዎች የደረሰኝ የህትመት ፈቃድ፡፡
2. ቸርቻሪዉ ለገዢዉ Invoice ከነፕሪንት አውቱ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ይቆርጣል፡፡
3. የአስመጭው እና የቸርቻሪው የታደሰ የንግድ ፈቃድ

22. **የምርት ዘመን የሌላቸው ተሽከርካሪ ምዝገባ**

ተሽከርካሪዎች ለተለያዩ አግልግሎት ሲመጡ የተሽከርካሪዎችን የምርት ዘመን የሌላቸው ሲያገጥሙ፡-

19. **የተሽከርካሪ ኦርጅናል ዲክላራሲዮን እና የሲስተም ማረጋገጫ/VVD/**

1. ለእያንዳንዱ የተሽከርካሪ ምዝገባ ከሚመለከተው አካል ኦርጅናል ዲክላራሲዮን መቅረብ ይኖርበታል
2. የተሰጠው ኦርጅናል ዲክላራሲዮን መረጃ በሲስተም ወይም በጉምሩክ ድህረ-ገጽ በኩል ከተለቀቀው መረጃ ጋር በማናበብ የመረጃው (ቬሪፊኬሽን ፎርም) ፕሪንት አውት ከሰነዶቹ ጋር መያያዝ አለበት
3. ቬሪፊኬሽን ፎርሙ ታትሞና በፊርማና ማህተም ተረጋግጦ ከዲክለራሲዮን ጋር ፋይል የሚደረግ ሲሆን ለተላላፊ ወይም ለምዝገባ አገልግሎት ብቻ እንጂ ለአስመጭ ወይም ለሌላ ባለንብረት ሊሰጥ አይችልም፡፡

20. **አስመጪ ድርጅት ተሽከርካሪ አስመጥቶ በራሱ በድርጅቱ ስም ለማስመዝገብ**

መሰረታዊ ሰነዶች መሟላታቸው እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1. Invoice/ደረሰኝ መቁረጥ አይጠበቅበትም
2. አንድ አስመጪ ተሽከርካሪውን ሲገዛ ሰነዶቹ በድርጅቱ ስም የተመዘገቡ መሆኑን ማረጋገጥ
3. 2% የቴምብር ቀረጥ ማስከፈል
4. ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ኮድ 03 ሰሌዳ ብቻ ይሰጠዋል

21. **ጅምላ ገዥ ተሽከርካሪ በችርቻሮ ለተጠቃሚዎች በሚሸጥበት ጊዜ**

መሰረታዊ ሰነዶች መሟላታቸው እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1. ቸርቻሪዉ ከጅምላ ሻጭ የገዛበት ደረሰኝ/Invoice ከነፕሪንት አውቱ ኮፒ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ በእርጥብ ማህተም የተረጋገጠ ወይም የእጅ በእጅ ሽያጭ ከገቢዎች የደረሰኝ የህትመት ፈቃድ፡፡
2. ቸርቻሪዉ ለገዢዉ Invoice ከነፕሪንት አውቱ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ይቆርጣል፡፡
3. የአስመጭው እና የቸርቻሪው የታደሰ የንግድ ፈቃድ

22. **የምርት ዘመን የሌላቸው ተሽከርካሪ ምዝገባ**

ተሽከርካሪዎች ለተለያዩ አግልግሎት ሲመጡ የተሽከርካሪዎችን የምርት ዘመን የሌላቸው ሲያገጥሙ፡-

1. 17 ዲጅት የሻንሲ ቁጥር ካላቸው በሻንሲ ቁጥር የስሪት ዘመን በመውሰድ የምርት ዘመን ተወስኖ ወይም
2. ከአስመጭዎች የስሪት ዘመን መረጃ ከመረጃ ቋት መውሰድ ወይም
3. የተመሳሳይ ተሽከርካሪ ሞዴል ፈልጎ የምርት ዘመን መውሰድ ወይም
4. commercial invoice የተቆረጠበትን ዘመን እንደ ምርት ዘመን መወሰድ ወይም
5. ወደ ሃገር ውስጥ ሲገቡ ተሽከርካሪዎቹ አዲስ ከነበሩ የገቡበትን ዘመን እንደ ምርት ዘመን በመውሰድ ወይም
6. ያገለገሉ ተሽከርካሪዎቹ ከነበሩ ከመግባታቸው በፊት የነበራቸው እድሜ እና ከገቡ በኋላ ያገለገሉበትን ዘመን ደምሮ ያገለገሉበትን ዘመን በመውሰድ ወይም
7. ሃገር ውስጥ የሚገጣጠሙ ከሆነ የተገጣጠሙበትን ዘመን እንደ ምርት ዘመን በመወሰድ አገልግሎት ይሰጣል

23. **የኢት ሠሌዳ አገልግሎት አሰጣጥ**

መሰረታዊ ሰነዶች እንደተጠበቁ ሆኖ፡

1. 44 እና ከ44 መቀመጫ እንዲሁም ከ70 እና ከ70 ኩንታል በላይ የሚጭኑ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ክልሎች በሚያገናኝ የንግድ/የግል ንግድ/የኮንስትራክሽን እንዲሁም የመንገድ ማመላለሻ ስራ ለሚሰሩ
2. ንብረትነታቸዉ የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤት የሆኑ ተሽከርካሪዎች
3. ክልል ተሻጋሪ በሆነ በኢንቨስትመንት ስራ ላይ የተሰማሩ ለመሆኑ ከሚመለከተው አካል የኢንቨስትመንት ፈቃድ

24. **ለአምቡላንስ እና ለቱሪስት ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች**

መሰረታዊ ሰነዶች ማሟላታቸው እንደተጠበቁ ሆኖ፡

1. ተሽከርካሪው ለአምቡላንስ አገልግሎት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ለማሟላቱ ከጤና ቢሮ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲያቀርብ እና

2. ለቱሪስት ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጭነት ለሚሰማሩ ባለንብረቶች ተሽከርካሪው ለተፈለገው አገልግሎት ብቁ መሆኑን ከፈቃድ ሰጭው አካል የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲያቀርቡ አገልግሎት ይሰጠዋል፡፡

## 25. ማሽነሪ የሚገጠምላቸዉ ተሽከርካሪዎች ምዝገባ

ማሽን የተገጠመላቸው ወይም ማሽነሪዎችን የሚጭኑ ተሽከርካሪዎች የምዝገባ መስፈርት ሁኔታ ለአገልግሎት አሰጣጡ እንዲያመች የኮንስትራክሽን ተሽከርካሪዎች ምዝገባ በልዩ ልዩ ሲስተናገዱና የመጫን አቅሙ ማሽን የተገጠመለት በሚል አግባብ አገልግሎቱ ይሰጣል

## 26. ተሽከርካሪዎች ለምዝገባ ሲቀርብ የሶስተኛ ወገን መድን ዋስትና ስለማስፈለጉ

1. ለምዝገባ የሚቀርቡ ተሽከርካሪዎች ተላላፊ ሰሌዳም ሆነ መደበኛ ሰሌዳ፣ሊብሬ እና ቦሎ ከማግኘታቸው በፊት በሻንሲ እና ሞተር ቁጥር የሶስተኛ ወገን መድን ዋስትና ሽፋን ክፍያ ደረሰኝ ማቅረብ አለባቸው
2. ማንኛዉም አይነት ተሽከርካሪዎች አመታዊ ቦሎ ለመውሰድ ሲቀርቡ ከምርመራ ሰርተፍኬቱ ጋር የሶስተኛ ወገን መድን ዋስትና ሽፋን ክፍያ ደረሰኝ ሲያቀርብ ቦሎ ይሰጣል
3. ለተሽከርካሪ አስመጪዎች በሚሰጡ ተላላፊዎች የሚነዱ ተሽከርካሪዎች በዲክላራሲዮን ሻንሲ እና ሞተር ቁጥር የተገባ የሶስተኛ ወገን የመድን ዋስትና ሽፋን ክፍያ ደረሰኝ መያዝ አለባቸው
4. በሽያጭ የተላለፈ ተሽከርካሪ ሰነድ የማጽደቅ ስልጣን ባለው አካል በጸደቀ ሰነድ የ3ኛ ወገን የመድን ሽፋን በስሙ ሲያቀርብ የስም ዝውውር አገልግሎቱ ይሰጠዋል፡፡

## 27. ለኮድ- 02 (ለግል መገልገያ) ተሽከርካሪ ምዝገባ

ማንኛውም በሞተር ሃይል በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪ ለቤት አገልግሎት /ኮድ2/ ለመመዝገብ የሚችለው፡-

1. ሰዎችን የሚያጓጉዝ ከሆነ አሽከርካሪውን ጨምሮ እስከ አስራ ሁለት /12/ መቀመጫ ያለው፤
2. ደረቅ ጭነት የሚያጓጉዝ ከሆነ አንድ ሺህ 1000/ ኪ.ግ የሚጭን፤

3. ድርብ ተግባር ከሆነ አሽከርካሪውን ጨምሮ አምስት/5/ መቀመጫና እስከ ስምንት መቶ /800/ ኪ.ግ የሚጭን፤
4. ተሳቢ ከሆነ ጠቅላላ ክብደቱ ከሰባት መቶ ሃምሳ/750/ ኪ.ግ የማይበልጥ ሲሆን ይመዘገባል
5. የአገልግሎት ዘርፍ በዲካላረሲዮን ላይ ከተገለጸና ዲክላራሲዮኑ ላይ የአገልግሎት ዘርፉ ካልተገደበ በተገለጸው የአገልግሎት ዘርፍ አገልግሎቱ ይሰጠዋል፡፡

## 28. ድርብ ተግባር /ደብል ካፕ ተሽከርካሪዎች አመዘጋገብ

ድርብ ተግባር ያለው ተሽከርካሪ ሊመዘገብ የሚችለው፡-

1. በቤት ተሽከርካሪ አገልግሎት
2. ለመኪና ኪራይ አገልግሎት
3. በድርጅት (ለግልንግድ) አገልግሎት
4. ለመንግስታዊ ድርጅቶች ለመዘገብ ይችላል

## 29. ኪን ካፕ ተሽከርካሪ አመዘጋገብ

1. በደረቅ ጭነት
2. ለቤት ተሽከርካሪ አገልግሎት
3. ለመኪና ኪራይ አገልግሎት
4. ለድርጅት (ለግልንግድ) አገልግሎት
5. ለንግድ አገልግሎት
6. ለመንግስት ድርጅት አገልግሎት ሊመዘገብ ይችላል

## 30. ልዩ ኀታችና ተሳቢ ተሽከርካሪ ምዝገባ

1. ተሳቢና ኀታች የተለያየ ሰሌዳ ስለሚሰጣቸው የየራሳቸውን ዲክለራሲዮን ተሰርቶላቸው ሲቀርብ ብቻ አገልግሎቱ ይሰጣቸዋል፡፡
2. ልዩ ኀታችና ተሳቢ በሚጣመሩበት ጊዜ ልዩ ኀታችና የተሳቢው የአክስል መጠን እኩል ሲሆን ወይም ልዩ ኀታቹ በአንድ ሲበልጥ ብቻ ማጣመር ይችላል

3. ልዩ ጎታች የጭነት ልክ በአክስል ብዛት እየተቀመረ የጭነት ልኩ በሊብሬዉ ላይ ይገለፃል፡፡
4. ለተሳቢ/ለተጎታች የጭነት ልክ በአክስል ብዛት እየተቀመረ የጭነት ልኩ በሊብሬዉ ላይ ይገለፃል፡፡

31. የሻንሲና የሞተር ቁጥር/Chassis and Engine No/ ማረጋገጥ

ሀ. የሻንሲና የሞተር ቁጥሮች ከፋብሪካው አፃፃፍ ውጭ መሆናቸውን ለመለየት፡

1. የመፃፊያው ቦታ አለመሞረዱን
2. ሻንሲው አካባቢ ተቆርጦ የተቀጠለ አለመሆኑን
3. ቀጥታ መስመር ላይ ቁጥሮቹ መፃፋቸውን
4. የቁጥር አፃፃፋቸው ጥልቀት አንድ ዓይነት መሆኑን
5. በቁጥሮች መካከል ያለው ርቀት ተመሣሣይ መሆኑን፣
6. ሳይንጋደዱ በትክክል መፃፋቸውንና በየተሽከርካሪው ዓይነትና ሞዴል ላይ ያለውን ሞተር ቁጥር የአፃፃፍ ዓይነት ከሌላው አለመለየቱን ማረጋገጥ፡፡

ለ. አጠራጣሪ የሻንሲና የሞተር ቁጥር ማረጋገጫ ዘዴዎች

1. ቦታውን አጽድቶ በማጉያ መነፅር/በሉፕ/ ማየት
2. ከዲክለራሲዮን እንዲሁም ከስታንዳርድ ማረጋገጫ ሠነዶች ላይ ማመሳከር
3. ከተሽከርካሪ አስመጭ ካምፓኒዎች የየራሳቸውን የመኪና ስፔስፊኬሽን/ ማኑዋል ማለትም የመኪና ሞዴል፣ የሥሪት ዘመን፣ የሻንሲና የሞተር ቁጥር የያዘ የመረጃ ቋት/የመረጃ ባንክ/ ላይ ጠይቆ በማረጋገጥ
4. ሌሎች የዳታ ምንጮችን ማለትም የኢንተርኔት የመረጃ ምንጮችን ከአምራች አድራሽ መጠቀም ሊረጋገጥ ይችላል

ሐ. የተሽከርካሪ ሞተር ቁጥር የሌለው ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ ለምዝገባ ሲቀርብ

1. የሞተር ቁጥር የሌለው መሆኑ በመሠረታዊ ሰነዶች ከተገለፀ
2. የቁጥር መፃፊያ መደቡ ያልተፋቀ/ያልተመታ እና የሞተር ቁጥሩ እንዳሌለዉ ወይም እንደማይነበብ (ባዶ/Unreadble/) ተብሎ በቴክኒክ ባለሙያ ከተረጋገጠ

3. በባለስልጣኑ ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ የትራንስፖርት ቢሮ የስራ ሃላፊ የሞተር ማስመቻ ፈቃድ እንዲያገኝ በማድረግ አገልግሎቱ የሚሰጥ ሲሆን
4. በምዝገባ ወቅት /Engine code/ የሞተር መለያ ኮድ ከሻንሲ ቁጥር የመጨረሻዎቹን 6 ቁጥሮች በመውሰድ ባለሙያው አረጋግጦ በተቋሙ የስራ ኃላፊ የሞተር ማስመቻ ፍቃዱ እንዲያገኝ ይደረጋል

**መ. የሻንሲ ቁጥር አመታት መርህ**

የሻንሲ ቁጥር የሌለው ተሽከርካሪ ለምዝገባ/ለምርመራ ሲቀርቡ በቴክኒክ ባለሙያዎች ከተረጋገጠ በኋላ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት መሆኑ እየተረጋገጠ በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ የትራንስፖርት ቢሮ የስራ ኃላፊ በኩል ፈቃድ ካለቸው ድርጅቶች እንዲያስመታ ማስመቻ ፈቃድ ተሰጥቶት ቀጥለዉ በተዘረዘሩት መርህ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

1. የሻንሲ ቁጥር የሚመታው የሻንሲ ቁጥር ለመምታት ከፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ፈቃድ በተሰጠው ተቋም ብቻ ነው፡፡
2. መጀመሪያ ከውጭ ሲመጣ የሻንሲ ቁጥር የሌለው ከሆነ በባለስልጣን የሻንሲ ቁጥር ሲሰጠውና ሻንሲውን የመምታት ፈቃድ ባለው ተቋም ተመቶ ሲቀርብ አገልግሎት መስጠት
3. ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የሻንሲ ቁጥር የተመታ ከሆነ የተመታ ተብሎ ሊብሬው ላይ ተጽፎ በመደበኛ ሰሌዳ ይስተናገዳል
4. በሀገር ዉስጥ ለሚመረቱ የሻንሲ ቁጥር እንዲመታ ፈቃድ የተሰጠው ተቋም የሻንሲ ቁጥር ሲመታ ሰነዶቹን ማለትም ባለስልጣን የሰጠውን የሻንሲ የቁጥር እንዴክስ ኮፒ፣ የመምቻ ፈቃድ ኮፒ በእርጥብ ማህተም የተረጋገጠ እና የታደሰ የንግድ ፈቃድና የግብር ክሊራንስ ማቅረብ
5. የሻንሲ ቁጥር በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም (በዝገት፣ በጨዉ መበላት፣ በግጭት) የሻንሲ ቁጥሩ ከ50% በላይ የመጥፋት ሁኔታ ካጋጠመዉ የቀድሞ ቁጥር መልሶ እንዲመታ የተሽከርካሪዉ ፋይል ባለበት ተቋም ፍቃድ እንዲሰጠዉ ይደረጋል፡፡ከ50% በላይ የሻንሲ ቁጥሮቹ የሚነበብ ከሆነ

የቴክኒክ አስተያየት ተሰጥቶበት ሊብሬው ላይ ተገልጾ ባለበት አገልግሎት ይሰጠዋል፡፡

6. ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው ስታንዳርድ መሰረት መሆኑ እየተረጋገጠ በክልሉ ወይም በከተማ አስተዳደሩ የትራንስፖርት ቢሮ የስራ ኃላፊ የሻንሲ ማስመቻ ፍቃዱ እንዲያገኝ በማድረግ አገልግሎቱ የሚሰጥ ሲሆን በምዝገባ ወቅት /Chasis code/ የሻንሲ መለያ ኮድ ባለሙያው መፃፍይኖርበታል፡፡

32. **የተሽከርካሪ ሞድፊክ /Value Add/ ስራ፡**

የተሽከርካሪ ሞዲፍክ ስራ አሰርቶ የሚቀርቡ ባለጉዳዮች ከተሽከርካሪ መሰረታዊ ሰነዶች በተጨማሪ የሚከተሉትን አሟልቶ ሲቀርቡ አገልግሎት ይሰጣቸዋል

1. ተቋሙ ሞደፊክ/Value Add ለማድረግ የተሰጠው የአካል ለዉጥ ፈቃድ
2. ሞዲፊክ የተሰራበት/Value Add/የተደረገበት የሰነድ መረጃ
3. ከአስመጭ የተገዛበት እና ለሞዲፊክ የወጣውን የዋጋ ድምር ያካተተ ደረሰኝ እና
4. የአስመጭ የንግድ ፈቃድ ሰነዶችን አያይዞ ሲቀርቡ አገልግሎት ይሰጣል

33. **በተለያዩ ምክንያት መረጃ ሳያሟላ ተመዝግቦ የተገኘ ተሽከርካሪ**

1. የተሽከርካሪውን መሰረታዊ ሰነዶች እና ስታንዳርድ መፈተሽና የጎደለውን መለየትና ማረጋገጥ
2. የጎደለው ሰነድ በመዝገብ/ምርመራ ተቋም አለማሟላት ከሆነ ተሽከርካሪው ማሟላት ያለበትን መስፈርት ለይቶ መስጠት
3. የጎደለው ሰነድ በባለንብረቱ ማሟላት ያለበት ከሆነ ባለንብረቱ እንዲያሟላ ማድረግ
4. ተሽከርካሪው በአካል እንዲቀርብ በማድረግ ለተሽከርካሪው ስፔስፊኬሽን መስራት
5. የጎደለው መረጃ በተሟላበት አገልግሎት ይሰጣል
6. ሰነድ ሳያሟላ እንዲመዘገብ ያደረገ ወይም የመዘገበ አካል ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑን በበላይ ኃላፊ ሲታመን በህግ እንዲጠየቅ ማድረግ

34. **የባለቤትነት ስም ምዝገባ ክፍያ/የቴምብር ቀረጥ2%/ የማይመለከታቸው**

1. መንግስት ባፀደቃቸዉ አለም አቀፍ ስምምነቶች እና ኮንቬንሽኖች መሰረት ሰነዶች ከቴምብር ቀረጥ ነፃ ይደረጋሉ፡፡
2. የአክስዮን ድርሻ የምስክር ወረቀት ሲመዘገብ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልም፡
3. ባለ በጀት የመንግስት መ/ቤቶች የቴምብር ቀረጥ አይከፈልም
4. ከቀረጥ ነጻ የገቡ ተሽከርካሪዎች ያገልግሎት ጊዜያቸውን ሳይጨርሱ ቀረጥ ከፍለው ሲቀርቡና የምዝገባ ለውጥ ሲያደርጉ በተሽከርካሪው ላይ የሚፈለግ ተጨማሪ የስም ማዛወሪያ የቴምብር ቀረጥ ያቀረቡትን ዲክላራሲዮን ከቀድሞው ዲክላራሲዮን ጋር በማነጻጸር በልዩነቱ ተሰልቶ የቴምብር ቀረጥ እንዲከፈሉ ይደረጋል፡፡

35. **ከቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲመዘገቡ ስለተፈቀደላቸው ተሽከርካሪዎች**

1. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው የገቡ ከሚመለከተው አካል መረጃ ሲቀርብ ተሽከርካሪዎች ቀረጥና ታክስ እንዲከፍሉ ሳይጠየቁ ለተፈቀደለት ሶስተኛ ወገን በሊብሬው ላይ ቀረጥ አልተከፈለም ተብሎ መተላለፍ ይችላሉ፡፡
2. ውጭ ሀገር ቆይተው የሚመለሱ ባለጉዳዮች ከቀረጥ ነፃ የግል መገልገያነት የገቡ ተሽከርካሪዎችን ቀረጥ ሳይከፈልባቸው የንግድ ሰሌዳ ሊሰጣቸው አይችልም፡፡
3. ከቀረጥ ነፃ የገቡ ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ለውጥ፣የምዝገባ ለውጥ፣የስም ዝውውር ወይም ሽያጭ ለማድረግ ከቀረጥ ነፃ እንዲገባ ከፈቀደለት መስሪያ ቤት የስምምነት ደብዳቤ ማቅረብ ወይም ቀረጥ በመክፈል ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማስረጃ ሲያቀርቡ የጠየቁት አገልግሎት ይሰጣቸዋል፡፡

36. **በጋራ ባለንብረት ላይ የቴምብር ቀረጥ፡-**

1. በጋራ ባለቤትነት በተያዘና በህግ መሰረት የንብረት ባለቤትነት ምዝገባ በሚፈፀምበት ንብረት ላይ አንደኛው የጋራ ባለቤት ያለውን ድርሻ ለሌላው የጋራ ባለቤት ወይም የጋራ ባለቤት ላልሆነ ማንኛውም ሰው ሲያስተላልፍ በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የሚታሰበው ሙሉ ዋጋ ላይ ሳይሆን በተላለፈው ድርሻ ላይ ብቻ ነው፡፡

2. እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት በንብረቱ ላይ ስላለው ድርሻ በማስረጃነት ህጋዊ ውል ወይም የፀደቀ ኑዛዜ ማቅረብ የማይችል ከሆነ ወይንም ውሉ ወይንም ኑዛዜው እያንዳንዱን ባለሀብት የድርሻ ልክ/መጠን የማያመለክት ሲሆን እያንዳንዱ የጋራ ባለሀብት በንብረቱ ላይ የጋራ ባለሃብት ሆኖ ይቆያሉ፡፡

## 37. የተሽከርካሪ አካል ስፋት እና ርዝመት ስታንዳርድ

የተሽከርካሪዎች ክብደት እና መጠን መወሰኛ ደንብ ቁጥር 11/1982 እንደተገለፀው፡-

1. ማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪ መኪና ወይም ግማሽ ተሳቢ ጭነት ቢኖረውም ባይኖረውም ጠቅላላ የጎን ስፋት ከውጭ በኩል ተለክቶ ከ 2.5 ሜትር መብለጥ የለበትም
2. ማንኛውም ባለሞተር ተሽከርካሪ መኪና ጭነት ቢኖረውም ባይኖረውም ከፊትና ከኋላ መግፊያዎቹን ጨምሮ ጠቅላላ ርዝመቱ ተለክቶ ከ12 ሜትር መብለጥ የለበትም፡፡
3. የሊሞዚን ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ከተሽከርካሪው ጋር በሚመጣው የፋብሪካ ብሮሸር /technical specification/ መሠረት በአክሰሎች መካከል /wheel base/ ያለውን እርቀት በመለካትና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል፡፡ በእንግሊዝኛ የተፃፈ የፋብሪካውን ብሮሸር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል

<u>ማስታወሻ</u>

- የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች (አባሪ 3 ይመለከቱ )
- በጭነት ማመላለሻ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ተሽከርካሪ ማሟላት ያለበት መስፈርት (አባሪ 4 ይመለከቱ)

## 38. የተሽከርካሪው ክብደት፡

### ሀ. የማይታለፍ የአክሰል የመሸከም አቅም

1. የመሪ አክስል........................................ ከ80 ኩንታል የማይበልጥ
2. የነጠላ ጎማ ያለው አክስል........................ ከ80 ኩንታል የማይበልጥ
3. ጥንድ ጎማ ያለው አክስል......................... ከ100 ኩንታል የማይበልጥ

4. ለተንጠልጣይ ጎማ .................................... የመሸከም አቅም አይሰጠውም

ለ. የተጠጋጉ ሁለት አክስሎች

1. በመካከላቸው ያለው ርቀት ከ1300 ሚ/ሜ በታች ከሆነ ጠቅላላ ከ170 ኩንታል የማይበልጥ
2. በመካከላቸው ያለው ርቀት ከ1300 ሚ/ሜ በላይ ከሆነ እያንዳንዱ ከ100 ኩንታል የማይበልጥ

ሐ. የአክስል የመጫን ልኬት፡

1. ከፊት አንድ የመሪ አክስል፣ አንድ የኋላ አክስል እና ከፊትና ከኋላ ነጠላ ጎማ ያለው አክስል ሲኖረው ጠቅላላ ክብደት ከ160 ኩንታል በላይ እንዲሆን አይፈቀድም፡፡
2. ከፊት አንድ የመሪ አክስል፣ አንድ የኋላ አክስል እና ከኋላ ድርብ ጎማ ያለው አክስል ሲኖረው ጠቅላላ ክብደት ከ180 ኩንታል በላይ እንዲሆን አይፈቀድም፡፡
3. ከፊት አንድ የመሪ አክስል፣ ከኋላ ሁለት አክስል እና ድርብ ጎማ ያላቸው ሁለት ተከታታይ አክስሎች ጠቅላላ ክብደት ከ280 ኩንታል በላይ እንዲሆን አይፈቀድም፡

መ. በተከታታይ አክስሎች መካከል ያለው ርቀት ጠቅላላ ክብደት

- እስከ 1300 ሚ/ሜ ከሆነ ከ250 ኩ.በላይ እንዲሆን አይፈቀድለትም፡፡
- ከ1300 ሚ/ሜ በላይ ከሆነ ከ280 ኩ.በላይ እንዲሆን አይፈቀድለትም፡፡

1. ድርብ ጎማ ያላቸው የኋላ አክስሎች በመካከላቸው ያለው ርቀት ከ1300 ሚ/ሜ በላይ ከሆነ በጠቅላላ ክብደት ላይ እያንዳንዱ አክስል የማይታለፍ 100 ኩንታል ይጨመርለታል፡፡
2. ከላይ የተዘረዘሩት የክብደትና መጠን ልኮች የማይታለፍ ጣሪያዎች ናቸው፡፡ ሆኖም በፋብሪካው የሚሰጠው በሠንጠረዥ ከተወሰነው በታች ሆኖ ሲገኝ በፋብሪካው የተሰጠው ክብደትና መጠን ተፈጻሚ ይሆናል፡፡/ይወሰዳል፡፡
3. ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው ተመሣሣይ ሞዴል ያላቸው ተሽከርካሪዎች ተመሣሣይ የመጫን ችሎታ /የመቀመጫ ልክ/ ማግኘት አለባቸው፡

39. በአንድ ደረሰኝ የተሸጡ ብዛት ያላቸዉ ተሽከርካሪዎች

1. በተሽከርካሪዎቹ ቁጥር ልክ ለየብቻ ደረሰኝ መቁረጥ ወይም በተሽከርካሪዎች ቁጥር ልክ ኮፒ ተደርጎ ኦሪጅናል ደረሰኝ የሚገኝበት ተቋም ስሌዳ ተገልጾ በኮፒ ላይ እርጥብ ማህተም ተደርጎ በተሽከርካሪ ፋይል ውስጥ ማስቀመጥ
2. ግለሰቡ/ተቋሙ ከአንድ በላይ ተሽከርካሪ በአንድ ደረሰኝ ሲገዛ ትራንስፖርት ተቋሙ ከኦርጅናሉ ጋር በተረጋገጠ ኮፒ አገልግሎቱን ይሰጣል
3. ኦርጅናሉን ደረሰኝ የያዘ የመንግስት ተቋም ኮፒውን አገናዝቦ በእርጥብ ማህተም አረጋግጦ በደብዳቤ ሲልክ ይስተናገዳል
4. የተሽከርካሪዎቹ ዋጋ እኩል ከሆነ ጠቅላላ ዋጋውን ለቁጥራቸው እያካፈሉ በመውሰድ እያንዳንዱ የሚጠበቅባቸውክፍያ ሲፈጽሙ አገልግሎቱ ይሰጣል

40. ኢንቮይስ ሲጠፋ

1. ደረሰኙ/Invoice / ካሽ ሪጅስተር ስለመጥፋቱ ከፖሊስ ማስረጃ ማምጣት
2. ስለ ደረሰኙ/Invoice/ ካሽ ሪጅስተር መጥፋቱ ከገቢዎችና ጉምሩክ ማስረጃ ማምጣት
3. የጠፋው ደረሰኝ የእጅ በእጅ ሽያጭ ከሆነ ደረሰኙን ከቆረጠው አካል የቀሪውን ኮፒ በእርጥብ ማህተም ከመሸኛ ደብዳቤ ጋር አያይዞ ማቅረቡን ተረጋግጦ ሲቀርብ አገልግሎቱ ይሰጣል

41. የመረጃ ግልባጭ አሰጣጥ

1. የተሽከርካሪ መሰረታዊ ሰነዶች ማለትም ዲክላራሲዮን በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ከባለንብረቱ ውጭ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ተገናዝበው አይሰጡም
2. የመሠረታዊ ሰነዶች መረጃ ለመጠየቅ የህግ መብት ያላቸው የፍትህ አካላት የሚመለከተው የስራ ኃላፊ በማቅረብ በማጣራት ግልባጭ መስጠት ይችላል፡፡

42. የኦርጅናል ደረሰኝ /invoice አጠቃቀም

1. ለመንግስት ተቋማት፣ የግብረሰናይ ድርጅቶችና ማህበራት፣ ለድርጅቶች (ኮድ 03 ሰሌዳ ለሚጠቀሙ)፣ አለም ዓቀፍ ድርጅቶች (UN,CD,AU...

ወዘተ) ኦርጅናል ደረሰኝ/invoice ከኦርጅናሉ ጋር የተገናዘበ ኮፒ በመቀበል አገልግሎቱን መስጠት

2. ለግለሰብ ተገልጋይ ኦርጅናል ደረሰኝ/invoice በመቀበል ማስረጃ ሲጠይቅ የተገናዘበውን ኮፒ መስጠት፡፡
3. ፋይናንስ የሚያትመው የውልና ማስረጃ ደረሰኝ በኮፒው አገልግሎት መስጠት አይቻልም፡፡
4. የውልና ማስረጃ ማስረጃው ሲጠፋ (የግለሰቡ) ከውልና ማስረጃ ኮፒ ተደርጎ ተገናዝቦ ሲመጣ አገልግሎቱ ይሰጣል

## 43. ልዩ ልዩ የእርማት አገልግሎቶች

1. ባለጉዳዩ የማመልከቻ ፎርም እንዲሞላ ማድረግ፣
2. የተጠየቀውን የእርማት /ማስተካከያ /ጥያቄ ከተሽከርካሪው ፋይልና ከኮምፒውተር በሚገባ ማጣራት ልዩነት ካለው ተሽከርካሪውን በአካል አስቀርቦ ማረጋገጥ፣
3. ጉድለቱ ከአመልካቹ ከሆነ አስፈላጊውን ክፍያ በማስፈፀም የተጠየቀውን የእርማት አገልግሎት መስጠት፣
4. ስህተቱ የተቋሙ መሆኑ በቅርብ ሀላፊ ከተረጋገጠ ያለክፍያ የእርማት /ማስተካከያ/ አገልግሎት ይሰጣል

ከማሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

# ክፍል ሶስት

## የተሽከርከሪ አገልግሎት አሰጣጥና የሚያስፈልጉ ሰነዶች

44. የተሽከርካሪ ወቅታዊ የዋጋ ግምት አሰጣጥ

1. የተሽከርካሪ ግምት በሚሰራበት ወቅት ተሽከርካሪው የተሰራበትን ሀገር ተመራጭነት መሰረት በማድረግ ለየሀገሮቹ የተሰጣቸው ነጥብ በግምት ስሌቱ ታሳቢ ይደረጋል
2. ለሀገሮቹ ተመራጭነት በዝርዝሩ ውስጥ የሌሉ ከሆነ ተሽከርካሪው የተመረተበት ሀገር ለአህጉሩ በተሰጠው ነጥብ እየተወሰደ የሚሰላ ይሆናል፡፡
3. የተሽከርካሪ ባለንብረትነት ሥም ዝውውር በሚከናወንበት ጊዜ የተሽከርካሪው ወቅታዊ ግምት በኮምፒውተር ስሌቱ እየተሰራ የስም ማዛወሪያ ቀረጥ/ የቴምብር ቀረጥ/ የሚከፈል ሆኖ የኮምፒውተር ግምቱ ቅሬታ የቀረበበት ከሆነ እንደ አስፈላጊነቱ በማንዋል በተቀመጠው የመገመቻ ቀመር መሠረት ሊሰራና ሊረጋገጥ ይቻላል፡፡
4. ለአገልግሎት ፈላጊ ተቋም የተሽከርካሪ ወቅታዊ ግምት በተቀመጠው የመገመቻ ቀመር መሠረት በኮምፒውተር ስሌቱ እየተሰራ በጠየቁት መሠረት ግምቱ ይሰጣቸዋል፡፡

45. በሽያጭ የተሽከርካሪ ስም ዝውውር

አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ሰነዶች

የተሽከርካሪ መሰረታዊ ሰነዶችን ማሟላት እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1. በተሽከርካሪው ላይ የተላለፈ ማንኛውም ዓይነት እዳ እና እገዳ እንዲሁም ቀረጥ ያለበት ከሆነ ህጋዊ ማስነሻ ማስረጃ ወይም የስምምነት ደብዳቤ
2. ኮድ 01 እና ኮድ 03 ከሆነ ከገቢዎች የግብር ክሊራንስ
3. የዘመኑን ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ/ቦሎ/ ያደረገ
4. የጸደቀ የውልና ማስረጃ ሰነድና የስም ዝውውር 2% የከፈለበት ማስረጃ
5. የንግድ ተሽከርካሪ ከሆነ አንዱ የግምት ውጤት ለሀገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን ይላካል ሁለተኛውን የግምት ውጤት ሁለቱ ተዋዋዮች ውል መፈፀም የሚችሉ ለመሆኑ በሸኚ ደብዳቤ ለሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት የተላከበት ሰነድ

6. የቤት ተሸከርካሪ ከሆነ የግምት ውጤቱን በቀጥታ ለሠነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ የተላከበት ሰነድ
7. የገዥ 2 ጉርድ ፎቶግራፍ
8. የስም ዝውውርና የአገልግሎት ለውጥ የሚያደርግ ከሆነ ተሸከርካሪው በድጋሚ ለቴክኒክ ምርመራ ብቃት ማረጋገጫ ሲቀርብ አገልግሎቱ ይሰጣል፡፡
9. የአንዳድ ማሰልጠኛ ተሸከርካሪዎች ስም ዝውውር ለማድረግ ሲፈልጉ ተቋሙ የማሰልጠን ፈቃዱን ከሰጠው አካል ፈቃድ ወይም የተፈቀደለትን ካታጎሪ መቀየሩን መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## 46. በጨረታ የሚሸጡ ተሸከርካሪ ለመመዝገብ የሚያስፈልጉ ሰነዶች

በጨረታ ተሸከርካሪ ለመሸጥ ህጋዊ መብት ያላቸው ተቋማት የተሸጡ የስም ዝውውር አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ሰነዶች፡-

1. ተሸከርካሪው ቀረጥ ያለበትና ዲክለራሲዮን የሌለው ከሆነ አዲስ በገዥው ስም የተሰራ ዲክላራሲዮን
2. በተጠቃለለው የጨረታ አዋርድ ደብዳቤ (ጨረታ የወጣበትን ቀንና ቁጥር፣የጋዜጣ ስም፣የአሸናፊውን ስም፣የተሸከርካሪውን የሻንሲና የሞተር ቁጥር ጨረታውን ያሸነፈበትን ዋጋ መያዝ አለበት) ከክፍያ ደረሰኝ ጋር ማቅረብ
3. ከመንግስት ተቋማትና ባንኮች በሚካሄድ የጨረታ የተሸከርካሪ ሽያጭ በሚከናወንበት ጊዜ የተሸከርካሪ ስም ዝውውር 2% ክፍያ የጨረታ ዋጋውን በመውሰድ በአገልግሎት መስጫ ተቋሙ የሚከፈል ይሆናል፡፡
4. ከተለያዩ የግል ድርጅቶች በጨረታና በቀጥታ ሽያጭ በሚከናወንበት ጊዜ በውልና ማስረጃ በጸደቀ ሰነድ ብቻ አገልግሎት የሚሰጣቸው ሆኖ የስም ዝውውር 2% ክፍያ በአዋዋዩ ተቋሙ የሚከናወን ሆኖ የከፈለበትን ደረሰኝ በመቀበል ይስተናገዳል፡፡
5. በጨረታ ተሸጦ ለምዝገባ የመጣ ተሸከርካሪ የዓመታዊ ቴክኒክ ምርመራ በማድረግ ሰርትፍኬት ማምጣት

47. **የመንግስት ድርጅት በሚዋሃዱበት፣ በሚለያዩበትና እንዲፈርሱ በሚደረግበት ጊዜ**

1. የመንግስት ድርጅት በህጋዊ መንገድ ሲቀላቀሉ በሁለቱም በተቀላቀሉ ድርጅቶች ስም የነበሩት ተሽከርካሪዎች የሚጠበቅባቸውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል አዲስ በተቀላቀሉ ድርጅት ስያሜ ለመዘገቡ ይችላሉ
2. አንድ የነበረው ድርጅት በሁለት ድርጅት ስያሜ ሲለያዩ በንብረት ክፍፍሉ ላይ በህጋዊ መንገድ በተገኙ ውሳኔ ሰነድ መሰረት ተሽከርካሪዎች ይመዘገባሉ
3. የመንግስት ድርጅት ሲፈርሱ ንብረቱ ወይም መብቱ በህጋዊ መንገድ ለተላለፈለት ድርጅት/ግለሰብ ህጋዊ ሰነድ ሲያቀርብ ሊመዘገብ ይችላል
4. ተሽከርካሪዎችን ከአንዱ ድርጅት/ተቋም ወደ ሌላ ድርጅት/ተቋም ለማስተላለፍ የተሽከርካሪውን ሻንሲና ሞተር እንዲሁም የሚተላለፍበት አግባብ ተጠቅሶ የተጻፈ ደብዳቤ በህግ ሰለመከናወኑ (ስለመፍረሱ፣ ሰለመዋሃዱ እና ስለመለያየቱ) የሚገልጽ ማስረጃ ሲቀርብ ስም ዝውውር ይከናወናል፡፡

48. **የሰነድ ጉድለት ያለበት እና የጠፋ ፋይል ያለው የተሽከርካሪ ስም ዝውውር ምዝገባ**

1. ቀደም ሲል በሊብሬው አገልግሎት እንዳገኙ/እንዳደሱ ማረጋገጥ
2. አገልግሎቱን የሚያገኝ ተሽከርካሪ የሊብሬ፣ የቦሎ፣ እና የክፍያ ደረሰኝ የአገልግሎት ክፍያ ማስረጃዎችን ማረጋገጥ
3. በሁሉም የአገልግሎት መስጫ ተቋማት እና ወደ ሲስተም ያልገባ ፋይል መረጃቸው በሲስተም እና በሃርድ ኮፒ ተፈልጎ የሌሉ መሆኑን በደብዳቤ ማረጋገጥ
4. በሻንሲና በሞተር ቁጥር ዲክላራሲዮን ማሰራት
5. ለንግድ/ለግል ንግድ የንግድ ፈቃድ ወይም የግብር ክሊራንስ
6. ተሽከርካሪው በአካል እንዲቀርብ በማድረግ ስፔስፊኬሽን መስራት
7. ተሽከርካሪው የመ/ቤቱ ወይም የድርጅቱ ከሆነ በንብረትነት ይዞ በነበረ ጊዜ በተሽከርካሪው ላይ የሚፈለግ እዳና እግድ በማንኛውም ጉዳይ ተጠያቂ ለመሆን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ከተቋሙ ማምጣት
8. የግለሰብ ተሽከርካሪ ከሆነ ባለንብረቱ በተሽከርካሪው ላይ የሚፈለግ እዳና እግድ ቢኖር ለመተካት ወይም ተጠያቂ ለመሆን የሚያስችል የውል ግዴታ

በህግ አገልግሎት ክፍል በተዘጋጀ ፎርማት መፈረም ፎርሙ በአባሪነት ይያያዛል

9. ውዝፍ ክፍያ ካለ በማስከፈል አገልግሎቱን መስጠት

## 49. የሰነድ ጉድለት ያለበት የመንግስት ተሽከርካሪ በጨረታ ተሸጦ ለምዝገባ ሲቀርብ

1. የጠፋው ሊብሬ ከሆነ ስለጠፋው ሊብሬ የማረጋጫ ደብዳቤ ከጨረታ አውጭ መስሪያ ቤቱ ማቅረብ
2. ጨረታ አውጭ መስሪያ ቤት ስለ ተሽከርካሪው የመረጃ ሁኔታ ዝርዝር መግለጫ ማቅረብ
3. በሻንሲና በሞተር ቁጥር ዲክላራሲዮን ማሰራት
4. ተሽከርካሪው በአካል እንዲቀርብ ማድረግ ስፔስፊኬሽን መስራት
5. በተጠቃለለው የጨረታ አዋርድ ደብዳቤ (ጨረታ የወጣበትን ቀንና ቁጥር፣የጋዜጣ ስም፣የአሸናፊውን ስም፣የተሽከርካሪውን የሻንሲና የሞተር ቁጥር ጨረታውን ያሸነፈበትን ዋጋ መያዝ አለበት)ከክፍያ ደረሰኝ ጋር ማቅረብ
6. ከተሽከርካሪው ጨረታ አውጭው መ/ቤቱ ወይም ድርጅት በይዞታው ስር በነበረ ጊዜ በተሽከርካሪው ላይ የሚፈለግ ማንኛውም ጉዳይ ኃላፊነቱን ይወስዳል

## 50. አደጋ የደረሰበት የኢንሹራንስ ተሽከርካሪ ስም ዝውውር ምዝገባ

1. ኢንሹራንስ በሻንሲው ላይ ሙሉ ጉዳት ደርሶበት የተረከቡትን ተሽከርካሪ በሚወገዱበት አግባብ ከማስወገድ ውጭ አስጠግኖ ለሽያጭም ሆነ ለማስመዝገብ ማቅረብ አይችሉም ይሁን እንጅ በአካል ለውጥና ጥገና መመሪያ መሰረት ፈቃድ ወስዶ አስጠግኖ ከቀረበ የሚስተናገድ ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተሽከርካሪው ባለቤት ለኢንሹራንሱ በውልና ማስረጃ የጸደቀ የውክልና ማስረጃ ሲቀርብ
3. ቻንሲ ቁጥር የሚመታ እና ቻንሲና ሞተር የሚቀየር እንዲሁም የአካል ለውጥ የሚደረግ ከሆነ ድርጅቱ በጥገና ጊዜ የቻንሲና ሞተር ቁጥር

የማስመቻ ፈቃድ፣ የሻንሲና የሞተር ለውጥ ፈቃድ እና የአካል ለውጥ ፈቃድ ባለስልጣኑ መ/ቤት ባወጣው ስታንዳርድ እና አሰራር መሰረት ተረጋግጦ ፋይሉ ካለበት ክክልል/ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ ያስፈቀደበት ደብዳቤ ሲቀርብ

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተፈቀደለት መሰረት ተሽከርካሪው የቻሲና የሞተር ቁጥር መመታት እና መለወጥ እንዲሁም የአካል ለውጥ ካደረገ የአካል ለውጥ፣ የቻሲና የሞተር ቁጥር መመታት እና መለወጥ ያደረገበት ማስረጃ እንዲሁም ህጋዊ ፈቃድ ካለው ጋረዥ የጥገና ሰነድ ጋር ሲቀርብ
5. የጥገና እና የአካል ለውጥ ካደረገ በኋላ ለአገልግሎቱ ብቁ መሆኑን የቴክኒክ ብቃቱ በባለሙያዎች ተፈትሾና ተረጋግጦ ሲቀርብ እና
6. በጨረታ ሲሸጥ ኢንሹራንሱ የሸጠበት የጨረታ ዋጋ ለቴምብር ቀረጥ የማስከፈያ የዋጋ ግምት በመጠቀም አገልግሎት ይሰጣል
7. ድርጅቱ ለራሱ ለመጠቀምም ሆነ ለመሸጥ የህግ አግባብ ማቅረብ ካልቻለ ተሽከርካሪን የሚወርሰውም ሆነ የሚሸጠው የተሽከርካሪ መመሪያ በሚያዘው መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡

## 51. የጠፋ ሠሌዳ ወይም ሊብሬ ምትክ አሰጣጥ

1. የተሽከርካሪው ሠሌዳ ወይም ሊብሬ በባለጉዳዩ ስም የተመዘገበ መሆኑን ማረጋገጥ፣
2. በአቅራቢያው ከሚገኝ የፖሊስ ጽ/ቤት ስለ መጥፋቱ ማስረጃ ማቅረብ
3. የጠፋውን ሠሌዳ ወይም ሊብሬ በዝርዝር ቅጹ ላይ በመሙላት ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲወጣ በባለጉዳዩ ስም ለፕሬስ መጻፍ፣
4. የጠፋዉ ሊብሬ ከሆነ የወጣው ጋዜጣ አየር ላይ ከዋለ ከ15 ቀን በኋላ መሆኑን በማረጋገጥ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ መረጃ ከፋይል ጋር በማያያዝ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ አሰከፍሎ ሊብሬ ግልባጭ በማዘጋጀት ለባለጉዳዩ አገልግሎት መስጠት እና
5. የጠፋው ሠሌዳ ከሆነ ጋዜጣ መውጣት ሳይጠበቅበት ለፕሬስ አገልግሎት የተከፈለበትን ደረሰኝ በመያዝ ለሠሌዳ ምርትና ስርጭት ማዕከል ደብዳቤ መፃፍ አለበት

52. የሊብሬ ግልባጭ አሰጣጥ፣

1. አዲስ ሊብሬ በመውሰድ የበርካታ ዓመታት ግብር ሳይከፍል እንደ አዲስ የንግድ ፈቃድ እንዳያወጣ የግብር ክሊራንስ መቅረቡን ማረጋገጥ
2. የሊብሬ ግልባጭ ጥያቄ ሲቀርብ ሊብሬው ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣበት ቀን፣ ወርና ዓ.ም በሊብሬ የግርጌ ማስታወሻ እና ሲስተም ላይ ተጠቅሶ የሚፈለግበትን ክፍያ ሲከፍል አገልግሎቱ ይሰጠዋል

53. ቦሎ ሲጠፋ ወይም ሲበላሽ ምትክ/ግልባጭ/ አሰጣጥ

1. የጠፋው ወይም የተበሸው ቦሎ የዘመኑ ቦሎ መሆኑን እና በአመልካቹ ስም መመዝገቡን ከኮምፒውተር ወይም ከደረቅ ፋይል ማጣራት እና
2. አመልካቹ ስለመጥፋቱ ያቀረበውን የፖሊስ መረጃ መሠረት አድርጎ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል የዘመኑን የቦሎ ምትክ አገልግሎት መስጠት፣

54. የተበላሸ ወይም የዕድሳት ቦታ ላለቀ ሊብሬ እና ለተበላሸ ሰሌዳ ምትክ ስለመስጠት

1. የተበላሸው ወይም የዕድሳት ቦታ ያለቀበት የተሽከርካሪ ሊብሬ በአመልካቹ ስም መመዝገቡን ማረጋገጥ
2. የተበላሸው የተሽከርካሪ ሰሌዳ ከሆነ በአመልካቹ ስም መመዝገቡን ማረጋገጥ
3. የተበላሸው ሊብሬ ሲሆን የተበላሸውን ይዞ በስሙ ስለመመዝገቡ ከኮምፒውተር ወይም ከደረቅ ፋይል በማጣራት ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣበት ቀን፣ ወር እና ዓ.ም በሲስተም ላይ ተጠቅሶ እና የሚፈለግበትን ክፍያ ሲከፍል የግልባጭ አገልግሎቱ ይሰጠዋል
4. የዕድሳት ቦታ ያለቀበት ሊብሬ ከሆነ ሊብሬውን በመሰረዝ ተመላሽ በማድረግ ፋይል ላይ አያይዞ በስሙ ስለመመዝገቡ ከኮምፒውተር ወይም ከደረቅ ፋይል ከተረጋገጠ በኋላ የሚፈለግበትን ክፍያ ሲከፍል የግልባጭ አገልግሎቱ ይሰጠዋል
5. የተበላሸው ሰሌዳ ከሆነ ባለጉዳዩ የተበላሸውን ሠሌዳ በመያዝ ሠሌዳ ምርትና ስርጭት ማዕከል በመቅረብ የሚጠበቅበትን ክፍያን በመክፈል አገልግሎቱን ያገኛል

**55. የብዙ ባለንብረትነት መብትና የሊብሬ ለውጥ፣**

በአንድ ሰው ስም የነበረ የተጨማሪ የተሽከርካሪ የባለንብረትነት መብት ጥያቄ ሲቀርብ

1. የባለንብረትነት መብት ክፍ/ቤት ውሳኔ ወይም ከውልና ማስረጃ የጸደቀ ሰነድ ሲቀርብ
2. የቴምብር ቀረጥ እንደ ድርሻው ተሰልቶ የሚከፈል ክፍያ ሲከፈል እና
3. ሊብሬ ላይ በእነ በሚል የሚመዘገብና የሁሉንም የባለንብረቶቹን ስም ዝርዝር ሊብሬ ላይ ለመጻፍ ቦታ በማይበቃበት ጊዜ በሃርድ ኮፒም ሆነ በሲስተም ላይ ስም ዝርዝራቸው ከነፎቶ ሰነዱ ላይ አብሮ በማያያዝ አገልግሎት ይሰጣል

**56. ለቀድሞ ሠሌዳ ለዉጥ መስጠት**

በደንብ ቁጥር 74/1993 መሰረት ሰሌዳቸውን ያልቀየሩ የተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ባለይዞታ የሚከተለውን መስፈርት ሲያሟሉ አገልግሎት ይሰጣቸዋል

1. ተሽከርካሪው በአካል ቀርቦ የቴክኒክ ብቃቱ ሲረጋገጥ
2. ሻንሲና ሞተር ቁጥር ትክክለኛ የፋብሪካው መሆናቸውን በማረጋገጥ እና
3. የሠሌዳ ለውጥ ያልተደረገበት ምክንያት አመልካቹ በደብዳቤ/ በማመልከቻ ሲያመለክት፣ ባለንብረቱ/ህጋዊ ተወካይ/ መቅረባቸውን በማረጋገጥና የቆየበት ምክንያት በመዝጋቢው አካል ኃላፊ ሲታመንበት ተፈላጊውን ክፍያ በማስከፈል አገልግሎቱ ይሰጣል፡፡

**57. የውጭ ሀገር መንግስት ኢምባሲዎች፣ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችና የቆንስላ ጽ/ቤቶች ተሽከርካሪ ሰሌዳ አመላለስ**

የዲፕሎማት መብት ያለው ሰው የአገልግሎት ጊዜውን ጨርሶ ሲጠቀምበት የነበረውን ሰሌዳ ሲመልስ ሰሌዳው እንዲሰረዝ

1. ባለስልጣኑ ወይም በባለስልጣኑ ውክልና የተሰጠው አካል ሰሌዳ መረከቡን የሚገልጽ ደብዳቤ
2. ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማረጋገጫ ደብዳቤ

3. ዲፕሎማቱ ሰሌዳ እና ለብሬ መልሶ የተሽከርካሪ ምዝገባ ስረዛ መደረጉን በማረጋገጥ እና ሰሌዳውን በአግባቡ መያዝ
4. ተሽከርካሪው ከሀገር እንዲወጣ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ(1-4) የተሟላ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደገና ተመላሽ የተደረገው ሰሌዳ አዲስ ለሚመጣው ዲፕሎማት ይሰጠዋል

## 58. የተሽከርካሪ ምዝገባ ስረዛ

1. ባለጉዳዩ ወይም ህጋዊ ተወካይ ሰሌዳ ለመመለስ የፈለገበትን ምክንያት በደብዳቤ ወይም በማመልከቻ ጥያቄ ማቅረብ
2. በኮምፒውተር ወይም በፋይል የተመዘገበ እዳ እና እግዳ ትዕዛዝ አለመኖሩን ማረጋገጥ
3. ትራፊክ ፖሊስና ከፖሊስ በወንጀል ዙሪያ ችግር የሌለበት ለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ
4. የንግድ ተሽከርካሪ ከሆነ የግብር ክሊራንስ ማቅረብ
5. የቦሎ አገልግሎት ክፍያ ካለ በቅጣት እንዲከፈል ማድረግ
6. የቴክኒክ ብቃቱን በሁለት ባለሙያዎች ማስገምገም እና ተሽከርካሪው ከጥቅም ውጭ እንዲሆን በባለሙያዎቹ የተሰጠ ማስረጃ ሲቀርብ እና
7. ተሽከርካሪው ፋይሉ ካለበት በእርቀት ቦታ ላይ የሚገኝ ከሆነ እና መንቀሳቀስ የማይችል ከሆነ በአቅራቢያው የሚገኝ የትራንስፖርት ቢሮ በመደባቸው ሁለት ቴክኒሻኖች የቴክኒክ ብቃቱ ተፈትሾ እና ከጥቅም ውጭ እንደሆነ በባለሙያዎች ተወስኖ የተሰጠ ማስረጃ ሲቀርብ
8. የዘመኑን ቦሎና የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል በማድረግ ሰሌዳውንና ሊብሬውን መመለሱን በማረጋገጥ ማስረጃ መስጠት

## 59. የተሽከርካሪ ምዝገባ ጊዜያዊ ስረዛ እና ሰሌዳና ሊብሬ በአደራ ሲቀመጥ

ሰሌዳ ወይም ሊብሬ ወይም ሁለቱም በአደራ ለማስቀመጥ የፈለገ ማንኛዉም ተገልጋይ ጥያቄውን በጽሁፍ ሲያቀርብ

1. ባለንብረቱ ወይም ህጋዊ ተወካይ ሰሌዳ ለማስቀመጥ የፈለገበትን ምክንያት በደብዳቤ መጠየቅ
2. በኮምፒውተር ወይም በደረቅ ፋይል የተመዘገበ እዳ እና እግዳ ትዕዛዝ አለመኖሩን ማረጋገጥ፡፡
3. ትራፊክ ፖሊስና ከፖሊስ በወንጀል ዙሪያ ችግር የሌለበት ለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ
4. ሰሌዳና ሊብሬዉን በመዝጋቢዉ አካል በሲስተም መዝግቦ መረከብ እና ማረጋገጫ መስጠት
5. የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ሰሌዳ መረከብና ማስወገድ እንዲሁም ሊብሬው ተሰርዞ ፋይል ማድረግ
6. ባለንብረቱ አገልግሎት ለማግኘት እንደገና ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ ሰሌዳዉ በቁጥሩ እንዲታተም ለሰሌዳ ምርት ክፍል በደብዳቤ መላክ
7. ከሁለት አመት በፊት ቀድሞ እና ከ አምስት አመት በኋላ የሰሌዳ ይመለስልኝ ጥያቄ ማቅረብ አይችልም
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 በተደነገገው ጊዜ ገደብ ባለንብረቱ ወይም ባለ ይዞታው የሰሌዳ ይመለስልኝ ጥያቄ ሲያቀርብ የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም ሰሌዳ እንዲያገኝ የድጋፍ ደብዳቤ ይሰጠዋል፡፡
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ(1-8) የተደነገጉት ቢኖሩም ተሽከርካሪ ከአገልግሎት ውጭ ሆኖ ሰሌዳ መልሶ የነበረ ተገልጋይ እንደገና አገልግሎት ይሰጠኝ ጥያቄ ሊስተናገድ አይችልም

60. **ከክልል ወደ ክልል የሚዘዋወር የተሽከርካሪ ፋይል**

**ሀ. በማዛወሪያ ቅጽ ወደ ሌላ ቦታ የሚዛወር የተሽከርካሪ ፋይል**

1. የተሟላ ፋይል የሌላቸው ተሽከርካሪዎች የፋይል ዝዉዉር አይፈቀድም
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት መስፈርቶች ሲያሟሉ የተሽከርካሪ ፋይል ዝውውር ይፈቀዳል
3. የተሟላ የተሽከርካሪ መሰረታዊ ሰነዶች መኖሩን በማረጋገጥ
4. በማዛወሪያ ቅጹ ላይ የተመለከቱት ማስረጃዎች መሞላታቸውን በማረጋገጥ
5. የዘመኑን ቦሎ ማድረጉን በማረጋገጥ

6. ለኮድ-01 እና ኮድ-03 ከሆነ ቀኑ ያላለፈበት የማዛወሪያ ክሊራንስ ማቅረቡን ማረጋገጥ
7. የሚላኩ ሰነዶች ከዋናዉ ሰነድ ጋር እየተገናዘበ በባለሙያዉ እና በኃላፊ ፊርማና በእርጥብ ማህተም ሲረጋገጥ እና
8. በፋይል ማዘዋወሪያ ቅጽ ስርዝ ድልዝ የሌለዉና ክፍት ቦታው መዘጋቱን በማረጋገጥ አስፈላጊውን ክፍያዎች በማስከፈል ፋይሉ በፖስታ ቤት በኩል መላክ አለበት

## ለ. በማዛወሪያ ቅጽ ከሌላ ቦታ ተዛውሮ የሚመጣ የተሽከርካሪ ፋይል

1. ትክክለኛ ማዛወሪያ ቅጽ ተሟልተው በፖስታ ታሽገው መምጣቱን ማረጋገጥ
2. ተሽከርካሪው በአካል ቀርቦ በተሽከርካሪው ላይ ያለው ሻንሲና ሞተር ቁጥር በተላከዉ ሰነድ ውስጥ ከተገለፀው ጋር በማገናዘብ እና የተሽከርካሪው የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጥ
3. የፋይል ዝውውር ከተላከ ከ6 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መሆኑን እና በትክክለኛ አድራሻ መላለኩን ማረጋገጥ
4. በፋይል ማዘዋወሪያ ቅጽ ስርዝ ድልዝ የሌለዉና ክፍት ቦታው መዘጋቱን ማረጋገጥ
5. ሊብሬ፣ ቦሎና ሠሌዳ በመረከብ ከኢት ሰሌዳ በስተቀር አስፈላጊውን ክፍያ በማስከፈል አገልግሎቱን ይሰጣል
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ለ (ከ1-5) የተደነገጉት ሰነዶች ካልተሟሉና የአድራሻ ስህተት ካለ ፋይሉ ወደ መጣበት/ ፋይሉ ወዳለበት ክልል ወይም የምዝገባ ቦታ በፖስታ ቤት በ15 ቀናት ውስጥ ፋይሉን የመረመረው ባለሙያ ለኃላፊው በማሳወቅ ተመላሽ ማድረግ አለበት፡፡

ሐማሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትራንስፖርት ሚኒስቴር የትራንስፖርት ባለሥልጣን ቁ.1
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

# ክፍል አራት

## የተሽከርካሪ የአካልና የአገልግሎት ለውጥ ስታንዳርድና ምዝገባ

61. ከደረቅ ጭነት ወደ ሕዝብ ማመላለሻነት በሞዲፊክ የሚለወጥ የተሽከርካሪ የጭነት ልክ አወሳሰን

    1. ከ30 መቀመጫ በላይ ሆነው ጠቅላላ ክብደታቸው ከፍተኛ፣ የተሳፋሪ ክፍል ርዝመታቸው አነስተኛ ለሆኑ ተሽከርካሪዎች የመቀመጫ መጠን በተሳፋሪ ክፍል ርዝመት የመያዝ አቅም ተሰልቶ 1 ረድፍ በመቀነስ እንዲሰጥ ይደረጋል
    2. የተሳፋሪ ክፍል ርዝመት ከፍተኛ ሆኖ አነስተኛ ጠቅላላ ክብደት ላላቸው ተሽከርካሪዎች የመቀመጫ መጠን ከጠቅላላ ክብደቱ የአካል ለውጥ ተደርጎ የሚገኘው ነጠላ ክብደት ተቀንሶ በሚገኘው ውጤት መሰረት የመቀመጫ መጠን ይወስናል፡፡
    3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም በተሳፋሪ ክፍል ከፍተኛ ርዝመት ምክንያት በሚኖረው ክፍት ቦታ ተጨማሪ ወንበር እንዳይገጠም ከሚወስነው የመቀመጫ ብዛት ውጭ ያለው 400 ሚ.ሜ ያክል ከኋላ ተረፈ አካል ሲቀር ቀሪው ሻንሲ የርቆረጣል፡፡
    4. ከፍተኛ ጠቅላላ ክብደት ኖሯቸው በጣም አነስተኛ የሆነ የተሳፋሪ ክፍል ርዝመት ለሚኖራቸው የመቀመጫ መጠን አገልግሎት እንዲሰጠው ጥያቄ ሲያቀርብ አንድ ረድፍ ተቀንሶ ይሰጣል፡፡

62. ከደረቅ ጭነት ወደ ሕዝብ ማመላለሻነት የሚለወጥ ተሽከርካሪ በቅድመ ምርመራ ወቅት የሚታዩ መስፈርቶች

    1. ጠቅላላ ስፋት/width/ በአንድ ተርታ ስንት መቀመጫዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ፣
    2. የተሳፋሪ ክፍል ርዝመት /Deck length/ ሻንሲው ሳይቀጠል ስንት ረድፍ መያዝ እንዳለበት ፣

3. ጠቅላላ ርዝመት/Total length or over all length/ ሻንሲው ሳይቀጠል የተሠራ መሆኑን ፤
4. የፊት ተረፈ አካል/Front Over hang/ ከተሽከርካሪ ጠቅላላ ርዝመት 21% በላይ አለመሆኑን
5. የኋላ ተረፈ አካል/Rear Over hang/ ከጠቅላላ ርዝመቱ 30% አለመብለጥ እና
6. በአክስሎች መካከል ያለ ርቀት/Wheel base/ ከፋብሪካው ከነበረው ርቀት ሳይለወጥ መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መስፈርቶች ናቸው

63. የተሽከርካሪው የወንበር ስፔስፊኬሽንና መስፈርት

1. በወንበሮች /ፊትና ኋላ/ መካከል ያለ እርቀት 700 ሚ.ሜ፣
2. የወንበር ማሰሪያ ቦታ ውፍረት 30 ሚ.ሜ ይሆናሉ
3. የአንድ ሰው መቀመጫ 400 ሚ.ሜ ርዝመት እና 400 ሚ.ሜ ስፋት ታሳቢ በማድረግ ይሰራል
4. የመተላለፊያ (gang way) ስፋት 350 ሚ.ሜ

64. በአካል ለውጥ ጊዜ የጭነት /የተሳፋሪ ብዛት /አወሳሰን

1. አንድ ሰው በአማካይ 75 ኪሎግራም ይመዝናል በሚል የሚሠራበት ሲሆን መንገደኛው በተጨማሪም 25 ኪሎግራም የሚመዝን እቃ ይዞ የመጓዝ መብት ያለው በመሆኑ /75+25/ የአንድ ሰው 100 ኪ.ግ ግምት ተወስዶ የተሳፋሪ ብዛት ይወሰናል፡፡
2. ከጠቅላላ ክብደት ላይ ነጠላ ክብደት በመቀነስ የተሳፋሪ ብዛትን ለመወሰን፣
   - ከተሽከርካሪ ስፋት በመነሣት ተርታ የመቀመጫ ብዛትን መወሰን፡፡ይህም ለአንድ ሰው 400 ሚ.ሜ ታሳቢ በማድረግ፡-
   - የተሳፋሪ ክፍል ርዝመት በ730 ሚ.ሜ በማካፈል ስንት ተርታ እንደሚሆን ማወቅ (በሚቀጥለው አንቀጽ ቀመር መሰረት ይሰላል)፣

65. በሞደፊክ የሚሠሩ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የጭነት አወሳሰን

1. የመቀመጫ ረድፍ ብዛት፡-

የመቀመጫ ረድፍ ብዛት = የተሳፋሪ ክፍል ርዝመት /Deck length/

በወንበሮች መካከል ርቀት+የወንበር ማሰሪያ ቦታ ውፍረት

የመቀመጫ ረድፍ ብዛት=የተሳፋሪ ክፍል ርዝመት /Deck length/

700 ሚ.ሜ+30 ሚ.ሜ

| |
|---|
| የመቀመጫ ረድፍ ብዛት=የተሳፋሪ ክፍል ርዝመት/Deck length/ |
| 730 ሚ.ሜ |

2. አንድ ተርታ ያለ የመቀመጫ ብዛት =ጠቅላላስፋት - የመተላለፊያ ስፋት

ለአንድ መቀመጫ ርዝመት

| |
|---|
| በአንድ ተርታ ያለ የመቀመጫ ብዛት =ጠቅላላ ስፋት - 350 ሚ.ሜ |
| 400 ሚ.ሜ |

## 66. ወደ ህዝብ ማመላለሻነት ሊቀየሩ የሚችሉ የተሽከርካሪ ሞዴሎች

በሀገር ውስጥ ከደረቅ ጭነት ወደ ሕዝብ ማመላለሻነት በሞደፊክ ስራ በሚለወጡበት ወቅት የወንበር ስፋትና በወንበሮች መካከል ያለው ርቀት መስፈርቱን የጠበቀ እንዲሆንና ሻንሲ በመቀጠል የሚታየውን የጭነት አሰጣጥ ልዩነትን ለማስወገድ ባላቸው የተሳፋሪ ክፍል ርዝመትና ጠቅላላ ክብደት መጠን በቀመሩ መሰረት እየተሰላ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ተመሳሳይ ሞዴልና የተሳፋሪ ክፍል ርዝመት ላላቸው ተሽከርካሪዎች ተመሳሳይ የጭነት ልክ ተሰጥቷል፡፡የተሽከርካሪው ሞዴልና የተሳፋሪ ክፍል ርዝመቱ /Deck length/ ከዚህ በታች በተገለጸው መሠረት ከሆነ የተሳፋሪ ብዛት ለመወሰን የተቀመጠውን ሰንጠረዥ አባሪ 5 እና 6 ይመልከቱ ፡፡

- በአባሪው ውስጥ ከተዘረዘሩት የተሽከርካሪ ሞዴሎች ውጭ ሲያጋጥም በተቀመጠው የአካል ለውጥ መስፈርት መሰረት በባለስልጣኑ መ/ቤት እየታየ የሚፈቀድ ይሆናል፡፡

**ሀ. የተፈቀደውን የጭነት /የተሳፋሪ ብዛት ለመያዝ ሻንሲያቸው ከመጨረሻ የሚቆረጥ ተሽከርካሪዎች**

| ተ.ቁ | የተሽከርካሪ ስሪት | ሞዴል | የተሳፋሪ ክፍል እርዝመት በሚ.ሜ | መቆረጥ ያለበት መጠን በሚ.ሜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አይሱዙ | NPR58L | 4325 | 275 | ከኋላ ተረፈ አካል |
| 2 | ማርቸዲስ | OF1721 | 9750 | 590 | >>>>>> |

**ለ. የሚቆረጠው የሻንሲ ስሌት፡**

መቆረጥ ያለበት የኋላ ተረፈ አካል= የተሳፋሪ ክፍል ርዝመት ሲቀነስ /የረድፍ ብዛት x 730 ሚ.ሜ/+ 400 ሚ.ሜ/ ይሆናል

በአባሪ 5 እና 6 በተቀመጠው የተሳፋሪ የክፍል ርዝመት መስፈርት ማረጋገጥ መሠረት ሆኖ ሲገኝ ብቻ የተጠቀሰው የተሳፋሪ መጠን የሚሰጥ ይሆናል ከዚህ ውጭ ሆኖ ከቀረበ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ይህንንም የአሠራሩን ትክክለኛነት የሚያረጋግጡ ባለሙያዎች የተሽከርካሪው አካል ላሜራ ከመልበሱ በፊት ስለትክክለኝነቱ ሂደው በማየት ሳያረጋግጡ ላሜራ መልበስ አይችልም፡፡

**67. ወደ ህዝብ ማመላለሻነት ሊቀየሩ የማይችሉ የተሽከርካሪ ሞዴሎች**

1. የተሽከርካሪው ሞዴልና የተሳፋሪ ክፍል ርዝመት /Deck length/ በአባሪ 7 በተገለጸው መሠረት ከሆነ በሞደፊክ ወደ ሕዝብ ማመላለሻነት መቀየር አይችልም፡

ባማሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

2. የተሽከርካሪው ሞዴል ተመሳሳይ ሆኖ ተሳፋሪ ክፍል እርዝመቱ የሚለያይበት ጊዜ በመኖሩ ሻንሲ ሳይቀጠል የተወሰነውን ጭነት ሊይዙ የሚችሉ ሲኖሩ እንዳንዶቹ ደግሞ ሻንሲ ካልተቀጠለ በስተቀር ለሞዴሉ የተፈቀደውን ጭነት /ተሳፋሪብዛት / ሊይዙ ካልቻሉ የአካል ለውጥ አይፈቀድም፡፡

## 68. የአካልና የአገልግሎት ለውጥ ምዝገባ የሚያደርጉ ተሽከርካሪዎች የዕድሜ ገደብ

1. ከሌላ አገልግሎት ወደ ፈሳሽ ጭነት ለመቀየር የተሽከርካሪው እድሜ ከ 6 (ስድስት) ዓመት ያልበለጠ
2. ከሌላ አገልግሎት ወደ ህዝብ ማመላለሻ ለመቀየር የተሽከርካሪው እድሜ ከ 7 (ሰባት) ዓመት ያልበለጠ መሆን ይገባቸዋል፡፡

## 69. በአካል ለውጥ አሰራር ሂደት ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች እና መረጃዎች

1. ባለንብረቱ የተሽከርካሪው ፋይል በሚገኝበት ተቋም የአካል ለውጥ ጥያቄውን ያቀርባል
2. በጥያቄው መሰረት ፋይሉ የሚገኝበት ተቋም ተሽከርካሪው ወደ ተፈለገው አካል ለውጥ ለማድረግ በባለስልጣኑ በወጣው ስታንዳርድ መሰረት መሆኑን በማረጋገጥ ፣ ዕዳና ዕገዳ እንዲሁም ቀረጥ የሌሌበት መሆኑን ወይም ካለበት የስምምነት ደብዳቤ እንዲያቀርብ በማድረግ ፈቃዱን ወደ ሚሰጠው ወደ ክልል/ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ መላክ፡፡
3. የአካል ለውጥ ፈቃጁ የክልል/የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ የተላከለትን መረጃ መሰረት በማድረግ ፈቃድ ወደ ተሰጠው ጋራዥ የአካል ለውጡን እንዲያደርግ በመፍቀድ የአካል ለውጡ ከተደረገ በኋላ በባለሙያዎች ታይቶ የፈቃድ ደብዳቤ ይጽፋል
4. ባለጋራዡ ተሽከርካሪውን በመስፈርቱ መሠረት ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ ስራዉ ስለ መስራቱ በቅፁ ላይ ሞልቶ በፊርማው እና በማህተም አረጋግጦ ፋይሉ ወደ ሚገኝበት ተቋም ይልከዋል፡፡

70. የአካል ለውጥ ያደረገ ተሽከርካሪ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልጉ ሰነዶች፣

1. የአካል ለውጥ የፈቃድ ደብዳቤ
2. በእርጥብ ማህተም የተረጋገጠ የባለጋራዡ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ኮፒ
3. በእርጥብ ማህተም የተረጋገጠ የታደሰ የአካል ለውጥ የብቃት ማረጋገጫ ኮፒ
4. አካል ለውጡን ያሰራበት ደረሰኝ፣
5. የመዝጋቢ ተቋሙ ቴክኒሻኖች የተሰራውን የአካል ለውጥ ስራ በስታንዳርዱ መሰረት ለተጠየቀው አገልግሎት ብቁ መሆኑን በማረጋገጥ የአገልግሎት ክፍያ አካል ለውጡን ያሰራበት ደረሰኝ 2% በማስከፈል አገልግሎቱን መስጠት፡፡

71. ከተቋም ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው ለውጥ የሚያደርጉ አገልግሎቶች

ሀ. የጭነት ተሽከርካሪ የጋቢና ለውጥ

ተሽከርካሪ ጋቢናው አደጋ በደረሰበት ወቅት ጋቢናውን በተሻለ ለመተካት፣

1. የተሽከርካሪው ጋቢና ከቀድሞ ጋር የተመሳሳይ ሞዴል ተሽከርካሪ ጋቢና ከሆነ፣
2. የጋራዥ የታደሰ የንግድ ፈቃዱን ኮፒ በእርጥብ ማህተም የተረጋገጠ፣
3. የታደሰ የጋራዥ የብቃት ማረጋገጫ ኮፒ በእርጥብ ማህተም የተረጋገጠ፣
4. የተቋሙ ቴክኒሺያኖች የተገጠመለት ጋቢና ለተጠየቀው አገልግሎት ብቁ መሆኑን በማረጋገጥ አገልግሎቱ ይሰጠዋል፡፡

ለ. የመስክ አውቶሞቢል እና የፒክ አፕ ተሽከርካሪ ጋቢና ለውጥ

የተሽከርካሪው አካል ላይ የሚገኝ የቻሲ ቁጥር አብዛኛዎቹ ላይ በተለጣፊ ታግ ላይ የሚፃፍ ሆኖ በጋቢናው ላይ በሪቬት ተያይዞ የሚገኝ ነው፡፡ይኸ ሪቬት በተለያዩ ምክንያቶች ከተገነጠለ ወይም ወድቆ ከጠፋ የሚሰጠው ትርጉም ጋቢናው ተለውጧል የሚል ይሆናል፣ ይህንን ችግር በሚከተለው አግባብ ይፈታል

1. የተሽከርካሪ ጋቢና ከቀድሞ ጋር የተመሳሳይ ሞዴል ተሽከርካሪ ጋቢና ከሆነ፣
2. የጋራዥ የታደሰ የንግድ ፈቃዱን ኮፒ በእርጥብ ማህተም የተረጋገጠ፣
3. የታደሰ የጋራዥ የብቃት ማረጋገጫ ኮፒ በእርጥብ ማህተም የተረጋገጠ፣
4. የተቋሙ ቴክኒሺያኖች የተገጠመለት ጋቢና ለተጠየቀው አገልግሎት ብቁ መሆኑን፣ በሻንሲው ላይ ምንም ዓይነት ቅጥል በሁለቱም አቅጣጫ /በግራና በቀኝ / በኩል የመበየድ ምልክት አለመኖሩ በቴክኒክ በማረጋገጥ አገልግሎቱ ይሰጠዋል፡

ሐ. በተሽከርካሪ ላይ ወንበር ጭኖ ስለመቅረብ

ያገለገለም ሆነ አዲስ ተሽከርካሪ የተሟላ ወንበር ሳይገጠምለት ለሕዝብ ማመላለሻ ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ ለሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲውል ለማድረግ፡

1. ለተሽከርካሪው ሞዴል የተቀመጠውን የወንበር መጠን መስፈርቱን ጠብቆ ወንበር በጋራዦች አሰርቶ ለምዝገባ ሲቀርብ እና
2. መርማሪ ቴክኒሽያኖች ተሽከርካሪው ላይ የተገጠመው ወንበር በመስፈርቱ መሠረት ለተጠየቀው አገልግሎት ብቁ መሆኑን በማረጋገጥ የምዝገባ አገልግሎት ይሰጠዋል፡፡

መ. ፓኔል ቫን/ግላስ ቫን እና ሚኒባስ ተሽከርካሪዎች

1. በዲክለሬሽን ላይ ለጭነት አገልግሎት ብቻ በሚል ተገልጾ የገባ ቫን ወይም ግማሽ ቫን ሚኒባስ ተሽከርካሪ ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ ወደ ህዝብ አገልገሎት ሚኒባስ ተሽከርካሪ ለሚቀይሩ በሀገር ውስጥ ብቃት ባላቸው ጋራዦች ለተጠየቀው አገልግሎት ብቁ አድርጎ ሲቀርብ የቴክኒክ ባለሙያዎች የተሽከርካሪዉን ብቃት በማረጋገጥ እና መረጃውን በማየት ተሽከርካሪው ለተጠየቀው አገልግሎት ብቁ ከሆነ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
2. በዲክለሬሽን ላይ ለህዝብ አገልግሎት ብቻ በሚል ተገልጾ የገባ ሚኒባስ ተሽከርካሪ ሀገር ውስጥከገባ በኋላ ወደጭነት አገልገሎት ሙሉ ፓኔል ቫን/ግላስ ቫን ወይም ግማሽ ቫን ለሚቀይሩ በሀገር ውስጥ ብቃት ባላቸው ጋራዦች ለተጠየቀው አገልግሎት ብቁ አድርጎ ሲቀርብ የቴክኒክ

ባለሙያዎች የተሽከርካሪዉን ብቃት በማረጋገጥ እና መረጃውን በማየት ተሽከርካሪው ለተጠየቀው አገልግሎት ብቁ ከሆነ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ መ (1- 2) የተጠቀሰዉ ተሽከርካሪ ወደ ኮድ 02 ለመቀየር ከተፈለገ ከጉምሩክ የቀረጥ ልዩነቱን ከፍሎ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
4. ሃገር ውስጥ የሚገጣጠም ሚኒባስ ተሽከርካሪ ከተገጣጠመ በኋላ ወደ ቫን ሚኒባስ ሲቀየር በቫን የታክስ አግባብ ይስተናገዳል፡፡

**ሠ. ከህዝብ/ውይይት/ ወደ ፒክ አፕ የአካል ለውጥ**

ከውይይት ወደፒክ አፕ የአካል ለውጥ ጥያቄ ሲቀርብ፡-

1. የጋራዥ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ኮፒ በእርጥብ ማህተም ሲረጋገጥ፣
2. የታደሰ የጋራዥ የብቃት ማረጋገጫ ኮፒ በእርጥብ ማህተም ሲረጋገጥ እና
3. የተቋሙ ቴክኒሺያኖች ለተጠየቀው አገልግሎት ብቁ መሆኑን በማረጋገጥ አገልግሎቱ ይሰጠዋል፡፡

**ረ. የተሽከርካሪ ቀለም ለውጥ**

የተሽከርካሪ ቀለም ለውጥ ማድረግ የተሽከርካሪውን መሰረታዊ አቋምና ይዘት የማይለውጥ በመሆኑም የተገልጋዩን ጊዜና ጉልበት የሚቆጥብ ለማድረግ

1. በተቋሙ ምዝገባ ያላደረገ አዲስም ሆነ ያገለገለ ተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ገዥ ለምዝገባ ከመቅረቡ አስቀድሞ ለሚፈለገው የአገልግሎት ዓይነት የሚያስፈልገውን የቀለም ዓይነት ያለ ቅድመ ፍቃድ ቀይሮ መቅረብ የሚቻል ሲሆን ለምዝገባ ሲቅርብ የቴክኒክ ብቃቱን በባለሙያዎች በማረጋገጥና የተሽከርካሪውን የቀለም አይነት በስፔስፊኬሽን ላይ በመግለፅ አገልግሎት ይሰጠዋል፡፡
2. በተቋሙ የተሽከርካሪ ምዝገባ አድርጎ የነበረ ባለንብረት ወይም ገዥ የተሽከርካሪውን ቀለም ለሚፈለገው አገልግሎት የሚያስፈልገውን ቀለም አስቀብቶ ለአገልግሎት ሲቀርብ የቴክኒክ ባለሙያዎች ስለ ቀለሙ ቅድመ

ፍቃድ ሳይጠይቁ የተሽከርካሪውን የቴክኒክ ብቃት በማረጋገጥ፤ቀለሙ በአግባቡ መቀባቱንና የተሽከርካሪውን የቀለም ዓይነት በስፔስፊኬሽን ላይ በማስፈር አገልግሎቱ ይሰጠዋል፡፡

## 72. የተሽከርካሪ የሞተር ለውጥ ፈቃድ ስለመስጠት

**የተሽከርካሪ የሞተር ለውጥ ጥያቄ አይነቶች**

1. ተመሳሳይ የነዳጅ አይነት ያለው ሞተር ለውጥ
2. ከቤንዚን ሞተር ወደ ናፍጣ ሞተር ለውጥ
3. ከናፍጣ ሞተር ወደ ቤንዚን ሞተር ለውጥ

## 73. የተሽከርካሪ የሞተር ለውጥ በሚደረግበት ወቅት በቴክኒክ መረጋገጥ ያለባቸው መስፈርቶች

ሀ. የቀድሞው እና አዲስ የሚገጠመው ሞተር:-

1. ተመሳሳይ የነዳጅ ዓይነት እንደሆኑ ማረጋገጥ
2. በተመሳሳይ ወይም (እስከ ±10 %) የፈረስ ጉልበት ልዩነት እንዳለቸው ማረጋገጥ
3. ተመሳሳይ ሞዴል መሆናቸውን ማረጋገጥወይም ከአምራቹ በአማራጭ የተቀመጠ መተኪያ ሞዴል መሆኑን ማረጋገጥ
4. በተመሳሳይ ወይም (እስከ ±10 %) የሲሲ መጠን ልዩነት እንዳላቸው ማረጋገጥ
5. በተመሳሳይ ወይም (እስከ ±10 %) የሞተር ዙር ፍጥነት /RPM/ ልዩነት እንዳላቸው መሆን አለባቸው
6. በአምራች ድርጅቱ ሞዴል አቅጣጫ (Recommendation) መሠረት በአማራጭ መቀየር ይቻላል

**ለ. የተለያዩ የነዳጅ ዓይነት ከሆኑም**

1. ተመሳሳይ የፈረስ ጉልበት ወይም (እስከ ±10 %) ልዩነት እንዳላቸው ማረጋገጥ

2. ተመሳሳይ የሲሲ መጠን ወይም (እስከ ±10 %) ልዩነት እንዳላቸው ማረጋገጥ
3. ተመሳሳይ የሞተር ዙር /RPM/ ወይም (እስከ ±10 %) ልዩነት እንዳላቸው በማረጋገጥ የፈቃድ አገልግሎት ይሰጣል

74. ለሞተር ለውጥ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እና ፈቃድ አሰጣጥ

ሀ. ሞተሩ የተገዛው ከአስመጭ ድርጅት ከሆነ

1. የሞተሩን ኦሪጅናል ዲክለሬሽን ሲቀርብ
2. ዋና ደረሰኝ/ኦሪጅናል ኢንቮይስ/ ሲቀርብ
3. ሞተሮቹ በአንድ ዲክለሬሽን ላይ የተመዘገቡ ከሆነ የዲክለሬሽን ቁጥር የተፃፈበት የሞተሮች (ሲሊንደር ብሎክ) ዝርዝር ከዲክለሬሽኑ ጋር ሲቀርብ እና
4. የሞተሩን ዋጋ የቴምብር ቀረጥ 2% እና የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል አገልግሎቱ ይሰጣል

ለ. ሞተሩ ከካምፓኒዎች የተገዛ ከሆነ

1. የተሟላ ዲክለሬሽን ሲቀርብ
2. ዋና ደረሰኝ /ኦሪጅናልኢንቮይስ/ ሲቀርብ እና
3. የሞተሩን ዋጋ የቴምብር ቀረጥ 2% እና የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል አገልግሎቱ ይሰጣል

ሐ. ሞተሩ ከተሽከርካሪ ላይ የወረደ ከሆነ

1. ሞተሩ ሠሌዳና ሊብሬ ከመለሰ ባለንብረት የተገዛ ከሆነ የተሽከርካሪው ሠሌዳና ሊብሬ የተመለሰበት ማስረጃ ኮፒ
2. በውልና ማስረጃ የጸደቀ ሞተሩ የተሸጠበት ማስረጃ
3. የሞተሩ ዋጋ ካልተገለጸ ከፋይል ወይም ከተመሳሳይ ሞዴልና የምርት ዘመን በመጠቀም ከተሽከርካሪው ዋጋ ላይ 25% በመውሰድ የሞተሩን የዋጋ ግምት የቴምብር ቀረጥ 2 % ክፍያ ማስከፈል

4. የግምት ውጤቱን ለመወሰን በተዋዋዮች የቀረበውን ዋጋ እና ተሽከርካሪው ተገምቶ የተገኘውን የ25% የሞተሩን የዋጋ ግምት በማወዳዳር የበለጠውን ዋጋ የመጨረሻ የግምት ውጤት በመውሰድ ያቀረቡት ውል እንዲፀድቅ ግምቱን በሸኝ ደብዳቤ ለሰነዶች ማረጋጋጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ይላካል፡፡
5. ግለሰቡ/ተቋሙ ከእራሱ ተሽከርካሪ ወደ ሌላኛው ተሽከርካሪ የሞተር ለውጥ ያደረገ ከሆነ ከሞተር ለውጥ ፈቃጁ ትራንስፖርት ተቋም የሞተር ለውጥ ፈቃድ እና የተቀየረበት የተሟላ ሰነድ ተያይዞ መቅረብ አለበት

መ. ሞተሩ ከተለያዩ ድርጅቶች በጨረታ የተገዛ ከሆነ

1. ለሌላ ወገን አሳልፎ መሸጥ ከፈለገ የሽያጭ ውል በማቅረብ የጨረታ ዋጋውን እንደ መነሻ በመውሰድና በውል ላይ ከቀረበው ዋጋ ጋር በማነፃፀር የበለጠውን ዋጋ የሞተር ግምት በመስራት ውሉ በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት እንዲያፀድቅ ያደርጋል፡፡
2. ሞተሩን በጨረታ የገዛው ባለንብረት በራሱ ተሽከርካሪ ላይ መግጠም ከፈለገ ሞተሩን ጭኖ ሲቀርብ በቴክኒክ ተረጋግጦ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡
3. ባለንብረቱ አዲስ ወይም ያገለገለ ሞተር በተሽከርካሪ ላይ አስገጥሞ ሲቀርብ መስፈርቶች መሟላታቸውን፣ የቴክኒክ ብቃቱንና የተሟላ መረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ ለተገልጋዩ አገልግሎቱ ይሰጠዋል፡፡
4. አዲሱ የሚቀየረዉ ሞተር የሞተር ቁጥር የሌለው ከሆነ እና የቁጥር መፃፊያ መደቡ ያልተፋቀ መሆኑን የቴክኒክ ባለሙያዎች ካረጋገጡ የሞተር ቁጥሩ ባዶ ተብሎ በስፔስፊኬሽን ላይ አስተያየት ይፅፋል፡፡
5. በስፔስፊኬሽን ላይ ያለውን አስተያየት በሊብሬው ላይ የሞተር ቁጥር ባዶ (ያልተፃፈ) ብሎ በመፃፍ የሞተር ቁጥር ሳይመታ ባለበት ሁኔታ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
6. የአስመጪው የንግድ ፈቃድ በራሱ ማህተም የተረጋገጠ ኮፒ ከሸጠው ሞተር ሰነድ ጋር አብሮ ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

ማሳሳቢያ፡-ፋይሉ በሚገኝበት ተቋም የሞተር ለውጥ ጥያቄ ሲቀርብ ፋይሉ የሚገኝ በት ተቋም እዳና እግድ የሌለበት መሆኑን በማረጋገጥ ለዋና መምሪያው ሲልክ የሞተር ለውጥ ፈቃዱ በክልሉ/በከተማ አስተዳደሩ የትራንስፖርት ቢሮ ባለሙያዎች ታይቶ ፈቃድ ይሰጣል

## 75. የተሽከርካሪ የሻንሲ ለውጥ ፈቃድ

1. የሻንሲ ለውጥ ጥያቄ ከተገልጋይ ሲቀርብ በተሽከርካሪው ላይ የሚገኘው ሻንሲ ለቀጣይ አገልግሎት መስጠት የማይችል መሆኑ በባለስልጣኑ በኩል በቴክኒክ ከተረጋገጠ አዲስም ሆነ ያገለገለ ሻንሲ ጋር ተመሳሳይ ስሪትና ሞዴል የሆነ ሻንሲ ብቻ መለወጥ ይቻላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ስለህጋዊነታቸው ሊከናወን የሚገባውና መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

   ሀ. ለሞተር ለውጥ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት የሚፈጸም ሲሆን የተለወጠው የሻንሲ ቁጥር ሻንሲዉ በተገጠመለት ተሽከርካሪ ሊብሬ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡

   ለ. ያለ ትራንስፖርት ጽ/ቤቱ (የክልልና የከተማ አስተዳደር) ፈቃድ የሻንሲ ቁጥርን በማስመሰል መምታት አይቻልም

   ሐ. የሻንሲ ቁጥር መፃፊያ ቦታ የተሞረደ ወይም የተፋቀ ሊሆን አይችልም፡፡

## 76. የተሽከርካሪ ሻንሲ እና ሞተር ቁጥር ስለ ማስመታት

ሀ. የአንድ ተሽከርካሪ መለያ ቁጥሮች /VIN/ ተመታ የሚባለው በተሽከርካሪው የሞተር ቁጥር መደብ ላይና በቻሲው ቁጥር መደብ ላይ የተደረደሩት ቁጥሮች ከፋብርካው ሥሪት አንፃር ሲታይ፣

1. የቁጥሮቹ አመታት ቀጥታ ረድፋን ያልተከተሉ እና ወጣ ገባ ሆነው ሲገኙ፣
2. የቁጥሩ አመታት ወይም አደራደሩ ከመሰል ሞዴል ተሽከርካሪዎች የተለየየ ቁጥሩ አደራደር ሲያጋጥም፣
3. በሞተርና ሻንሲ የቁጥር መደብ ላይ የሚደረደሩት ቁጥሮች ጥልቀት ወጥነት የሌለው ከሆነ፣

4. የሞተርና የሻንሲ ቁጥር መፃፊያ መደብ የተፋቀ እና የቀድሞው ወይም በሊብሬው ላይ ያሉት ቁጥሮች በዚህ መደብ ላይ ተመተው ወይም ተፅፈው የሚገኙ ከሆነ፣
5. የአንዳንድ የተሽከርካሪ ሞደሎች የሞተርና የሻንሲ ቁጥሮች በተላጣፊ ታግ ላይ ተፅፈው በሪቬት አማካኝነት በሞተሩ ወይም በሻንሲው ላይ ተያይዘው የሚገኙ እና እነዚህን ተለጣፊ ታጎች የሚያያይዘው ሪቬት ተነቅሎ የተገኘ ከሆነ፣

ከላይ ከ‹‹1››እስከ ‹‹5›› የተገለፁት ሁኔታዎች በተሽከርካሪው ሞተርና ሻንሲ ላይ ከተከሰቱ ቁጥሮቹን በማስመሰል የተመታ ወይም የተሽከርካሪው ሻንሲ ወይም ሞተር ያለፈቃድ ለውጥ ተደርጎበታል የሚል ትርጉም ሊያሰጠው ይችላል፡፡

ለ. ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች የተሽከርካሪ መለያ ቁጥሮች/VIN/ በማስመሰል ተመተው ወይም ሞተርና ሻንሲያቸው ያለፈቃድ ተለውጠው ሊገኝ ይችላል፡፡

1. ያገለገለ ተሽከርካሪ ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ ምዝገባ ከማድረጉ በፊት የሞተርና የሻንሲ ቁጥሮች መመታት ሊያጋጥም ይችላል፡፡
2. በተቋሙ ምዝገባ ተደርጎለት ሠሌዳና ሊብሬ ያለው ተሽከርካሪ በተለያዩ ምክንያቶች በቴክኒክ ምርመራ ወቅት የሞተር ወይም የሻንሲ ቁጥር ወይም ሁለቱም ተመተው ሊገኝ ይችላል፡፡
3. የመንግስት መ/ቤቶች እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተሽከርካሪ በጨረታ ሽያጭ አካሂደዉ ለግለሰቦች ስም ዝዉዉር በሚደረግበት ወቅት የሞተር ወይም የሻንሲ ቁጥሮች በማስመሰል ተመተው ወይም ያለፍቃድ ተቀይሮ መገኘት የመሳሰሉት የችግሮቹ ዋና ዋና ምንጮች ናቸው፡፡

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ለ (1 - 3) ድረስ በተጠቀሱት ምክንያቶች በምዝገባ እና በስም ዝውውር ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በሚከተለው መልኩ ይፈታሉ፡፡

1. መስፈርቱን አሟልቶ ሀገር ውስጥ የገባ ያገለገለ ተሽከርካሪ የሻንሲ ወይም የሞተር ቁጥር የተመታ ለመሆኑ በጉምሩክ ጣቢያ በሚገኙ የትራንስፖርት ባለስልጣን የቴክኒክ ባለሙያዎች የቴክኒክ መመርመሪያ /ሮዝ ወረቀት/ ላይ የተመታ መሆኑ ተጠቅሶ ለመጀመሪያ ጊዜ በመዝጋቢ ተቋሙ ቀርቦ የምዝገባ አገልግሎት ሲጠይቅ የሞተር ወይም የሻንሲ ቁጥር የተመታ መሆኑ በቴክኒክ ባለሙያ ከተረጋገጠ የተመታው እንዳለ በስፔስፊኬሽን ላይ



ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

ተጠቅሶ የምዝገባ ሠራተኛው የሞተር ወይም የሻንሲው ቁጥር የተመታ መሆኑን በሊብሬው ላይ ማብራሪያ በመፃፍ ባለበት ሁኔታ በመደበኛ ሠሌዳ አገልግሎት ያገኛል፡፡

2. ያገለገለ ተሽከርካሪ የሞተር ወይም የሻንሲ ቁጥር በጉምሩክ የትራንስፖርት ባለስልጣን የቴክኒክ ብቃት አረጋጋጫ ባለሙያዎች የተመታ መሆኑ ካልተጠቀሰ እና ለመጀመሪያ ጊዜ በቴክኒክ ሲመረመር የሻንሲ ወይም የሞተር ቁጥሩ የተመታ መሆኑ ከተረጋገጠ ባለንብረቱ መሸጥ መለወጥ አለመቻሉን ግዴታ አስገብቶ ቀይ ምልክት ያለው ሠሌዳ በመስጠት የምዝገባ አገልግሎት ያገኛል፡፡

3. በባለስልጣኑ ምዝገባ ያላደረገ የመከላከያ እና የፖሊስ ተሽከርካሪ በጨረታ ተሸጦ የስም ዝዉዉር አገልግሎት ሲጠይቅ የሞተር ወይም የሻንሲ ቁጥር መመታቱ በተቋሙ ቀርቦ በቴክኒክ ሲረጋገጥ የምዝገባ ሠራተኛው የሻንሲ ቁጥር መመታቱን በሊብሬው ላይ በመፃፍ ባለንብረቱ መሸጥ መለወጥ አለመቻሉን ግዴታ አስገብቶ ቀይ ምልክት ያለው ሠሌዳ በመስጠት የምዝገባና የስም ዝውውር አገልግሎት ያገኛል፡

4. በተቋሙ ምዝገባ አድርጎ ሠሌዳና ሊብሬ ያለው የመንግስት ተሽከርካሪ በጨረታ ሲሸጥ፣ በባንክ በጨረታ የሚሸጥ እና በፍርድ አፈፃፀም ፍርድ ቤት በጨረታ የሚሸጠው ተሽከርካሪ በስም ዝውውር ወቅት የሻንሲና የሞተር ቁጥር መመታት በቴክኒክ ከተረጋገጠ የምዝገባ ሠራተኛው የሻንሲ ቁጥር መመታቱን በሊብሬው ላይ በመፃፍ ባለንብረቱ መሸጥ መለወጥ አለመቻሉን ግዴታ አስገብቶ ቀይ ምልክት ያለው ሠሌዳ በመስጠት የምዝገባና የስም ዝውውር አገልግሎት ያገኛል፡

## 77. የሻንሲና የሞተር ቁጥር ማስመቻ ፈቃድ

የተሽከርካሪ መለያ ቁጥሮች (VIN) በተለያዩ ምክንያቶች ሊደበዝዙ እና ለንባብ አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ የሻንሲ ቁጥር ማስመቻ ፈቃድ ሊያስፈልግ ይችላል፡

1. የሻንሲና የሞተር ቁጥር በዝገት ምክንያት መበላት ችግር ሲያጋጥም

- አዲስም ሆነ ያገለገለ ምንም ምዝገባ ያላደረገ እና ሠሌዳ ያልተሰጠው ተሽከርካሪ በባለስልጣን የቴክኒክ ብቃት አረጋጋጫ ባለሙያዎች በሚሰጡት ሙያዊ ማብራሪያ መሠረት በዝገት ምክንያት ከ50% በላይ ቁጥሮቹ መበላታቸዉ ከተረጋገጠ የማስመታት ፍቃድ በመዉሰድ እንዲያስመታ ይደረጋል፡፡

2. የሻንሲ ቁጥር በተለያዩ አደጋዎች በቁጥሩ እና በአቅራቢያው ላይ ሊደርሱ በሚችሉ ጉዳቶች ምክንያት በሚደረግ ጥገና ቁጥሩ ላይነበብ ስለሚችል
   - የሻንሲ የቁጥር መደብ አካባቢ በአገልግሎት ብዛት፣ከጭነት ልክ በላይ በመጫን እና በተለያዩ አደጋዎች ምክንያት ጉዳት ከደረሰበት እና ከተሰነጠቀና ከተቆረጠ ከመጠገኑ በፊት ባለንብረቱ የተሽከርካሪውን ጉዳት በቴክኒክ አሳይቶ የጥገና ፈቃድ ማግኘትና ማስጠገን አለበት፡፡
3. የሞተር እና የሻንሲ ቁጥሮች ከስሪታቸው በተለጣፊ ታግ ላይ ተጽፈው የተለጠፉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
   - የሞተርና የሻንሲ ቁጥር በተለጣፊ ታግ ላይ የሚገኙ ከሆነ እና ችግር ካጋጠማቸው የቴክኒክ ባለሙያዎች የሪፔቱ ሁኔታ የተሽከርካሪው መሆኑንና አለመሆኑን በማረጋገጥ የሻንሲ ማስመቻ ፈቃድ ተሰጥቶት ማስመታት አለበት፡፡

## 78. የተሽከርካሪ ሻንሲ ለውጥ እና የሻንሲ ጥገና ፈቃድ

ሀ. የተሽከርካሪ ሻንሲ በአገልግሎት የዕድሜ ብዛት፣ ከጭነት ልክ በላይ በመጫንና በአደጋ ምክንያት የሻንሲ መሰንጠቅ ወይም መቆረጥ ሊያጋጥም ይችላል፡፡

1. ሻንሲው ችግር የደረሰበት መለያ ቁጥሮቹ በሚገኙበት አካባቢ ከሆነና ጥገናው ቁጥሮቹን የሚነካ ከሆነ ጥገና ከመደረጉ በፊት ከፈቃድ ሰጪው አካል ፈቃድ ማግኘት ይጠበቅበታል፡፡

2. የሻንሲ ለውጥ ተመሣሣይነት ካለዉ የተሽከርካሪ ሞዴል በቴክኒክ ተረጋግጦ የሚለወጥ ይሆናል

3. የሻንሲ አካል ለውጥ የሚደረገው በባለስልጣኑ የሻንሲ አካል ለመለወጥ ፈቃድ በተሰጠው ተቋም መሆኑ ይኖርበታል
4. የሻንሲ ቁጥር የሌለው ከነበረ በባለስልጣኑ የሻንሲ ቁጥር መምቻ ፈቃድ በተሰጠው ተቋም መሆን ይኖርበታል
5. የሻንሲ ቁጥር እንዲመታ ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ሰነዶቹን በእርጥብ ማህተም አረጋግጦ ከብቃት ፈቃዱ ኮፒ ጋር ማቅረብ አለበት
6. ሻንሲው የሚለወጥ ከሆነ ሻንሲው የተገዛበት ህጋዊ ሰነዶች መሟላት አለባቸው
7. ሻንሲው የሚቀየር ከሆነ ከባለስልጣኑ ፈቃድ የተሠጠበት ማስረጃ
8. ሻንሲው በጥገና የሚስተካከል ከሆነ በአገልግሎት መስጫ ተቋሙ ፈቃዱን ያገኛል

ለ. የሻንሲ ለውጥ አድርጎ የመጣ ተገልጋይ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ሰነዶች፡-

1. የሻንሲ ቁጥር እንዲመታ ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ሰነዶቹን በእርጥብ ማህተም አረጋግጦ ከብቃት ፈቃዱ ኮፒ ጋር ማቅረብ አለበት
2. ሻንሲው የሚለወጥ ከሆነ ሻንሲው የተገዛበት ህጋዊ ሰነዶች መሟላት አለባቸው
3. ሻንሲው የሚቀየር ከሆነ ከባለስልጣኑ ፈቃድ የተሰጠበት ማስረጃ

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

# ክፍል አምስት

## የተሽከርካሪ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ /ቦሎ/

79. **የዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ አስፈላጊነት፡-**

1. ተሽከርካሪው በተመዘገበበት የአገልግሎት ሁኔታ መንቀሳቀስ መቻሉን
2. የቴክኒክ ብቃቱ አስተማማኝ እና አደጋ የማያደርስ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን
3. ማንኛውም ተሽከርካሪው በተመዘገበበት ስፍራ ወይም ክልል ዓመታዊውን የቴክኒክ ምርመራ በዓመት አንድ ጊዜ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

80. **ተሽከርካሪው ቦሎ ለመውሰድ የማያስችሉ ሁኔታዎች**

1. የባለንብረትነት የምስክር ወረቀት ላይ የሚሞሉ ዝርዝር ሁኔታዎች አጣራጣሪ ና በግልጽ የማይነበቡ ከሆነ፣
2. የሞተርና የሻንሲ ቁጥር ወይም የባለንብረቱ ስምና አድራሻ ላይ ቀድሞ በፋይሉ ከተመዘገበው ልዩነት ሲኖር እና
3. ተሽከርካሪው ዓመታዊ ምርመራ የተደረገበትን ጊዜ ያላፈ ከሆነ አገልግሎት አያገኝም
4. በየትኛው ምክንያት የተሽከርካሪው ደረቅ ፋይል በሌለበት ሁኔታ የቦሎም ሆነ ሌላ አገልግሎት መስጠት አይቻልም

81. **የቦሎአሰጣጥ በተሽከርካሪ የአገልግሎት አይነት**

1. ኮድ 02 የቤት ተሽከርካሪ የቤት ቦሎ ይሰጣል
2. ኮድ 01/03 የንግድ ተሽከርካሪ የንግድ ቦሎ ይሰጣል
3. ኮድ 03 የግል ንግድ ተሽከርካሪ የግል ንግድ ቦሎ ይሰጣል
4. ኮድ 04 የመንግስት ተሽከርካሪ የመንግስት ቦሎ ይሰጣል
5. ኮድ ፖሊስ የመንግስት ተሽከርካሪ የፖሊስ ቦሎ
6. ሌሎች ተሽከርካሪዎች ሌሎች ቦሎ (CD, AU, UN, ኮድ 05, ዕድ, ልዩ, እንዲሁም ሌሎች የእርድታና ማህበራት ድርጅቶች) ቦሎ ይሰጣቸዋል

82. ለዓመታዊ የተሽከርካሪ ምዝገባ /ቦሎ/ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ሠነዶች

1. የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/
2. የምርመራ ሰርተፊኬት የቆይታ ጊዜ ተሽከርካሪው ከተመረመረበት ቀን ጀምሮ ቦሎ ለመውሰድ ለኢ.ት ሰሌዳ 30 ቀን ለሌሎች ክልል ወይም ከተማ መስተዳድሮች 20 ቀን ያላለፈዉ
3. የመርማሪ ቴክኒሻኖች ስም፤ የፊርማ ናሙና እና የትምህርት መረጃ ሲስተም ዉስጥ የተመዘገበ መሆኑ
4. አመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ በሚካሄድበት ወቅት የምርመራ ተቋሙ ሁለት ቴክኒሽያኖችን እና የተቋም ኃላፊ መፈረማቸው
5. ተሽከርካሪው ወደ ምርመራ ቦታ መጥቶ የተመረመረ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የተሽከርካሪዉን ሰሌዳ በግልጽ የሚያሳይ ምስል ፕሪንት አውት ላይ ፎቶግራፍ ከሚነበብ ሰሌዳ ጋር መኖሩ
6. ለግል ንግድ በንግድ ፈቃዱ ስም፤ ለንግድ በተሽከርካሪው ሰሌዳ፣ የሻንሲና የሞተር ቁጥር የተገለጸ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ወይም የግብር ክሊራንስ መኖር
7. የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ የገባበት ዉል መኖሩን
8. የመንገድ ፈንድ ክፍያ የከፈለበት ደረሰኝ ኮፒ መኖሩን እና
9. የቴክኒክ ምርመራ ባለፈው ዓመት ምርመራ ካላደረገ የቅጣት ጨምሮ የዘመኑ ቦሎ ክፍያ ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎችን መክፈሉ ተረጋግጦ ቦሎ ይሰጣል
10. ማንኛውም ግለሰብ ከላይ የተጠቀሱትን ሰነዶች እና ማንነቱን የሚገልጽ የመታወቂያ ኮፒ ሲያቀርብ ይስተናገዳል፡፡

ከማሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 83. የስም ዝውውር ወይም የባለቤትነት መብት የሚተላለፍባቸው ህጋዊ መንገዶች

1. ሽያጭ
2. ስጦታ
3. በመለዋወጥ
4. ውርስ /በኑዛዜ/ ያለኑዛዜ
5. በፍርድ ቤት ውሳኔ በሐራጅ/ያለ ሀራጅ ሽያጭ
6. በባንክ በሀራጅ ሲሸጥ
7. ባንኮች በዋስትና የያዙትን ወደራሳቸው ስም ሲያዞሩ

ከላይ የተገለጹት የስም ዝውውሮች በሙሉ 2% የቴምብር ቀረጥና የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላሉ፡፡

### 84. በሽያጭ ስም የሚዞርበት ሁኔታ

**ሀ. ሽያጩ በሰዎች መካከል ሲሆን ውሉ ማሟላት ያለበት፣**

1. የሽያጭ ስምምነት የተፈጸመበት ሰነድ በተለምዶ የመንደር ውል የሚባለው አፃፃፍ ፎርም
2. የሻጭና የገዥ ሙሉ ስም ከነአድራሻቸው፣
3. ተወካይ የሚሸጥ ከሆነ በውክልና ስልጣን እንደሚሸጥ መጠቀስ ይኖርበታል፣
4. የተሽከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር /የሻንሲቁጥር፣የሞተርቁጥር/የተጠቀሰበት መሆኑ
5. የተሻሻጡበት ገንዘብ መጠን፣
6. ቢያንስ በሁለት ምስክሮች መኖርና መፈረም ይኖርባቸዋል፣
7. ውሉ የተፈፀመበት ቀን፣

**ለ. ሁለት የህግ ሰውነት ባላቸው ሰዎች/በድርጅቶች/ መካከል የሚፈጸም ሽያጭ**

1. ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ(3,4,5,6) በተጨማሪ የሻጭ ስም የድርጅቱ ስም /መኪናው የተመዘገበበት ስም/ ይሆናል የገዥ ስም የሚገዛው ድርጅት መሆን
2. በመጨረሻ ድርጅቱን ወክሎ የሸጠው ሙሉ ስም ከነስራ ድርሻው እና የመሸጥ መብት የሚገልጽ ማስረጃ ማያያዝ

3. እንዲሁም ድርጅቱን ወክሎ የገዛው ሙሉ ስም ከነስራ ድርሻውእና የመግዛት መብት የሚገልጽ ማስረጃ ማያያዝ እና
4. የሻጭና የገዥ ድርጅት ፊርማ ባለበት የድርጅቱ ማህተም መኖር አለበት፣
5. የሽያጭ ውሉ በውልና ማስረጃ መጽደቅ አለበት በህግ ሰውነት በተሰጠውና በተፈጥሮ ሰው መካከል በሚደረግ መሻሻጥ አንዱ ካንዱ ሲገዛም ሆነ ሲሻሻጡ ተመሳሳይ ሁኔታ ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ (1,2,3,4) እንዳለ ሆኖ የተፈጥሮ ሰው የሆነው ማህተም አይጠየቅም፡፡

## 85. በስጦታ ስም የሚዞርበት ሁኔታ

1. ስጦታው በሰዎች መካከል ሲከናወን ከላይ በአንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ ሀ5 ከተገለጸው በስተቀር ሌሎቹ መሟላት አለባቸው፡፡
2. ስጦታው የህግ ሰውነት በተሰጣቸው አካላት ሲከናወን በተመሳሳይ ሁኔታ ከላይ በአንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ ሀ ስር የተዘረዘሩትን ማሟላት ሲኖርበት እንደ ሽያጭ ግን የገንዘብ መጠን እንዲገልጹ አይገደዱም፡፡
3. በተፈጥሮ ሰውና በህግ ሰውነት በተሰጣቸው መካከል የሚፈጸም ስጦታ ልክ እንደ ሽያጭ ተመሳሳይ ፎርም የሚከተል ሆኖ የገንዘብ መጠን ብቻ እንዲገልጹ አይገደዱም፡፡

## 86. ተሽከርካሪ በመለዋወጥ ስም የሚዞርበት ሁኔታ

ተሽከርካሪ በተሽከርካሪ በመለዋወጥ የሚደረግ የስም ዝውውር ልክ እንደ ሽያጭና ስጦታ በተመሳሳይ መንገድ የሚታይ ነው በዚህም ላይ የገንዘብ መጠን እንዲገልጹ አይገደዱም፣

## 87. በውርስ ወይም በኑዛዜ ስም የሚዞርበት ሁኔታ

በውርስ ወይም በኑዛዜ የሚደረግ የመብት መተላለፍ ውርሱ ወይም ኑዛዜው በፍርድ ቤት ውሳኔ አግኝቶና ፀንቶ መምጣት አለበት፡፡

1. የባልነት ወይም የሚስትነት ማረጋገጫ የፍ/ቤት ውሳኔ ይዞ የሚመጣ ሰው በተሽከርካሪው ላይ የሚኖረው መብት ግማሽ በመሆኑ ቀሪው ለግማሹ ሌላ ህጋዊ ወራሽ እንጂ ወደ ባለ ግማሹ መብት ላለው ሰው አይዞርም፡፡
2. በፍርድ ቤት የወራሽነት ማረጋገጫ ውሳኔ ከውርስ ንብረት ማጣራት ሪፖርት ጋር መቅረብ አለበት

## 88. ወራሽነት ያለኑዛዜ

1. ያለኑዛዜ ወራሽ የሆኑ የሟች ዝምድና ያላቸው በፍ/ቤት አስወስነው በሚያመጡት የወራሽነት ውሳኔ ላይ ከውርስ ንብረት ማጣራት ሪፖርት ጋር መቅረብ አለበት
2. ባል ሚስቱን ሚስት ባሏን አትወርስም (ምክንያቱም የንብረት ባለድርሻ ስለሆኑ)
3. ብዙ ወራሾች ከሆኑ ውርሱ በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ በተገለጸው የወራሾች ስም ዝርዝር መሰረት ይመዘገባል፡፡
4. አውራሽ መኪናውን ገዝተው ወደ ስማቸው ሳይዞር ቢሞቱ ውሉ ሰነድን የማረጋገጥ ስልጣን ባለው አካል በተተኪዎች ስም ሲረጋገጥ በሟች እግር ተተክተው መኪናውን እንደገዙ ተቆጥሮ መኪናው ከሻጭ ወደ ወራሾች ስም ይመዘገባል፡፡
5. የስም ዝውውር ተደርጎ የባለቤትነት ደብተር ከተሰጠ በኋላ ሌላ ወራሽነት ቢመጣ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር አይስተናገዱም፡
6. የጋራ ተሽከርካሪውን ባለመብት ያላቸው ድርሻቸውን ለመሸጥ ከፈለጉ ባላቸው ድርሻ ላይ ብቻ አግባብ ባለው አካል ያጫቸውን አጽድቀውና ድርሻቸው ያልሆነውን እና ባለመብቱ ካልተገኘ ገንዘቡ ለመንግስት ገቢ በማድረግ ከመጡ ገቢ የሆነበት ደረሰኝ ተረጋግጦ ወደ ገዥው ስሙ ይዞራል፡፡

## 89. ወራሽነት በኑዛዜ

1. በኑዛዜ ወራሽነታቸው የተረጋገጠላቸው ባለመብት በፍርድ ቤቱ ውሳኔ የተረጋገጠው የኑዛዜ ወረቀት በፍ/ቤቱ ማህተም ተረጋግጦ መቅረብ አለበት፡፡
2. በኑዛዜው ላይ ተሽከርካሪውን እንዲወስድ ስሙ ለተጠቀሰውሰው የመኪና ስም ይዞራል፡

## 90. በፍርድ ቤት ውሳኔ ያለ ሀራጅ የተሽከርካሪ ስም ዝውውር

ፍርድ ቤቶች አንድ ተሽከርካሪ ከባለንብረቱ ወደ ሌላ ሰው በቀጥታ እንዲዞር ሲወስኑ ስሙ ወደ ውሳኔው ባለመብት ይዞራል፡፡

## 91. በፍርድ ቤት ውሳኔ በፍርድ አፈጻጸም አማካኝነት አንድ ተሽከርካሪ በሀራጅ ሲሸጥ

1. የፍርድ አፈጻጸም ተሽከርካሪውን በሀራጅ እንዲሸጥ ፍርድቤት የሰጠው ትእዛዝ፣
2. የፍርድ አፈጻጸም ተሽከርካሪውን በሀራጅ የሸጠበት ሰነድ መቅረብ፣
3. ተሽከርካሪው በሀራጅ ሲሸጥ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ ከሌለና ለገዥ ካልተሰጠ የፍርድ አፈጻጸም መመሪያው ይህንን የሚገልጽ ደብዳቤ መጻፍ፣

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

4. የተሸጠው ተሽከርካሪ ሰሌዳ ያልተሰጠው ከሆነ የተሽከርካሪውን መረጃ ሊኖርስ ለማይችል የጉሙሩክ ዲክላራሲዮን ለተሽከርካሪው እንዲሰጠው አፈጻጸም መምሪያው ለጉሙሩክ በማዘዝ ዲክላራሲዮን ተሰርቶ መምጣት፣
5. ፍርድ ቤቶች በሀራጅ፣አማካኝነት ተሽከርካሪ ሲሸጥ የሞተርና የሻንሲ ችግር ካለበት መብቱ የተላለፈላቸው ሰዎች በተሽከርካሪው ላይ የሚኖራቸው መብት የቀድሞ ባለንብረቱ ያለውን መብት ያህል በመሆኑ ባለ ቀይ ምልክት ሰሌዳ ይሰጣቸዋል፡፡

## 92. ባንክ በዋስትና የያዘውን ተሽከርካሪ በህግ ሲሸጥ

1. ገዥ ከባንኩ የገዛበትን ሰነድና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/ ማቅረብ አለበት፣
2. ባንኮች ተሽከርካሪውን በባለዕዳ ስም እያለ በድርድር መሸጥ አይችልም፣
3. በሁለት ጊዜ የሀራጅ ማስታወቂያ ገዥ ከጠፋና ሊሸጥ ካልቻለ ባንኩ ተሽከርካሪውን ለሌላ ሰው ከመሸጡ በፊት ወደ ራሱ ስም ማዞር አለበት፣
4. ባንኮች በዋስትና የያዙትን ተሽከርካሪ ሁለት ጊዜ ጨረታ አውጥቶ ሊሸጥ ካልቻለ ንብረቱ በብድር ውሉ ውስጥ በሰፈረው የዋጋ ግምት መሰረት ለመውሰድና የባለቤትነት ስሙ ወደ ባንኩ ስም ሊዞርለት ይቻላል፡፡
5. ተሽከርካሪው ወደ ባንኩ ከዞረ በኋላ ባንኩ ተሽከርካሪውን መሸጥ የሚችለው ቀደም ሲል ተሽከርካሪውን በሀራጅ ለመሸጥ ባለው የዋስትና መብት አይደለም፡፡ ባንኮች ወደ ራሳቸው ስም ያዞሩትን ተሽከርካሪ ሲሸጡ እንደማንኛውም ሽያጭ የሚታይ ነው
6. በሁሉም የመብት ማስተላለፊያ ሰነዶች በውጭ ዜጎች መካከል በውጭ ቋንቋ የተፈጸመ ቢሆንም እንኳ የፈጸመው የመብት ማስተላለፊያ ሰነድ በአማርኛ ህጋዊ በሆነ ትርጉም ቤት ተተርጉሞ መቅረብ አለበት፡፡
7. ባንኮች በውርስ አማካኝነት ባለ ቀይ ሰሌዳ ተሽከርካሪው ሲሸጥ የሞተርና የሻንሲ ችግር ካለበት መብቱ የተላለፈላቸው ሰዎች በተሽከርካሪው ላይ የሚኖራቸው መብት የቀድሞ ባለንብረቱ ያለውን መብት ያህል ይሆናል፡፡

## 93. እገዳ ማገድ

አንድ ተሽከርካሪ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በማናቸውም መንገድ ሰነዱ ወደ ሌላ ሰው እንዳይዞር የእገዳ ትእዛዝ የሚቀርበው ከባንክ፣ ከፍርድ ቤት፣ከኢንቨስትመንት ቢሮ፣



ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

4. የተሸጠው ተሽከርካሪ ሰሌዳ ያልተሰጠው ከሆነ የተሽከርካሪውን መረጃ ሊኖርስ ለማይችል የጉሙሩክ ዲክላራሲዮን ለተሽከርካሪው እንዲሰጠው አፈጻጸም መምሪያው ለጉሙሩክ በማዘዝ ዲክላራሲዮን ተሰርቶ መምጣት፣
5. ፍርድ ቤቶች በሀራጅ፣አማካኝነት ተሽከርካሪ ሲሸጥ የሞተርና የሻንሲ ችግር ካለበት መብቱ የተላለፈላቸው ሰዎች በተሽከርካሪው ላይ የሚኖራቸው መብት የቀድሞ ባለንብረቱ ያለውን መብት ያህል በመሆኑ ባለ ቀይ ምልክት ሰሌዳ ይሰጣቸዋል፡፡

## 92. ባንክ በዋስትና የያዘውን ተሽከርካሪ በህግ ሲሸጥ

1. ገዥ ከባንኩ የገዛበትን ሰነድና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/ ማቅረብ አለበት፣
2. ባንኮች ተሽከርካሪውን በባለዕዳ ስም እያለ በድርድር መሸጥ አይችልም፡
3. በሁለት ጊዜ የሀራጅ ማስታወቂያ ገዥ ከጠፋና ሊሸጥ ካልቻለ ባንኩ ተሽከርካሪውን ለሌላ ሰው ከመሸጡ በፊት ወደ ራሱ ስም ማዞር አለበት፡
4. ባንኮች በዋስትና የያዙትን ተሽከርካሪ ሁለት ጊዜ ጨረታ አውጥቶ ሊሸጥ ካልቻለ ንብረቱ በብድር ውሉ ውስጥ በሰፈረው የዋጋ ግምት መሰረት ለመውሰድና የባለቤትነት ስሙ ወደ ባንኩ ስም ሊዞርለት ይቻላል፡፡
5. ተሽከርካሪው ወደ ባንኩ ከዞረ በኋላ ባንኩ ተሽከርካሪውን መሸጥ የሚችለው ቀደም ሲል ተሽከርካሪውን በሀራጅ ለመሸጥ ባለው የዋስትና መብት አይደለም፡፡ ባንኮች ወደ ራሳቸው ስም ያዞሩትን ተሽከርካሪ ሲሸጡ እንደማንኛውም ሽያጭ የሚታይ ነው
6. በሁሉም የመብት ማስተላለፊያ ሰነዶች በውጭ ዜጎች መካከል በውጭ ቋንቋ የተፈጸመ ቢሆንም እንኳ የፈጸመው የመብት ማስተላለፊያ ሰነድ በአማርኛ ህጋዊ በሆነ ትርጉም ቤት ተተርጉሞ መቅረብ አለበት፡፡
7. ባንኮች በውርስ አማካኝነት ባለ ቀይ ሰሌዳ ተሽከርካሪው ሲሸጥ የሞተርና የሻንሲ ችግር ካለበት መብቱ የተላለፈላቸው ሰዎች በተሽከርካሪው ላይ የሚኖራቸው መብት የቀድሞ ባለንብረቱ ያለውን መብት ያህል ይሆናል፡፡

## 93. እገዳ ማገድ

አንድ ተሽከርካሪ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በማናቸውም መንገድ ሰነዱ ወደ ሌላ ሰው እንዳይዞር የእገዳ ትእዛዝ የሚቀርበው ከባንክ፣ ከፍርድ ቤት፣ከኢንቨስትመንት ቢሮ፣



ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

ከገቢዎችና ጉምሩክ የብድርና ቁጠባ ተቋማት እንዲሁም ሌሎች ህግ የሚፈቅድላቸው ናቸው፡፡

1. እግድ የቀረበበት ተሽከርካሪ ፋይል ስለመኖሩ በኮምፒውተር እና በደረቅ ፋይል ውስጥ ስለመኖሩ ማረጋገጥ ፤
2. የእግድ ትእዛዝ ሲመጣ ወደ መ/ቤታችን ገቢ በሆነበት እለት ወዲያው ተሽከርካሪው መታገድ አለበት፡፡መታገዱንም እንዲታገድለት ለጠየቀው አካል ማስታወቅ ፡፡
3. እንዲታገድ የታዘዘውን ተሽከርካሪ በጥያቄው መሠረት የእግድ ደብዳቤና የተሽከርካሪው ፋይል እንዲሁም የኮምፒውተር መረጃዎቹ መጣጣማቸውን ማረጋገጥ፣
4. እግድ በኮምፒውተርና በተሽከርካሪው ፋይል ላይ በትክክል ተመዝግቦ በሠራተኛው ፊርማና ቲተር ማረጋገጥ እና
5. የባንክ እግድ ጥያቄ በባንኩ ወኪል ሲቀርብ አቅራቢው ህጋዊነት እንደአስፈላጊነቱ በማረጋገጥ የገንዘቡን መጠን በሊብሬው ላይ በማስፈር፤ በኮምፒውተር ሲስተም ፋይል እና በሊብሬ ላይ አግዶ ሊብሬውን ለባንኩ ተወካይ ማስረከብ
6. የአገልግሎት ክፍያ በታሪፉ መሠረት ማስከፈል፣
7. ሌሎች ተቋማት በውልና ማስረጃ የፀደቀ የስምምነት ሰነድ ካቀረቡ ተሽከርካሪው ሊታገድላቸው ይችላል፡

94. የፍርድ ቤት ዕግድ

1. የተሽከርካሪው ሰሌዳ ሳይጠቀስ የባለንብረቱ ስም ብቻ ተጠቀሶ እንዲታገድ ሲመጣ በርካታ ተመሳሳይ ስም ሊኖር ስለሚችል ለጊዜው ፋይሉን በጥንቃቄ በማገድ አስፈላጊ ሲሆን ተጨማሪ ማብራሪያ እግዱን ከሰጠው አካል መጠየቅ እና
2. ፍ/ቤቶች ሰሌዳውን ብቻ በመጥቀስ የባለቤቱን ስም አጣርታችሁ ሳይል እንዲታገድ ብቻ ትእዛዝ ከሰጡ ትእዛዙ መፈፀም አለበት፡፡

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

95. ባንኮችና የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት/ድርጅቶች፦

1. ባንኮችና የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት /ድርጅቶች በዋስትና የያዙትን ተሽከርካሪ እንዲታገድላቸው በሚጽፉት ደብዳቤ ጊዜ እግዱ በፋይል፣ በኮምፒውተር፣ በባለቤትነት መታወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ ላይ መመዝገብ አለበት
2. ባንኮችና የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት/ ድርጅቶች ተሽከርካሪ እንዲታገድላቸው በሚያቀርቡት ደብዳቤ ላይ ሌላ እዳና እግዳ፣ ቀረጥ ነጻ እንደሌለበት አጣርታችሁ፤ በአንደኛ ደረጃ እግዱን መዝግቡልን የሚል አገልግሎት አይሰጥም፡፡
3. የፋይናንስ ተቋማት የዕግድ ጥያቄ ሲያቀርቡ ከዚህ በፊት የተላለፈ እግድ አለመኖሩን ማረጋገጥ፣ቀደም ሲል የተመዘገበ እግድ ካለ ይህንኑ በዝርዝር በመግለፅ እንዲታገድለት ለጠየቀው አካል በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት
4. አነስተኛ ብድር አቅራቢ ድርጅቱ ከተሽከርካሪ ባለመብት ግለሰብ ጋር ያደረገውን የብድር ውል ስምምነቱን እና የእግድ ደብዳቤ ሲቀርብ የዕግድ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

96. የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዕግድ፦

- በግለሰቡ ስም ወይም በድርጅቱ ስም፣ ወይም በተሽከርካሪው ላይ የሚፈለግበት ዕዳ እንዳለበት በመጥቀስ እንዲታገድለት ጥያቄ ሲቀርብ አገልግሎት ይሰጠዋል፡፡

97. እግድ ማንሳትን

የእግድ ይነሳልኝ ጥያቄ ቀደም ሲል ዕግድ ከሰጠው ህጋዊ አካላት ሲቀርብ

1. የባለጉዳዩን ማንነትና ህጋዊነት ማረጋገጥ፣
2. የታገደው እግድ እንዲነሳ የጠየቀው አካል በትክክል የእርሱ ሰነድ መሆኑን ማለትም የታገደበት ቀንና ቁጥር፣ የታገደበት ጉዳይ፣ ያገደው አካል ማረጋገጥና የተሽከርካሪ ታሪክ ከደረቅ ፋይልና ከኮምፒውተር ተመሳሳይ መሆኑን ማጣራት
3. ከዕግድ የተነሳ መሆኑ እዳ እገዳ የተመዘገበውን እግድ ከኮምፒውተርና ከፋይል በመሰረዝ ማረጋገጫ መስጠት፣
4. ለተሰጠው አገልግሎት በታሪፉ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል፣



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority

5. እግዱ የሚነሳው በባክንኮችና በአነስተኛ የብድር ተቋማት የታገዱ ከሆነ ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች እንደተጠበቁ ሆነው የብሩ መጠን መገለጽ አለበት
6. በአንድ ተሽከርካሪ ላይ በተለያዩ ባለመብቶች ጠያቂነት በፌደራልና በክልል ፍ/ቤቶች የተሰጡ የተለያዩ እግዶች በተመሳሳይ ጊዜ ከተነሱ ቀድሞ የአፈፃፀም ፋይል ከፍቶ ተሽከርካሪውን ለመረከብ የመጣው የፍርድ ባለመብት በፍርድ ባለ እዳው ይግባኝ ተጠይቆ አፈፃፀሙ እንዳልታገድ ተጣርቶ ተገቢውን አገልግሎት ይሰጠዋል፡፡
7. በአንድ ተሽከርካሪ ላይ በተለያዩ ባለመብቶች ጠያቂነት የተለያዩ የፌደራልና በክልል ፍ/ቤቶች እግድ ቢሰጡና ከፍርድ ቤቶቹ መካከል አንዱ ከባለመብቶቹ ላንዱ እግዱን አንስቶ ፍርድ ቢሰጥና የፍርድ ባለመብቱም የአፈፃፀም ፋይል ከፍቶ አገልግሎት ለማግኘት ሲያቀርብ የሌሎች ፍርድ ቤቶች እግድ ቢኖርም በፍርድ ባለ እዳም ሆነ በሌሎች ባለመብቶች ይግባኝ ተጠይቆ አፈፃፀሙ እንዳልታገደ ተጣርቶ አገልግሎት ይሰጠዋል፡፡

98. **የባለንብረትነት መብትና የሊብሬ ለውጥ፡**

በአንድ ሰው ስም የነበረ የተሽከርካሪ የባለንብረትነት መብት የተጨማሪ ሰዎች የባለንብረትነት መብት እንዲኖሩት ሲጠየቅ፡

1. የተጨማሪ ሰዎች የባለንብረትነት መብት ከፍ/ቤትና መሰል ውሳኔ ሰጭ አካላት ውሳኔ የተሰጠበት ደብዳቤ ሰነድ
2. የባለንብረትነት መብቱን ግለሰቦቹ እራሳቸው ተስማምተው ሰነዱን የማጽደቅ ስልጣን ካለው አካል አጸድቀው ሰነድ ሲያይዙ
3. የባለንብረትነት ስም ለውጥ ክፍያ የቴምብር ቀረጥ 2% የከፈለበት ደረሰኝ
4. ሊብሬ ላይ እነ እነ በሚል የሚመዘገብና የሁሉንም የባለንብረቶቹን ስም ዝርዝር ሊብሬ ላይ ለመጻፍ ቦታ በማይበቃበት ጊዜ በሃርድ ኮፒም ሆነ በሲስተም ላይ ስም ዝርዝራቸው ከነፎቷቸው ሰነዱ አብሮ መያያዝ እና
5. የንግድና የግል ንግድ ተሽከርካሪ ከሆነ የገቢዎች የግብር ክሊራንስ ማቅረብ ሰነድ ተያይዞ ሲቀርብ አገልግሎት ይሰጣል ፡፡

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority

99. **የውርስ ድርሻ መልቀቅን በተመለከተ**

1. በተሽከርካሪ ላይ ያለን የውርስ ድርሻ በነፃም ሆነ በክፍያ ለሌሎች ወራሾች መልቀቅ
2. የውርስ ድርሻ በነፃ የተለቀቀለት ወራሽ ስመ ሀብቱን ወደ እራሱ ስም ለማዞር የሚያስፈልጉ ክፍያዎች መክፈል መሸፈን እና
3. የውርስ ድርሻው በክፍያ የተለቀቀለት ወራሽ ተሽከርካሪውን በሽያጭ ጊዜ እንዲከፍል የሚጠበቅበትን ክፍያ በመፈፀም ወደ ሌላኛው ወራሽ ማዞር አለበት፡፡

100. **ሻጭ በተወካይ መኪናውን ሽጦ ስም ሳያዞር የመኪናው ባለቤት (ሻጩ ወይም ወካዩ) ቢሞት**

1. ሻጭ በተወካይ መኪናውን ሽጦ ስም ሳያዞር ቢሞት ገዥ ትራንስፖርት ቢሮ ቀርቦ የሻጭ ወራሾች ስም እንዲያዞሩለት ይጠይቃል፡፡
2. ወራሾቹ ትራንስፖርት ቢሮ ቀርበው ለገዥ ስም ለማዞር ፈቃደኛ ካልሆኑ ገዥ መብቱን በፍርድ ቤት አስከብሮ በሚያመጣው ውሳኔ መሰረት ስም ይዞርለታል፡፡
3. ሻጭ መኪናውን በተወካይ ሸጦ ስም ሳያዛውር ቢሞትና ወራሾች ባይገኙ ወይም ባይኖሩ ገዥ ከፍርድ ቤት በሚያቀርበው የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት ስም ይዛወርለታል፡፡
4. የንግድና የግል ንግድ ተሽከርካሪ ከሆነ የገቢዎች የግብር ክሊራንስ ማቅረብ ይጠበቅበታል

101. **የተሽከርካሪ የሽያጭ ሂደት ከተጀመረ በኋላ ሻጭ ሲጠፋ**

ሻጭና ገዥ የሽያጭ ውል ፈፅመው ትራንስፖርት ቢሮው በአካል ቀርበው ውሉ ፋይል ውስጥ ተያይዞ የሽያጭ ሂደቱን ጀምረው በመሃል ሻጭ ቢጠፋ እና ለገዥው ስም ማዛወር ካልቻለና ገዥው የስም ዝውውር ጥያቄ ለመዘገበው ተቋሙ ማቅረብ የሚችለው ውሉ ከተፈጸመበት ከ6 ወር በኋላ መሆን አለበት፡፡

ከላይ ከተገለጸው የጊዜ ገደብ በኋላ ገዥው የስም ዝውውር ጥያቄ ለትራንስፖርት ተቋሙ ሲያቀርብ

1. ቀደም ሲል ውሉ ፋይሉ ውስጥ የተያያዘ መሆኑን በማረጋገጥ በሻጭ ወረዳ በኩል ለሻጭ ተፅፎለት በ10 ቀናት የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ወረዳው ቅ/ጽ/ቤቱ የፃፈው ማስታወቂያ እንደደረሰው መልስ ለቢሮው ሲልክ
2. በማስታወቂያዉ መሠረት በ10 ቀን ውስጥ ሻጭ ቀርቦ ስም ለገዥ ካላዛወረለት የትራንስፖርት ተቋሙ የህግ ክፍል ወይም የትራንስፖርት ተቋሙ ሥራ አስኪያጅ ፋይሉን መርምሮ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ማስታወቂያ እንዲያወጣ በባለጉዳዩ ለፕሬስ ደብዳቤ ይፅፋል፡
3. ባለጉዳዩ ማስታወቂያ የወጣበትን የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ይዞ ሲቀርብ ጋዜጣውን ከፋይል ጋር በማያያዝ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ ከ31ኛ ቀን ጀምሮ የትራንስፖርት ተቋሙ እራሱ ለገዥው ስም ዝውውሩን ፈፅሞ ሊብሬ ሰርቶ ለገዢ ያሰረክበዋል
4. ማንኛውንም የአገልግሎት ክፍያ ገዥው ይከፍላል፡፡

## 102. ገዥዉ በውልና ማስረጃ አጸድቆ ሊብሬና ተሽከርካሪውን ገዥ ከተረከበ በኋላ ሻጭ ቅሬታ ካቀረበ

1. የትራንስፖርት ተቋሙ ለሻጭ ምንም ዓይነት አገልግሎት አይሰጥም
2. ሻጭ ይህንን ዓይነት ጥያቄ ለትራንስፖርት ተቋሙ የሚያቀርብ ከሆነ ባለጉዳዩ ገዥውን በፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ በፍርድ ቤት በኩል ውሳኔ ሲቀርብ ብቻ በውሳኔው መሰረት አገልግሎት ይሰጠዋል

## 103. ውል ማፍረስ

የተሽከርካሪ ግምት ከወሰዱ በኋላ ሻጭ ወይም ገዥ ውል ማፍረስ ሲፈልጉ

1. ሻጭና ገዥ በአካል ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት በግንባር ሲቀርቡ
2. የውል ማፍረሻ የስምምነት ሰነድ ሲቀርብ
3. የገዥና ሻጭ የመታወቂያ ኮፒ ሲቀርብ
4. የወሰዱትን የግምት ወረቀት ሲመልሱ
5. የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍሉ አገልግሎት ይሰጣቸዋል

## 104. ባል ወይም ሚስት በስጦታ፣ በውርስ ወይም በሌሎች ሁኔታዎች በግላቸው ያገኙትን ተሽከርካሪ የጋራ ንብረት ስለማድረግ

1. ባል ወይም ሚስት በስጦታ፣ በውርስ ወይም በሌሎች ሁኔታዎች በግላቸው ያገኙትን ተሽከርካሪ የጋራ ንብረት የሚያደርጉት ተሽከርካሪውን የጋራ ንብረት ለማድረግ የተስማሙበት ውል በፍርድ ቤት ሲፀድቅ ብቻ ነው
2. በፍርድ ቤት የፀደቀውን ውሳኔ ይዘው ሲቀርቡ በጋራ በተደረገው ዋጋ ልክ 2% የቴምብር ቀረጥ እና የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል እና
3. የባልና ሚስት የጋራ ንብረት የሆነ ተሽከርካሪን ለመሸጥ የባልና ሚስት በአካል መገኘት ወይም ባል ሚስትን ወይም ሚስት ባልን ወክለው በመቅረብ የሽያጭ ውሉን በሙሉ ስምምነት ፊርማቸውን በማሳረፍና በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት ሲጸድቅ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

## 105. የባልና ሚስት የስም ዝውውር /ድርሻ መልቀቅ/ ጉዳይ

ተሽከርካሪው በባልና ሚስት ስም በጋራ ባለንብረትነት ቆይቶ ባል/ሚስት ባለንብረትነቱን ሲያጠቃልል፡

1. የፍ/ቤት ውሳኔ ሲቀርብ
2. የስም ማዛወሪያ የቴምብር ቀረጥ የአንደኛውን ወገን ድርሻ ሁለት ፐርሰንት 2% ወይም የተሽከርካሪውን ጠቅላላ ዋጋ አንድ ፐርሰንት (1%) ሲከፍል
3. የአገልግሎት ክፍያ አስከፍሎ አገልግሎቱን ይሰጣል

## 106. የባልና ሚስት የተሽከርካሪ ባለንብረትነት መብት

በሚስት/በባል ብቻ ስም ተመዝግቦ የቆየ ተሽከርካሪ ባል/ሚስት የጋራ ባለንብረትነት መብቱ ይታወቅልኝ እና ስሜ ይካተተልኝ ጥያቄ ሲቀርብ፡

1. የፍ/ቤቱ ውሳኔ ሲቀርብ
2. የሁለቱን የባልና ሚስቱን ስም ሊብሬው ላይ በመመዝገብ አገልግሎት መስጠት

## 107. በፕራይቬታይዜሽን ድርጅት ለሚሸጡ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት አሰጣጥ

1. ኤጀንሲው የተጠቀመበት የሽያጭ ሞዳሊቲ/ውል ንብረትን ብቻ ያካተተ ከሆነ ወደ ባለ አደራ ቦርዱ በማስተላለፍ ለገዢው የሚያስተላልፈው ንብረት ተሽከርካሪ ይሆናል፡፡
2. ንብረት ብቻ ለገዢው በሚስተላልፍበት ጊዜ ባለ አደራ ቦርዱ መረጃዎቹን አሰባስቦ ተገቢውን እንደሚፈፅም ይጠበቃል፡፡
3. ኤጀንሲው ድርጅቶቹን ከመሸጡ በፊት ወደ አክስዮን ማህበርነት ለውጦ በሚያዘጋጅበት ወቅት ወደ አዲሱ ኩባንያ ሊተላለፉ የሚገባቸውንና ወደ ባለ አደራ ቦርድ ሊተላለፉ የሚገባቸውን ዕዳዎችና ተሰብሳቢዎች በቅድሚያ በመለየት ለድርጅቶቹ አዲስ የሀብትና ዕዳ ሚዛን ያስተላልፋሉ፡፡
4. ባለ አደራ ቦርዱ የተሽከርካሪዎችን በጨረታ/በውል ስምምነት ሰነድ ለአሸናፊው ድርጅት/ግለሰብ ያሸነፈበትን የእያንዳንዱን የተሽከርካሪዎችን የዋጋ ዝርዝር ከአሸናፊበት ደብዳቤ ማቅረብ
5. በትራንስፖርት ተቋሙ ባለው መረጃ ውልና ማስረጃ መሄድ ሳይጠበቅበት የተሽከርካሪዎች ግምት ተሰልቶ የሁለት ፐርሰንት (2%) የቴምብር ቀረጥ ክፍያ አስከፍሎ ማስተጋገድ

**ይህ በሚሆንበት ጊዜ፡-**

1. ኤጀንሲው ለአዲሱ ኩባንያ የተላለፉትና የማይተላለፉት ዕዳዎችና ተሰብሳቢዎች በመለየት ድርጅቶቹንና ባለአደራ ቦርዱን ያሳውቃል፡፡
2. ድርጅቶቹና ባለአደራ ቦርዱ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሶስተኛ ወገኖች በጽሁፍ ያሳውቃሉ፣ በዚሁ አፈጻጸሙን ይከታተላሉ፡፡

## 108. የጉምሩክ ዕዳዎችን በሚመለከት

1. የጉምሩክ ቀረጥ ሳይከፈልበት በነፃ የገባ ተሽከርካሪ ወደ ሶስተኛ ወገን የሚተላለፍ ከሆነ ቀረጡ በቅድሚያ እንዲከፈል ይደረጋል፡፡
2. ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲው ድርጅቶቹን ሲሸጥ የተሽከርካሪ ዋጋ እንደ አዲስ በመተመን በገበያ ዋጋ ሲሸጥ እንደማንኛውም የሽያጭ ሁኔታ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
3. ያልተከፈለ ዕዳ ሲኖር ገዥውን አይመለከትም እንደዚህ ዓይነት ተሽከርካሪ ሲያጋጥም፡-

ሀ. ኤጀንሲውና ድርጅቶቹ ተሽከርካሪውን በመለየት የቀረጥ ተመን እንዲሠራለት ለጉምሩክ ባለስልጣን ያሳውቃሉ፡፡

ለ. ኤጀንሲው ተመኑን ተቀብሎ ለአፈፃፀሙ ወደ ባለአደራ ቦርድ በማስተላለፍ እና

ሐ. ንብረቶቹ ካለምንም ውጣ ውረድ ለአዲሱ ገዢ ወይም ደግሞ ለሽያጭ ወደ ሚዘጋጀው አዲስ አክስዮን ማህበር ይዛወራሉ፡፡

## 109. የመተባበር ግዴታ

ይህ መመሪያ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 110. የተሻሩ መመሪያዎች

1. በአዋጅ 468/1997 የወጡት የተሽከርካሪ አካል ለውጥ፤ የሻንሲና ሞተር ቁጥር መለወጥ መመሪያዎች እና የተሽከርካሪ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽረዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተጠቀሰው ቢኖርም በዚህ መመሪያ እና ከዚህ መመሪያ በፊት በባለስልጣኑ የወጡ መመሪያዎች ቢቃረኑ በዚህ መመሪያ ላይ የተገለጹት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 111. መመሪያውን የማሻሻል

ይህንን መመሪያ ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በከፊልም ይሁን በሙሉ ሊያሻሽለው ይችላል

## 112. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ መጋቢት 01 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ካሳሁን ኃ/ማርያም

የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር

ካሣሁን ኃ/ማርያም
ዋና ዳይሬክተር

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

## አባሪ 1. አዲስ/ያላገለገሉ/ ተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ምርመራ ሂደት

| ተ.ቁ | ክንውን | ምርመራ |
|---|---|---|
| 1 | በጉምሩክ የትራንስፖርት ባለስልጣን የፍተሻና ምርመራ ጣቢያ ተወካይ፡-<br>➢ ተሽከርካሪው በሕጋዊ መልኩ ስለመግባቱ በሚቀርብለት ማስጫኛ ሠነድ መሠረት የጉምሩክ ቀረጥ ከመከፈሉ በፊት ተሽከርካሪው በሀገሪቱ ደረጃ /Standard/ መሠረት መሆኑን በምርመራ ያረጋግጣል፣መረጃ በኮምፒውተር ኔትወርክ ለባለሥልጣኑ መ/ቤት ያስተላልፋል፣ለተገልጋዩ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ | |
| 2 | መረጃ አጣሪና የደንበኞች አገልግሎት /እንግዳ ተቀባይ/፡-<br>➢ ባለጉዳይ ወይም ሕጋዊ ተወካይ ማመልከቻ ፎርም እንዲሞላ ያደርጋል፡፡<br>➢ ለአዲስ ተሽከርካሪ ምርመራና ምዝገባ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ሰነዶች፣<br>• የማስገቢያ ፈቃድ ከፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን<br>• በጉምሩክ የፍተሻ ጣቢያ ከትራንስፖርት ባለስልጣን የስታንዳርድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት<br>• ዲክላራሲዮን ዋናውን<br>• ተሽከርካሪው የተመዘነበት የሚዛን ማስረጃ /ሚዛን ለሚያስፈልጋቸው<br>• ማስገቢያ ፈቃድ /በግል የገቡ<br>• ተሽከርካሪው ከሕጋዊ አስመጪ የተገዛ ከሆነ ሻንሲና ሞተር ቁጥር እንዲሁም የማስገቢያ ፈቃድ ቁጥርና ቀን የያዘ የተገዛበት ማስረጃ /ኢንቮይስ/<br>• መታወቂያ ፎቶ ኮፒ እና ከ6 ወር ወዲህ የተነሱት 2 ጉርድ ፎቶ መሟላቱን በማረጋገጥ ማመልከቻው ተላላፊ ለመውሰድ የቀረበ ከሆነ ሰነዶቹን ተቀብሎ ተላላፊ ይሰጣል፡፡<br>• ደንበኛው ተሽከርካሪውን ለምርመራ ሲያቀርብ ተሽከርካሪውን ከነቁልፉ በመቀበል የምርመራ ኮድ ለባለጉዳዩ በመስጠት ቁልፉን ለዕይታ መርማሪ ቴክኒሻን ያስተላልፋል፡፡ | |

| ተ.ቁ | ክንውን | ምርመራ |
|---|---|---|
| 3 | ገንዘብ ተቀባይ፡- <br> ➢ የተላላፊ ፣ የሊብሬ ፣ የቦሎ ፣ የሠሌዳና የሌሎች አገልግሎት ክፍያን ይቀበላል፡፡ | |
| 4 | የዕይታ ምርመራ ቴክኒሻን፡- <br> ➢ ተሽከርካሪውን ከነቁልፉ ከማሽን መርማሪ ቴክኒሻን በመቀበል፡- <br> • የሕዝብ መጓጓዣ ተሽከርካሪ ከሆነ የተሣፋሪ ብዛትን ይወስናል፡፡ <br> • የደረቅ ጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ ከሆነ ከሚዛን ጣቢያ በቅጽ ተሞልቶ በመጣው የነጠላ ክብደት ውጤት መሠረት ነጠላ ክብደቱን ቀንሶ ጭነቱን ይወስናል፡፡ <br> • የፈሣሽ ጭነት ከሆነ ጭነቱን ወደ ሊትር ለውጦ በቅጽ ይሞላል፡፡ <br> • የተሽከርካሪ አረግራጊ ክፍሎች /Suspension System/ እና የጭስ መውጫ ክፍሎችን ጨምሮ ሌሎች የተሽከርካሪ አካላትን ለትክክለኛ አገልግሎት ብቁ መሆናቸውን በእይታ በማረጋገጥ ውጤቱን በኮምፒውተር መዝግቦ በመፈረም ስፔስፊኬሽኑን ለምዝገባ ሠራተኛ ያስተላልፋል፡፡ ቼክ ሊስት ተያይዟል፡፡ | |
| 5. | ምዝገባ ሠራተኛ፡- <br> ➢ በመርማሪ ቴክኒሻኖች በኮምፒውተር ኔትወርክ የተላለፈውን የምርመራ ውጤት ከሠነድ ጋር በማገናዘብ ሊብሬና ቦሎ አዘጋጅቶ በመፈረም ለሠሌዳ ሰጭ እና ማሕደር ሠራተኛ ይሰጣል፡፡ | |
| 6. | ሠሌዳ ሰጭና ማሕደር ሠራተኛ፡- <br> ➢ ክፍያ መፈጸሙን አረጋግጦ በማስፈረም ሠሌዳ ሊብሬና ቦሎ ለባለጉዳይ ይሰጣል፡፡ <br> ➢ የተሽከርካሪውን ማሕደር በአግባቡ ይይዛል፡፡ <br> ➢ ከላይ ከመርማሪ ቴክኒሻን በኮምፒውተር ኔትወርክ የተላለፈው መረጃና ከእንግዳ ተቀባይ የተላለፈውን የሠነድ መረጃ አለመጣጣም ከታዩ ለንዑስ የሥራ ሂደቱ አስተባባሪ ያስተላልፋል፡፡ | |

አባሪ 2፡ የኢ.ምባሲዎች፣ የዓለም አቀፍና የዕርዳታ ድርጅቶች የሰሌዳ አይነቶችና የቀለም ቅብ

| ተ.ቁ | የሰሌዳው ዓይነት | የቀለም ህብርና መለያ ቁጥር/የፊደላት ጥምርታ | ትርጉም |
|---|---|---|---|
| 1. | የኢ.ምባሲ.ዎች፡የዓለም አቀፍና የዕርዳታ ድርጅቶች፣ | ነጭ መደብ ከደብዛዛ ሰማያዊ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራና ቀኝ ክንፍ ቢጫ ቀለም ላይ ኮዲ፣ የተመ፣ CD እና UN የሚል ጽሁፍ የሚገኝበት | በተባበሩት መንግስታት መስሪያ ቤት ውስጥ የዲፕሎማቲክ መብት ላላቸው ባለስልጣናት ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 2. | | ነጭ መደብ ከደብዛዛ ሰማያዊ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራና ቀኝ ክንፍ የተመ እና UN የሚል ጽሁፍ የሚገኝበት | ለተባበሩት መንግስታት መስሪያ ቤት ወይም ለመስሪያ ቤቱ አባላት ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 3. | | ነጭ መደብ ከደብዛዛ አረንጓዴ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራና ቀኝ ክንፍ ቢጫ ቀለም ላይ ኮዲ፣ አሕ፣ AU እና CD የሚል ጽሁፍ የሚገኝበት | በአፍሪካ ሕብረት መስሪያ ቤት ውስጥ የዲፕሎማቲክ መብት ላላቸው ባለስልጣናት ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 4. | | ነጭ መደብ ከደብዛዛ አረንጓዴ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራና ቀኝ ክንፍ አሕ እና AU የሚል ጽሁፍ የሚገኝበት | ለአፍሪካ ሕብረት መስሪያ ቤት ወይም ለመስሪያ ቤቱ አባላት ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 5. | | ነጭ መደብ ከጥቁር ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በመሀል ቀኝ ክንፍ በቢጫ ቀለም ላይ ኮዲ እና CD የሚል ጽሁፍ የሚገኝበት | ለዲፕሎማቲክ መልዕክተኞች ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 6. | | ነጭ መደብ ከብርቱካናማ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር በግራና ቀኝ ክንፍ ኮዲ እና CD የሚል ጽሁፍ የሚገኝበት | በተራድኦ ድርጅት መስሪያ ቤት ውስጥ የዲፕሎማቲክ መብት ላላቸው ባለስልጣናት ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |
| 7. | | ነጭ መደብ ከብርቱካናማ ፊደላትና ቁጥሮች ጋር | በተራድኦ ድርጅት እና በእርዳታ ለሚመጡ ባለሙያዎችና ግለሰቦች ተሽከርካሪዎች የሚሰጥ |

## አባሪ 3 የተሽከርካሪ ጠቅላላ ስታንዳርድ

| ተ.ቁ | መግለጫ | መለኪያ | ስፔስፊኬሽን |
|---|---|---|---|
| 1 | የተሽከርካሪው ልክ /ጠቅላላ ይዘት ከዚህ መብለጥ የለበትም | ሚ/ሜ | - |
| 1.1 | የአካሉ ርዝመት | በሜትር | 12.00 |
| 1.2 | የአካሉ ከፍታ | በሜትር | 4.2 ቢጭንም ባይጭንም |
| 1.3 | እስከ 30 መቀመጫ ድረስ /በር/ | በቁጥር | 1 ለተሳፋሪ በቀኝ |
| | ከ30 መቀመጫ በላይ | በቁጥር | 2 ለተሣፋሪ በቀኝ |
| | የበር መጠን | ሚ/ሜ | ስፋት 800 ቁመት 1850 |
| 1.4 | የመወጣጫ ደረጃ | ሚ/ሜ | 420 ቢያንስ |
| | የመጀመሪያ ደረጃ ከመሬት | ሚ/ሜ | 250 |
| | ሁለተኛ | ሚ/ሜ | 250 |
| 1.5 | ተ/ፋ አካል ኦቨርሀንግ | ሚ/ሜ | |
| | የፊት | ሚ/ሜ | 0.21Xየአካል ርዝመት |
| | የኋላ | ሚ/ሜ | 0.30Xየአካል ርዝመት |
| 1.6 | ከመሬት በላይ ያለ ክፍተት እስከ 30 መቀመጫ | ሚ/ሜ | 250 ቢያንስ |
| | ከ30 መቀመጫ በላይ | ሚ/ሜ | 300 ቢያንስ |
| 1.7 | የመነሻ አንግል | ዲግሪ | 10 ቢያንስ |
| 1.8 | የመድረሻ አንግል | ዲግሪ | 12 ቢያንስ |
| 2 | የተሣፋሪዎች መጓጓዣ ክፍል | | |
| 2.1 | በጣራና በወለል መካከል ያለ ርቀት | ሚ/ሜ | 1900 |
| | ወንበር | | |
| 2.2 | ወንበር በሙሉ ወደፊት የሚያዩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ | | |
| | በተርታ ወንበሮች መሀል ያለ ርቀት | ሚ/ሜ | 700+ 30(መደገፊያ) |
| 2.3 | መተላለፊያ | ሚ/ሜ | 350 |
| 2.4 | የመቀመጫ መጠን | ሚ/ሜXሚ/ሜ | 400X400 |
| 2.5 | የመቀመጫ ከፍታ ከወለል | ሚ/ሜ | 400 |
| 2.8 | የተሽከርካሪ መሪ | | በግራ በኩል |

## አባሪ 4. የጭነት ተሽከርካሪ ስታንዳርድ

| ተ.ቁ | መግለጫ | መለኪያ | ስፔስፊኬሽን |
|---|---|---|---|
| 1. | የተሽከርካሪ ልክ /ጠቅላላ ይዘት መጠን | | |
| | ▪ የአካሉ ስፋት | ሜትር | ከ2.50 ያልበለጠ |
| | ▪ የአካሉ ከፍታ | ሜትር | ከ4.20 ያልበለጠ ቢጭንም ባይጭንም |
| | ▪ የአካሉ ርዝመት ቪልቶ | ሜትር | ከ12.00 ያልበለጠ |
| 3. | የተሽከርካሪው መሪ | | በግራ በኩል |



## አባሪ 5. የህዝብ ተሽከርካሪ አካል ለውጥ የጭነት መወሰኛና ሞዴል

| No | Make and model | GVW KG | TARE WEIGHT /KG/ | DECK LENGTH /MM/ | No. of Rows | Seat Arrange ment | No OF SEATS | REMARK |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ISUZU NPR 58G | 5500-6000 /5800/ | ≤ 3700 | 3475 | 5 | 2+2 | 20+1 | |
| 2 | ISUZU NPR 58L | 5800 | ≤ 3700 | 4325 | 5 | 2+2 | 20+1 | Extra Space 275ሚ.ሜ ይቆረጣል |
| 3 | ISUZU NPR 58L | 5800 | ≤ 3700 | 4325 | 5 | 2+2 | 20+1 | Extra Space 275ሚ.ሜ ይቆረጣል |
| 4 | ISUZU NPR 66L | 5500-7000 /6300/ | ≤ 3800 | 4250 | 6 | 2+2 | 24+1 | |
| 5 | ISUZU NPR 66L | 5500-7000 /6300/ | ≤ 3800 | 4250 | 6 | 2+2 | 24+1 | |
| 6 | ISUZU NPR 66P | 6300 | ≤ 3800 | 4910 | 6 | 2+2 | 24+1 | It has Extra Space |
| 7 | ISUZU NPR 66P | 6300 | >> | 4910 | 6 | 2+2 | 24+1 | >>>>>>>> |
| 8 | ISUZU NPR 71P | 8000 | ≤ 3800 | 4910 | 7 | 2+2 | 29+1 | |
| 9 | ISUZU NQR 71R | 8000 | >> | 4810 | 7 | 2+2 | 29+1 | |
| 10 | ISUZU FSR 33L | | ≤ 7000 | 6070 | 8 | 3+2 | 39+1 | |
| 11 | IVECO CC1 50E 21H | 16000 | ≤ 9900 | 7830 | 11 | 3+1 | 54+1 | |
| 12 | IVECO CC1 50E 21H | 16000 | ≤ 9900 | 8800 | 12 | 3+2 | 60+1 | If there is original broacher |
| 13 | IVECO 150E 18H | 15000 | ≤ 10500 | 5823 | 8 | 3+2 | 39+1 | |
| 14 | IVECO 150E 18H | 15000 | >> | 6583 | 9 | 3+2 | 44+1 | If there is original broacher |
| 15 | MERCEDES OF 1318 | 13000 | ≤ 8500 | 6570 | 9 | 3+2 | 44+1 | |
| 16 | MERCEDESS OF 1721 | 17000 | ≤ 10900 | 9750 | 12 | 3+2 | 60+1 | 590 ሚ.ሚመቆረጥ አለበት |

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No 1

## አባሪ 6. ወደ ህዝብ ተሽከርካሪ የሚለወጡ ሞዴሎች

| No | Make and model | GVW KG | TARE WEIGHT/KG/ | DECK LENGTH/MM/ | No.of Rows | Seat Arrangment | No OF SEATS | REMARK |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ISUZU FSR33L | 11000 | ≤ 7000 | 6540 | 9 | 3+2 | 44+1 | |
| 2 | ISUZU FTR33M | 14200 | 9000 | 6600 | 9 | 3+2 | 44+1 | |
| 3 | ISUZU FVR 23P | 15000 | 10500 | 7300 | 10 | 3+2 | 49+1 | |
| 4 | NISSAN MK210 | 10400 | 5900 | 6600 | 9 | 3+2 | 44+1 | |
| 5 | ELCHER 10-70 | 6750 | 4250 | 4540 | 6 | 2+2 | 24+1 | |
| 6 | MITSUBISHI FE645E6L | 6300 | 3800 | 4550 | 6 | 2+2 | 24+1 | |
| 7 | MITSUBISHI FE659F6L | 7000 | 4500 | 4660 | 6 | 2+2 | 24+1 | |
| | MITSBISHI FE659F6L | 7,000 | ≤4,500 | 5,200 | 7 | 2X2 | 28+1 | |
| 8 | IVECO135-17 | 20000 | 15000 | 7300 | 10 | 3+2 | 49+1 | |
| 9 | DAF 2500 | 24000 | 9040 | 8030 | 11 | 3+2 | 54+1 | |
| 10 | ISUZU NLR55E | 3,300 | ≤ 1,900 | 3,120 | 4 | 2X1 | 14+1 | |
| 11 | ISUZU NPR71H | 7,000 | ≤ 3,800 | 4,300 | 6 | 2X2 | 29+1 | NPR6SN |
| 12 | ISUZU NPR71K | 7,000 | ≤ 4,200 | 5,300 | 7 | 2X2 | 28+1 | NPR6SN |
| 13 | ISUZU NPR75K | 7,000 | ≤ 4,200 | 5,110 | 7 | 2X2 | 28+1 | NPR6SN |
| 14 | ISUZU NQR71L | 8,000 | ≤ 4,900 | 5,670 | 8 | 2X2 | 31+1 | NPR6SS |
| 15 | ISUZU FRR12HA | 8,150 | ≤ 4,500 | 5,100 | 7 | 2X2 | 29+1 | |
| 16 | ISUZU FRR33H | 10,600 | ≤ 6,500 | 6,200 | 8 | 2X3 | 40+1 | |
| 17 | ISUZU FSR6M | 11,000 | ≤ 7,000 | 6,580 | 9 | 2X3 | 44+1 | |
| 18 | ISUZU FVR33P | 15,100 | ≤ 10,000 | 7,300 | 10 | 2X3 | 49+1 | |



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 19 | MITSBISHI FE84PE6L | 6,350 | ≤ 4,100 | 4,350 | 6 | 2X2 | 24+1 | |
| 20 | MITSBISHI FM617LHL | 14,030 | ≤8,500 | 7,300 | 10 | 2X3 | 49+1 | |
| 21 | I56120G MITSUBISHI | 16,000 | ≤ 10,000 | 9,500 | 13 | 2X3 | 64+1 | |
| 22 | TATA LPT1116 | 11,500 | ≤6,700 | 6,000 | 8 | 2X3 | 39+1 | |
| 23 | TATA LPT1618TC | 16,000 | ≤8,500 | 7,L300 | 10 | 2X3 | 49+1 | |
| 24 | NISSAN CP87L | 14,500 | ≤9,750 | 6,700 | 9 | 2X3 | 44+1 | |
| 25 | HYUNDAI HD 72 | 7,200 | ≤4,400 | 4,860 | 7 | 2X2 | 48+1 | |
| 26 | MANCLA 18-220 | 18,000 | ≤11,000 | 9,500 | 13 | 2X3 | 65+1 | 1PASSNGER DOOR INFRONT OF FOH |
| 27 | ISUZU NQR75L | 8,000 | ≤4,900 | 5,670 | 8 | 2X2 | 31+1 | NPR6SS |

## አባሪ 7. ወደ ሕዝብ ማመላለሻነት ሊቀየሩ የማይችሉ ሞዴሎች

| NO | MAKE & MODEL | GVW KG | TARE WEIGTH /KG/ | DECK LENGTH/MM/ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ISUZU NPR 58P | 5500-6000 /5800/ | ≤ 3700 | 4985 |
| 2 | ISUZU NPR 58P | 5500-6000 /5800/ | ≤ 3700 | 4985 |
| 3 | ISUZU NPR 66G | 5500-7000 /6300/ | ≤ 3800 | 3400 |
| 4 | ISUZU NPR 66G | >>>> | ≤ 3800 | 3400 |
| 5 | ISUZU NQR 71H | 8000 | >> | 4250 |
| 6 | ISUZU FSR 33F | 11.000 | ≤ 7000 | 4470 |
| 7 | ISUZU FSR 33H | >> | ≤ 7000 | 5120 |
| 8 | IVECO 135-17 | 13.300 | ≤ 8300 | 5830 |
| 9 | IVECO 150E-18H | 15.000 | ≤10500 | 3973 |
| 10 | IVECO 150E-18H | >> | >> | 4558 |
| 11 | IVECO 150E-18H | >> | >> | 5233 |
| 12 | IVECO 150E-18H | >> | >> | 5395 |
| 13 | IVECO 190.30H | 19000 | ≤ 9900 | - |
| 14 | IVECO 190.30H | 19000 | ≤ 11400 | - |
| 15 | FIAT 110 NC | 11001 | ≤ 6500 | - |
| 16 | FIAT 110 PC | 11000 | ≤ 6500 | - |